

© Safeguarding Religious Treasures of the Ethiopia Orthodox Church.

# ፈለገ ጥበብ

ሚያዝያ - ሰኔ ቁጥር ፩ ፲፱፻፺፪ ዓ.ም



✣ ጉዞ ወደ ምድረ ምሁር
✣ [illegible]
✣ የተሰቀለው ተነሥቶአል
✣ ሐተራውያን

www.ethiopianorthodox.org

እኛና እናንተ

# እኛና እናንተ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
ለሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ
ፈለገ ጥበብ መጽሔት

በጅማ ሀገረ ስብከት በያዝነው የሥራ ዘመን በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ ሲሆን ለአብነት ያህል የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል:-

፩. በጅማ ሀገረ ስብከት የሚተዳደሩ ፲፫ ወረዳዎች አሉ፤ ወሰናችንም በምሥራቅ ትልቁ ግቤ በምዕራብ ኢሉባቦር ሀገረ ስብከት በሰሜን ወለጋ በደቡብ ዳውሮ ያዋስኑናል። ስለሆነም ጅማ ዓመት እስከ ዓመት ለምና አረንጓዴ ነው።

፪. በ፲፫ ወረዳዎች ለሚገኙት ሊቃነ ካህናት በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ በብፁዕ አቡነ ሳሙኤል ሰብሳቢነት በተሠጠው የሥራ መመሪያ ከማንኛውም ጊዜ በተሻለ ስብከተ ወንጌል እንዲስፋፋ፤ የሰንበት ት/ቤቶች እንዲጠናከሩ እና ልማት በቤተክርስቲያን እንዲስፋፋ እየተደረገ ነው። በተሰጠው የሥራ መመሪያ ሁሉም ስብከተ ወንጌልን በማስፋፋት ሰ/ት/ቤቶችን በማጠናከር ከፍተኛ የሆነ ጥረት እየተደረገ ነው።

፫. በዚሁ ዓመት ፱ አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናት ተሠርተው አገልግሎት እየሠጡ ነው፡

፬. ፫ አብያተ ክርስቲያናት በዘመናዊ መልኩ እየተሠሩ ሲሆን በተለይ የጅማ ደብረ ኅሀል ቅ/ሚካኤል ቤተክርስቲያን ካቴድራል በብር ፪ ሚሊዮን ፯ መቶ ሺህ (ሁለት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሺህ ብር) የሚፈጅ ትልቅ ሕንፃ እየተሠራ ነው። በመሆኑ በመልአኩ ተራዳኢነት ሕንፃው ከተጠበቀው በላይ በመፋጠን ላይ ይገኛል፡

፭. በየወረዳው የሰንበት ት/ቤት ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ተቋቁሟል፡

፮. ካህናት የባህርይ ለውጥ እንዲያደርጉና ንስሐ ልጆቻቸውን ከመናፍቃን ነቅ ተው እንዲጠብቁ በሰዓት የተወሰነ ሳምንታዊ የሙያ ማሻሻያ እየተሰጠ ነው። በዚሁ የትምህርት ፕሮግራም ውስጥ ጅማ እንዴት ሰነበቱ በሚል ርዕስ ውይይት በማድረግ አመርቂ ውጤት እያስገኘ ነው።

፯. ፩. የቅዳሴ መምህር ፩. የዝማሬ መዋሥዕት መምምህር ፩. የአቋቋም መምህር ተቀጥረው በርካታ ተተኪ የቤተ ክርስቲያንን ልጆች እያስተማሩ ነው።

፰. አንድ መዋዕለ ሕፃናት ለመክፈት እቅድ ተይዞ ጥረት እየተደረገ ነው።

፱. የስብከተ ወንጌል ማሪሚያ ቤት ለሕግ ታራሚዎች እየተሰጠ ከመሆኑም ባሻገር ስብከቱን ቋሚ ለማድረግ ከማረሚያ ቤቱ ኃላፊዎች ጋር ባደረግነው ውይይት እና የደብዳቤ ልውውጥ አዳራሽ ለመሥራት ቦታ ተሰጥቶን ሥራውን ለመጀመር እየጣርን ነው።

፲. በአሁኑ ዘመን ልመና እንደ ልዩ ፋብሪካ የገቢ ምንጭ ሆኖ የተያዘ ቢሆንም በተለይ በቤተ ክርስቲያን ዙሪያ የቤተክርስቲያንን ንዋየ ቅድሳት ዘርግተው የሚለምኑ በቁጥር ለመጥቀስ አዳጋች ነው። ከሚገርሙ አብዛኛው ማለት ይቻላል የልማና ፈቃድ እና ካርኒዎች ይዘው ይገኛሉ። ይህንም ከክልሉ የሚመለከታቸው የመንግሥት ባለሥልጣናት ጋር በመተባበር በሀገረ ስብከታችን ልመና እንዲቆም አድርገናል። ለዚህ ክትትል የሚያደርጉ ልዩ መታወቂያ ያላቸው ሠራተኞችን አሠማርተናል።

፲፩. በክብረ በዓል እና በወርኃ በዓላት በእየአድባራቱ የሚገባውን መብዓ (ስዕለት) በሀገረ ስብከቱ በሚደረገው ቁጥጥር በመጠኑ ብክነትን እየተቋቋምን ነው።

፲፪. ከመሐል ከተማ ከሚገኙት አድባራት አንዱ በሆነ በደብረ ሰላም ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ስም ሠፊ የልማት ቦታ ከኦሮሚያ ከተማ ልማት በተደረገው የስበካ ጉባኤ እና በሀገረ ስብከቱ ጥረት ፲ ሺህ (አሥር ሺህ) ካሬ ሜትር መሬት ተረክበው በቦታው ላይ ከመቶ ሺህ የማያንስ ለአገልግሎት የደረሰ የባሕር ዛፍ ተክል የለማበት ሲሆን በዚህ ዓመትም ከአምስት መቶ ሺህ የማያንስ ባሕር ዛፍ ለመትከል ታቅዷል።

በሀገረ ስብከታችን ፪፻፭ አብያተ ክርስቲያናት ይገኛሉ። ከነዚህም መካከል ፴ዎቹ ታላላቅ አድባራት ናቸው በሁሉም መንፈሳዊ አገልግሎት እየተሠጠ ነው።

ሊቀ መዘምራን ብርሃኑ ጌጡ

ተ/ሥራ አስኪያጅ

• • •

ለውድ የፈለገ ጥበብ አዘጋጆች
ከሁሉ አስቀድሜ የከበረ ሰላምታዬን አቀርብላችኋለሁ።

ውድ አዘጋጆች! ጥንታዊት ሐዋርያዊትና ብሔራዊት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ያፈራቻቸው ልጆችዋ በየጊዜው እያዘጋጁ የሚያወጧቸው ጋዜጦችና መጽሔቶች ሕዝበ ክርስቲያኑን እራሱን ከነጣቂ ተኩላ እንዲጠብቅ ከፍተኛ እገዛ እንደ አደረጉ የታመነ ቢሆንም በተለይ የፈለገ ጥበብ መጽሔት ቁጥር ፫ ጥር ፲፱፻፺፪ ዓ.ም ፍጹም ባማረና በተከሸነ ሁኔታ መውጣት ደግሞ የአንባቢያንን ሕይወት በይበልጥ እንዲለውጥና በራስ መተማመን እንዲኖር ማገዙን መመስከር ይቻላል።

መጽሔቱ በዋናው ሽፋን ካለው ዕፁብ ድንቅ ሥዕል ጀምሮ እስከ መጨረሻው አምድ ድረስ ያለው ቁም ነገር አንድ ጊዜ አንብበህ የምትረካው ሳይሆን ደግመህ ደጋግመህ እንድታነብ የሚጋብዝና እራስህን ወዴት ነው ያለሁት? ብለህ እንድታይ የሚያደርግ ነው። በተለይ ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን በተመለከተ የቀረበው ጽሑፍ ጥቅምና ጉዳቱን ሳይለዩ እገሌ ቆረበ እኔም ልቁረብ ለሚሉ፤ ከቁርባን በፊት ማስተማር የሚገባንን ሳናስተምር በድፍረት ቁረቡ ለምንል ካህናት፤ የሰጠው ትምህርት እጅግ ከፍተኛ ከመሆኑ በላይ እኛ ካህናትም በዘልማድ ቤተ መቅደስ ስንገባ በቅዳሴ ጊዜ የምንለውና የምናደርገውን ከነትርጓሜው ለይተን እንድናውቅ የረዳን ስለሆነ ጸሐፊውን አመስግኑልኝ።

እንደዚሁም እንደ ዓይናችን ብሌን የምናያቸውን አባቶች ሊቃውንት እድሜና ጤንነትን ይስጣችሁ፤ ቃለ ሕይወት ያሰማችሁ፤ በሉልኝ እናንተ አዘጋጆችንም ብርታቱን ሰጥቶአችሁ ለሦስት ወር ሳይሆን በየወሩ እንድናገኛችሁ ቅዱስ ፈቃዱ ይሁንልን አሜን።

ቀሲስ ጥበቡ ቢያደርግልኝ – ከኮተቤ

• • •

መጽሔቷን ወድጄታለሁ

ለፈለገ ጥበብ መጽሔት ዝግጅት ክፍል መጽሔትዋን በጣም ወድጄታለሁ። ይሁንና ወደ ደቡብ በአብዛኛው ስለማትዳረስ ብዙዎቹ የሰንበት ት/ቤት ተማሪዎች ተጠቃሚ አልሆኑም። ግፋ ቢል የምትመጣው አርባ ምንጭ ድረስ ነው። ከዚያ ሌላ ቦታ የሚወስድ የለምና፤

ስለዚህ እኔ በበኩሌ ለዶርዜ ሆሎኦ ቅዱስ ሚካኤል ደብር፤ ለዶርዜ ላካ ተክለ ሃይማኖት፤ ለዶርዜ ጐዲዮ በዓለ ወልድ፤ እንዲሁም ለዶርዜ አደይራ ቅዱስ ዮሐንስና ቅዱስ ጊዮርጊስ አብያተ ክርስቲያናት መጽሔቷ እንዲታመልጣቸው በግሌ ገንዘብ ከፍዬ በፖስታ ቤት በኩል እንዲደርሳቸው ስለምፈልግ ለአምስቱም አብያተ ክርስቲያናት የዓመት ሂሳቡን አስልታችሁ ብትልኩልኝ ወይም በስጠኋችሁ አድራሻ መሠረት አዲስ አበባ ያሉት ዘመዶቼን አነጋግራችሁ ሁኔታውን እንድታመቻቹልኝ እጠይቃለሁ።

ወታደር እንዳልካቸው ገላዬ – ፰ኛ ክ/ጦር ፪፻፴ኛ አየር መቃወሚያ ብርጌድ ፪ ሺህ ፺፪ ሻለቃ ፆረና ግንባር

• • •

ከአዘጋጅ – መልእክትህን አድርሰናል፤ በተረፈ በእግዚአብሔር ኃይል በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት ግዳጅህን በድል ፈጽመህ እንድትመለስ ጸሎታችን ነው።




# ፈለገ ጥበብ

፪ኛ ዓመት ቁጥር ፬

ሚያዝያ ፲፱፻፺፪ ዓ.ም


## ከአዘጋጁ ብዕር

ፈለገ ጥበብ ቁጥር አራት በዓለ ሆሣዕናን ተንተርሳ ብቅ ስትል ብርሃነ ትንሣኤው ለሁላችሁም የደስታና የሰላም በዓል እንዲሆንላችሁ በመመኘት ነው። ከእናንተ ከአንባቢያን ከሚደርሱን የማበረታቻ መልእክቶችና ጥቆማዎች በመነሳት የመጽሔቷን ጥራት ከእትም እትም ለማሻሻል ጥረታችንን ቀጥለናል።

እንዳለፉት እትሞቻችን ሁሉ ዛሬም በቋሚ አምዶቿ በታወቁ የቤተክርስቲያን ሊቃውንት የተዘጋጁ ለቀጣዮቹ ሦስት ወራት ብቻ ሳይሆን ለዓመታት አብሮዋችሁ የሚቆዩ ቋሚ ጽሑፎችን ይዛ እነሆ ትላችኋለች። በሆሣዕና ጀምረን ስቅለትን፤ ትንሣኤን፤ ዳስሰናል። ሥርዓተ ቤተክርስቲያንና ትምህርተ ሃይማኖትን የሚተነትኑ፤ ዝግጅቶቻችንም እንዳሉ ናቸው። እኔም ወጣት ነበርኩ በሚል ዓምዳችን እንጋፋውና ታላቁ አባት ብፁዕ አቡነ ሚካኤልን ይዘንላችሁ ቀርበናል።

በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿ በተለይ ደግሞ ወጣቱን ትውልድ እየተፈታተኑ ስላሉ የኤድስና የመናፍቃን ወረርሽኞችም የምንለው ይኖረናል። ኤድስ አምራቹን፤ የነገ ሀገርና ቤተክርስቲያን ተረካቢ የሆነውን ወጣት ክፉኛ እያጠቃው ይገኛል። ባለፈው እትማችን ይህንን በተመለከተ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ያስተላለፉት ትምህርታዊ ጽሑፍ ይዘን መቅረባችን ይታወሳል። ዛሬም ቅዱስ ፓትርያርኩ ይህንን ቀሳፊ በሽታ አስመልክተው በተለያዩ ጊዜያት ካስተላለፉዋቸው መልእክቶች አንኳር አንኳሮችን በቃለ በረከት አምዳችን አስፍረናል። የመጽሔታችን ቋሚ ጽሑፍ አቅራቢ ብፁዕ አቡነ ገሪማም ለአሁኑ በኤድስ ዙርያ ጠቃሚ ትምህርት ይኖራቸዋል።

የመናፍቃኑን ወረርሽኝ በተመለከተም ፈለገ ጥበብ የምትዳስሰው ነጥብ አለ። የመናፍቃን ዋና ዓላማ እነርሱ እንደሚሉት ክርስቶስን ለመስበክ (ለ፪ ሺህ ዓመታት ክርስቶስ በተሰበከባት ሀገር) ሳይሆን የሀገር ዋልታና ምሰሶ ሆና የቆየችውንና ያለችውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንን አዳክሞና አፍርሶ ሕዝባችንን ንግሥቲቱ የሞተችበት የንብ ሠራዊት አድርጎ ለባዕዳን ማስረከብ ነው። በዚህ በኩል የጉራጌ ማኅበረሰብ እየወሰደው ያለ ሕጋዊና ሰላማዊ እርምጃ ለሌሎችም አርአያነት አለው ከሚል ቃኝተነዋል። ሌሎችም አሉን። ማንበቡንና የእርምት አስተያየቱን ለናንተ እንተወዋለን።

አምላከ ኢትዮጵያ ከሁላችን ጋር ይሁን


ዋና አዘጋጅ:- ካሕሳይ ገ/እግዚአብሔር

ም/ዋና አዘጋጅ:- መልአከ ሰላም ኃይለ ኢየሱስ ከበደ

ስልክ 11–23–69/11–34/25

ፖ.ሣ.ቁ.81286

አዲስ አበባ



በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ት/ቤቶች

ማደራጃ መምሪያ

በየ፫ ወሩ የሚዘጋጅ መጽሔት


## ማውጫ


✣ ቃለ በረከት . . . . . . . . . . ፪

✣ ሆሣዕና . . . . . . . . . . ፫

✣ የተሰቀለው ተነሥቶአል . . . . . ፯

✣ ሕገ እግዚአብሔር ይጠበቅ . . . . . ፲፩

✣ ትምህርተ ሃይማኖት . . . . . . . ፲፬

✣ መግረሬ ፀር
የዲያብሎስን ሥራ ይሽር ዘንድ
የእግዚአብሔር ልጅ ሰው ሆነ . ፲፯

✣ እኔም ወጣት ነበርኩ . . . . . . . ፳

✣ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን
ምሥጢረ ንስሐ . . . . . ፳፬

✣ ከወጣቱ ለወጣቱ . . . . . . . . ፳፯

✣ ጉዞ ወደ ምድረ ምሁር . . . . . ፳፰

✣ እግዚአብሔር ለሕዝቡ
በመጽሐፍ ይነግራቸዋል . . ፴፩

✣ እስትጉብእ
ሐቁተ ራይቶች . . . . . ፴፫



ኤዲተሮች

ሊቀ ካህናት ኃይለ ሥላሴ ዓለማየሁ


ቀሲስ በላይ ተገኝ

መጋቤ ብሉይ ሠይፈሥላሴ ዮሐንስ


www.ethiopianorthodox.org

# ቃለ በረከት

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት በተለያዩ ጊዜያት ካስተላለፉት ቃለ በረከት የተወሰዱ ምርጥ ጥቅሶች።



«...ከአበው የወረስነውን ቀና ሃይማኖት፣ በጎ ምግባር፣ አኩሪ ባህልና መልካም ስም እያጣጣልን ሀገራችንን በኤድስ በሽተኞች ብዛት ማኅደር ማስመዝገቡ በእጅጉ የሚያሳፍርና የሚያሳዝን ነው። የኢትዮጵያዊነታችንንም ክብር በእጅጉ የሚነካ ነው። በአንፃሩ አሁን ያለው የተማረ፣ ሀገሩን የሚያፈቅርና ለእናት ሀገሩ ሉዓላዊነት የሚጋደል ትውልድ፣ በራሱ ባህልና ታሪክ በመኩራት፣ ሥነ ሥርዓት በማክበር፣ ሕገ እግዚአብሔርን በመጠበቅ የሚከበርና የሚፈራ ትውልድ ሊሆን ይገባዋል። ስለዚህ ሁሉም ሰው ወንድ ሴት ሳይል ፈጣሪውን ከልቡ እየለመነ፣ ንስሐ እየገባ፣ በሥርዓት እየኖረ የኤድስን መቅሰፍት ከሀገራችን ለመከላከልና ለማጥፋት በትሑት መንፈስ፣ በሙሉ ልብ ሊነሳሳ ይገባዋል። ዋናውና ብቸኛው የበሽታው መከላከያ ስልት አምላክን ይዞ ጉዞ ነው። እግዚአብሔር በረድኤቱ እንዳይለየን ተግተን እንጸልይ፤ የምሕረት ፊቱን ወደኛ እንዲመልስ ጥዋት ማታ ባለመታከት እንማለደው፤ ድኅነት የሚገኘው ከርሱ ብቻ ነውና።»

✣ ✣ ✣

«...ኃጢአት ሰውን የሚበላ እንጂ የማይበላ የሲኦል ስንቅ ስለሆነ ማጠራቀሙ ምንም አይበጅም። የሲኦል እሳት የጋለ እቶን ስለሆነ የኃጢአት ቤንዚን አያሻውም። ማንኛውም ሰው ዛሬውኑ ጌታ እንዳዘዘው ለመምሕረ ንስሐው ኃጢአቱን እየተናገረ በእግዚአብሔር ፊት በንስሐ እየወደቀ፣ እየተነሣ፣ የኃጢአት ሸክሙን በማራገፍ፣ ከበሽታ መንጻት አለበት።»

ጥቅምት ፳፮ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ.ም በአዲስ አበባ ስታድየም ካስተላለፉት ቃለ በረከት የተወሰደ

✣ ✣ ✣

«ቤተክርስቲያናችን ኅብረተሰቡ በራሱ ቋንቋና ፊደል የሥነ ጽሕፈት፣ የሥነ ጥበብና የኪነ ጥበብ፣ የሥነ ሕንፃና የቅርፃ ቅርፅ በአጠቃላይም የረቀቀ ዕውቀት እንዲኖረው የአስደናቂ ቅርስ ባለቤት እንዲሆን አድርጋለች። ብሔራዊ መልክና ውበት ያለው ሥዕል እንዲሥል፣ ብሔራዊ ሥልተ ድምፅና ቃና ባለው ዜማ እንዲያዜም፣ በራሱ ምሥጢራዊና ብሂላዊ ኅዳና በቋንቋው ቅኔ እንዲቀኝ አስተምራለች። የትምህርትና ሥነ ጥበብ፣ የፍትሕ፣ የመንፈሳዊና የማኅበራዊ አገልግሎት ኃላፊም በመሆን የብዙ ዓመታት አገልግሎት አበርክታለች። በአጠቃላይ ኅብረተሰቡ ለፍትሕና ለርትዕ፣ ለነፃነትና ለእኩልነት፣ ለፍቅርና ሰላም፣ ለአንድነትና ለኅብረት ሚዛናዊ አመለካከት ሊኖረው የቻለም በዚች ጥንታዊት ቤተክርስቲያን ሐዋርያዊ ተልእኮ መሆኑን ማንም የማያስተባብለው እውነት ነው።»

መጋቢት ፲፩ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ.ም ለጋዜጠኞች ከሰጡት መግለጫ



# ሆሣዕና

መዝ.፻፲፰፣፳፭–፳፮ ፣ማቴ.፳፩፣፱ ፣ዮሐ.፲፪፣፲፫

በመልአከ ሰላም ዳኛቸው ካሣሁን



ይህ ቃል በሚነገርበት (በሚሰማበት) ጊዜ በውስጡ፣

- ሆሣዕና ማለት ምን ማለት ነው?
- የሆሣዕና በዓል ለምን ይከበራል?
- በሆሣዕና ዕለት የሰሌን (ዘንባባ) ቅጠል የሚታደለው ለምንድን ነው?
- በሆሣዕና በዓል አከባበር የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት እንዴት ነው? የሚሉ ጥያቄዎች በሕሊና እንደሚመላለሱ የታወቀ ነው።

ለነዚህ ጥያቄዎች መልስ መስጠት የሆሣዕናን ትርጉም፣ በዓሉ የሚከበርበትን ምክንያትና ከታሪኩ የሚገኘውን ትምህርት ግልጽ ያደርገዋል።

ቃሉ በሁለት ቋንቋዎች የተሰጡ ትርጉሞች አሉት። በግእዙ መድኀኒት ማለት ነው። የሰው ልጆች የድኅነት ባለቤት የሆነውን እውነተኛ መድኀኒት ኢየሱስ ክርስቶስን ከማዳን ሥራው አንጻር ይገልጻል። በአረማይክ ልሳን ደግሞ ከዚሁ ብዙ ያልተራራቀ ፍች አለው «አሁን አድነን፣ ርዳን፣ እንድታድነን፣ እንድትታደገን እንማልድሀለን» ማለትን ያሳያል።

እሥራኤል አጥፍተው፣ በድለው፣ በጥፋታቸው ቅጣት በመጣባቸውና ለጠላት በተጋለጡ ቁጥር መሸሻቸውና መጠጊያቸው የእግዚአብሔር ቸርነት ነበር! ከጭንቀታቸው ተላቀው ችግራቸው ታወግዶ ነፃ ሆነው ሲሰነብቱ ይዝናናሉ! እንደገና ይበድላሉ! በቅጣት ወጥመድ ሲያዙ ወደ እግዚአብሔር ይጮኻሉ። አድነን ርዳን ልንጠፋ ነው አውጣን ይላሉ። በዚሁ መንፈስ በዓለ መጸለትን በሚያከብሩበት ጊዜ ለሰባት ቀን በየቀኑ አንድ ጊዜ፣ በ፯ኛው ቀን ሰባት ጊዜ በደብተራ አሪት ዙሪያ እየዞሩ። «ሆሣዕና በአርያም» እያሉ ይዘምሩ ነበር። እኛም ዛሬ በበዓለ ሆሣዕና በቤተ ክርስቲያን ዙሪያ እየዞርን የምንዘምረው ያን ታሪክ መሠረት በማድረግ ነው።

የሆሣዕና በዓል የሚከበረው ጌታችን መድኀኔታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእድግትና ዕዋል (በአህያና ውርንጭላዋ) ተቀምጦ፣ በብዙ ሕዝብ ታጅቦ፣ በሕፃናት ምስጋና ወደ ቤተ መቅደስ የገባበትን ታላቅ የክብር፣ የገቢረ ተአምራትና የምሥጋና ቀን ለማሰብ ነው።

የሆሣዕና ዕለት የሰሌን (የዘንባባ) ቅጠል በቤተ ክርስቲያን የሚታደለው (የሚሰጠው) ጌታ ወደ ቤተ መቅደስ ለመግባት ጉዞ ባደረገበት ጉዳና የነበሩ ብዙ ሰዎች የሰሌን ቅጠል የወይራና የልዩ ልዩ ዛፎች ዝንጣፊ እየያዙ በመንገዱ ላይ እየነዘነዙ፣ የኃይልና የድል ባለቤት መሆኑን እየገለጹ፣ በክብር በምስጋና በዝማሬ በይባቤ እንደተቀበሉት የሚናገረውን ታሪክ በማስተጋባት ለእውነተኛው መድኀኒት፣ ለድልና የክብር ባለቤት ለኢየሱስ ክርስቶስ የሚገባውን ዝማሬና ምስጋና ለማቅረብ ነው።

የጥንቱ እሥራኤል ድኅነትን ሲሹ በሙሴ ድንኳን በመሥዋዑ ዙሪያ እየዞሩ ይዘምሩ፣ ያመሰግኑ እንደ ነበረ ጌታም ቤተ መቅደስ በደረሰ ጊዜ ሦስት ጊዜ ዞሮአል። ያንን ምሳሌ አድርገን የዘንባባ ቅጠል ይዘን ሆሣዕናን እየዘመርን በቤተ ክርስቲያን ዑደት እናደርጋለን።

በዑደቱ ሥርዓት መጀመሪያ በቅድስተ ቅዱሳን (በመቅደስ) ውስጥ ስለበዓለ ሆሣዕና በገፃዊው በተመለከተው መሠረት ከቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ምንባብ ይነበባል። ከዚያ በኋላ በምዕራብ በር ተወጥቶ በደቡብ፣ በምሥራቅ፣ በመዞር በሰሜን በር ይገባል። በአራቱም ማዕዘናት ምስባክ ይሰበካል፣ ወንጌል ይነበባል፣ በዓሉን የተመለከተ የቅዱስ ያሬድ ድጓ ይዘመራል።

ካህናቱ ሰሌኑን (ዘንባባውን) ለሕዝቡ ሲያበረክቱ (ሲሰጡ) «ያለ ደዌና ያለ ሕማም ያለፃማና ያለ ድካም፣ እግዚአብሔር እንደዛሬ ቀን በደስታና በፍቅር፣ በአንድነት ያድርሰን፣ ያድርሳችሁ» ይላሉ። ሕዝቡም አሜን እያሉ ይቀበላሉ።

ሁሉም ሥርዓትና እንቅስቃሴ የክብር ባለቤት ኢየሱስ ክርስቶስ በምስጢረ ሥጋዌው የፈጸመውን የቸርነቱን ሥራ የሚገልጽ ነው። ዑደቱም፣ ጸሎቱም፣ ወደሱ መቅረብን፣ ከባሕርይ ጌትነቱ የሚገኘውን በጎውን ስጦታ ሁሉ ለማግኘት መሻትን ያመለክታል።

እግዚአብሔር እውነተኛ መጋቢ ነው። ፍጥረት ሁሉ የማይቋረጠውን ምግብና የሚያገኘው ከእሱ ብቻ ነው። ሰው የሚሰጠው ከሰጪው ከእግዚአብሔር ያገኘውን ነው። ሰጥቶ ስለሚያልቅበት፣ ሠፍሮ ስለሚጉድልበት፣ ብልፅግናው ፍጹም አይደለም፤ እግዚአብሔር ግን የሚሰጠው ከባሕርይ ጌትነቱ ስለሆነ ለነፍሳችንና ለሥጋችን በሚያስፈልገን ሁሉ ወደ እግዚአብሔር መለመን እንደሚገባን ቅዱሳት መጻሕፍት በየክፍሉ ያስረዱናል።

ነቢዩ ኤርምያስ «ትሹኛላችሁ ታገኙኛላችሁ በፍጹም ልባችሁ ብትፈልጉኝ እገኝላችኋለሁ» ብሏል። (ኤር.፳፱፣፲፫)።

ዳዊትም በመዝሙሩ «እግዚአብሔርንና ኃይሉንም ፈልጉ ፊቱንም ፈልጉ ሁል ጊዜ ሹት» ብሎ ጽፎአል (መዝ.፻፬፣፫)

ከዚህም ሁሉ ጋር ጌታችን መድኀኔታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ለምኑ ይሰጣችኋል፣ ሹ ታገኛላችሁ፣ ደጅ ምቱ ይከፈትላችኋል» ብሎ ያስተማረው ከሱ የምንሻውን ለማግኘ



www.ethiopianorthodox.org

ታችን የማይጠራጠሩት መተማመኛ ነው። እነ ቅዱስ ጳውሎስ «በተስፋችሁ ደስ ያላችሁ በመከራውም የምትታገሡ ሁኑ፤ በጸሎትም ተጸመዱ» በማለት ያስተማሩት በችግራችንና በፈተና ጊዜ ሁሉ ታግሠን ሳንሰለች መለመን፤ ሳንታክት መሻት፤ ተስፋ ሳንቆርጥ በእምነት የእግዚአብሔርን ቸርነት መጠየቅ እንዳለብን የሚያመለክት ነው። (ሮሜ.፲፪፥፲፪)

«ሆሣዕና አቤቱ ፈጥነህ አድነን፤ እንድት ታደገን እንማልድሀለን» የሚለው አገላለጽ በችግር ማዕበል በምንከበብበት ጊዜ ከጭንቁ ለማውጣት ከሃሊነት የባሕርይ ገንዘቡ የሆነውን አምላክ መጠየቅ እንዳለብን ይነግረናል።

ዘንባባና የልዩ ልዩ ዛፎች ዝንጣፊ (ቅጠል) ይዞ በሠልፍ መታየት የድልና በድል የተገኘ የደስታ መግለጫ ነው።

የሆሣዕናውን ታሪክ በሚገልጸው የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ እንደምንመለከተው «ከውርንጭላዋ ጋር የታሠረች አህያ ታገኛላችሁ ፈትታችሁ አምጡልኝ» የሚል ትእዛዝ ለደቀ መዛሙርቱ መስጠቱን እና ያለን። ሰው ሁሉ ከማዕሠረ ኀጢአት መፈታቱን የሚያበስር መልእክት ነበር፤ የታሠረችውን አህያ ከነውርንጭላዋ ፈትተው እንዲያመጡ የታዘዙት ደቀ መዛሙርት ወደ በሚሠራው የኃጢአት ገመድ የታሠረውን፤ ሰብአዊ ክብሩን በእንስሳት ግብር ለውጦ እንስሳትን የመሰለውንና የኃጢአት መጫኛ የሆነውን ዓለም ከበደል እሥራቱ እንዲፈቱ የኃጢአት ሸክሙን እንዲያቀሉለትና ወደ ልጅነት ክብር እንዲጠሩት «በምድር የፈታችሁት በሰማይ የተፈታ ይሆናል።» የሚለው ክህነታዊ ሥልጣን የተሰጣቸው መሆኑን ያሳያል።

በጌታ የተጠሩ፤ ከጌታ የተማሩ፤ ትእዛዙን መመሪያውን የተቀበሉ ሐዋርያት ያስተማሩት ወደ ሕይወት ባለቤት የጠሩት ሰው ሁሉ የልጅነትን ክብር ለማግኘት፤ የዘለዓለም ሕይወት ወራሽ ሊመሆን፤ ከልካይ አይኖርበትም፤ የኃጢአት ማሠሪያ ተብትቦ ሊያስቀረው አይችልም «ምን ታደርጋላችሁ? የሚላችሁ ቢኖር ጌታቸው ይሻቸዋል በሉ፤ ያን ጊዜ ላኪው ማን እንደሆነ ያውቃል ያሰናብታችኋል» ነው የተባለው። እግዚአ ብሔር የላከው እንዲህ በሥራው ይታወቃል፤ የሚከተለው ምልክት በሥራ ተገልጾ ይታያል። ከጌታ የተላኩ ሐዋርያት (መም ህራን) የሚታወቁት የሚከተላቸው ምልክት ከኃጢአት እሥራት ሲፈታ ከልዩ ልዩ ደዌ ሲፈውስ በተለያየ የፈተና ወጥመድ ውስጥ የገቡትን አውጥቶ ወደ ሕይወት መንገድ ሲመራ ነው፤ በፍሬ መታወቅም ይኋል ይህ ነው።

ለጽዮን ልጅ ንገሯት ጻድቅ የባሕርይ አምላክ፤ የዋህ ኃዳጌ በቀል፤ ንጉሥሽ በአህያና በውርንጭላዋ ተቀምጦ ይመጣል» ተብሎ በነቢያት የተነገረው ይደርስ፤ ይፈጸም ዘንድ እግዚአ ነቢያት ጌታ በእንስሳ ጀርባ ተቀምጦ ወደ ቤተ መቅደስ ገባ። ለጽዮን ልጅ ንገሯት ያለ ኢሳይያስ፤ ንጉሥሽ ይመጣል ብሎ የተናገረ ዘካርያስ ነው። ኢሳይያስ እንደ አባት እንደ መምህር ኤርምያስ እንደ ልጅ እንደ ደቀ መዝሙር ሆነው በአንድ መንፈስ ምሳሌያዊ ትንቢቱን ተናግረዋል።

ጌታ በአህያ የመቀመጡ ምሥጢርም በምሳሌ የሚገልጸው ታላቅ ትምህርት አለው። የቀድሞ አበው ነቢያት ዘመኑ ፍቅርና ሰላም የጠፋበት፤ ፀብ ክርክር ጦርነትና ችግር ያለበት ከሆነ በፈረስ በሠረገላ ተቀምጠው ዘገር ነጥቀው ይታያሉ፤ ዘመኑ ሰላም የሆነ እንደሆነ በአህያ ተቀምጠው መነሳንስ ይዘው በሕዝቡ መካከል ይመላለሳሉ። አንደኛው የችግርን ጊዜ ሲያመለክት ሌላው የሰላምን ተስፋ ይተረጉማል። በሌላም ገጹ በአህያ የተቀመጠ ሸሽቶ አያመልጥም አሳዶ አይዝም። ጌታም በዚህ ሥዕላዊ መልእክት ያስተማረው ካልሹኝ አልገኝም፤ ከሹኝም አልታጣም» የሚለውን ታላቅ ትምህርት ነው።

ምሥጢረ መጻሕፍት የነፍስን ጥራት የሚያረካ የሕይወት ፈሳሽ ነው። መጻሕፍትን በንባባቸው ብቻ እማራለሁ፤ አስተምራለሁ፤ እረዳለሁ፤ አስረዳለሁ ማለት ያልተለቀመ እህል መፍጨት ነው፤ ያልተለቀመ የወፍጮ እህል ወፍጮ ያበላሻል፤ የፈጪውንም ጉልበት ያደክማል። መንፈስ እግዚአብሔር ያደረበት በመንፈስ እግዚአብሔር የተቃኘ ሰው ምሥጢረ መጻሕፍትን እያፍታታ ሲናገር፤ ሲጽፍ፤ ሲያስተምር፤ መልካም ዋነተኛ ይመስላል፤ በምስጢር ባሕር ገብቶ የሚዋኝ መምህር ሌሎችንም ወደ ዋናው ይስባል፤ ይጋብዛል፤ የዕለተ ሆሣዕና የጌታችን ወደ ቤተ መቅደስ ጉዞ ሥዕላዊ ታሪኩ፤ ምሳሌያዊ ትምህርቱና በውስጡ የሚታየው ምሥጢራዊ መልእክቱ ልቡናን ደስ የሚያሰኝ ነው።

እድገት:- (እናቲቱ አህያ)

በኢየሩሳሌም (በጽዮን)፤ በእናት፤ በሕግ

በእሥራኤል

በኦሪት ስትመሰል

ውርንጭላዋ ደግሞ

በልጅ፤ በአሕዛብ፤ በእሥራኤል

በወንጌል አንጻር ተሥላ፤ በሁለቱም አንጻር በምሥጢር የበለጸገ ምሳሊያዊ ትምህርት ተሰጥቶባቸዋል። መልካም እናት ልጆችዋን በሕግ በሥርዓት፤ ቀጥታ በሥነ ምግባር አሠልጥና እንደምታሳድግ ሕግም የሰውን ልቡና በዕውቀት ልጓም ጉትታ በሥርዓት ታኖራለች። እድገት ጭነት፤ የሠረገላ ቀንበር፤ መሸከም የለመደች እንደሆነች በእድገት አንጻር የተጠቀሱ እሥራኤልም ሕግ መጠበቅን በሕግ፤ በሥርዓት፤ መኖርን የለመዱ መሆናቸውን ያሳያል። የሙሴን ሕግ ተምረዋል፤ በትንቢተ ነቢያት ታንጸዋል። ሕግ ያልተማሩ፤ በሕግ በሥርዓት ተቀጥተው ያላደጉ፤ ሁሉን ላፊ፤ ሁሉን ለሆዱ የሚሉ አሕዛብ ግን በሕግ በሥርዓት ለመኖር ችግር ያለባቸው መሆኑን አነፃፅሮ ይገልጻል። በኦሪትና በወንጌል አንፃር የተነ ገረው ኦሪት የታወቀች የተለመደች ወንጌል ያልተለመደች ሕግ መሆኗን ያስትምራል። ጌታ ወደ ቤተ መቅደስ ሲያመራ በናፍቆት ያጅቡት የነበሩ ሰዎች፤

ልብሳቸውን ደለደሉለት፤ ኮርቻ ይቆረቁ ራል፤ ልብስ ይደላል፤ የማትቆረቁር ሕግ ወንጌል መሠራቷን ያሳያል።

ልብስ በአካል ያለውን ነውር ይሠውራል (የሰውነትን ገበና ይሸፍናል) አንተም ከባቴ አበሳ ነህ የሰውን በደል በትዕግሥትህ ትሠወራለህ ማለትን ያሳያል።

ልብሳቸውን አነጠፉለት፤ ቅጠሉን ጐዘጐዙለት፤ ስንኳን አንተ የተቀመጥህባት አህያ መሬት መርገጥ አይገባትም ሲሉ ነው።



አበባና ዘንባባ የመስጠትን ታሪክ ስንመ ለከት እግዚአብሔር ለሕዝብ አስተዳደር መርጦ መሪ ባነገሠ ጊዜ (፪ነገ.፱፥፲፫)

ደጋግ ልጆች ሲወለዱ፤ ከባርነት ቀንበር ከግፍ አገዛዝ ነጻ ሲወጡ፤ በወራሪ ጠላት ቢመሪር አገዛዝ ላይ ድል በተገኘ ጊዜ የዘንባባ ቅጠል የልዩ ልዩ ዛፎች ቅጠሎችና የአበባ ጉንጉኖች ይዞ ደስታን መግለጥ የተለመደ ነው። በተለይ ሰሌን ለጌታ መቀበያ የተያዘበት ምሥጢር፤

ሰሌን እሾኻም ነው። ትእምርተ ኃይል ትእምርተ መዊዕ (የኃይልና የአሸናፊነት ምልክት) አለህ ለማለት ነው፤

እሳት አይበላውም ለብልቦ ይተወዋል፤ ባሕርይህ አይመረመርም ማለትን ያሳያል። በተምርና በወይራ ቅጠል አንጻርም ሌላ ኅብር ተነግሮአል። በሁሉም ምሳሌ የተነገረውና የተገለጸው ክብሩንና ጌትነ ቱን፤ አሸናፊነቱንና ቸርነቱን፤ ባሕርዩንና ልግስናውን ለኛ ለማስተማር የተጻፈ ነው።

ወደ ቤተ መቅደስ በተጓዘበት ጊዜ ብዙ ሕዝብ ተከትሉት ነበር፤ በፊትም በኋላም የነበሩት «ሆሣዕና በአርያም ለዳዊት ልጅ መድኀኒት መባል ይገባል፤ በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ የተባረከ ነው። መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስን የሚያርቅ፤ በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስን የሚያድል ነው። በሰማይ ያለ መድኀኒት» እያሉ በዝማሬ ያመሰግኑት ነበር። ኢየሩሳሌም ከተማ በገባ ጊዜ ከተማዋ ታወከች፤ ተሸበረች፤ የፊቱ ብርሃን ፀሐይን ሲበዛብዛት ዐይታ፤ የሕፃናትን ምስጋና ሰምታ፤ በልዩ ልዩ ደዌ የተያዙ ሰዎች ቀርበው ሲፈወሱ፤ ከደዌ እሥራት ሲፈቱ፤ ከጭንቅ ከኀዘን ነጻ ሆነው በደስታ ሲያመሰግኑ ተመል ከታ:- መሥዋዕት ሊሠውላቸው ዕጉለ ርግብ ዘውገ ማዕነቅ ይዘው ወላጆቻቸው ወደ ቤተ መቅደስ ያወጡአቸው የዓርባ፤ የሰማኒያ፤ የመንፈቅ፤ ያመት፤ ያመት ከመንፈቅ፤ የሁለትዓመት ሕፃናት በዚህ ሠልፍ ተገኝተው ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ቤተ መቅደስ በገባበት ወቅት የምስጋናው ተካፋይ ሆነዋል። ብቻ ሕፃናትም አይደሉ አዕባን (ድንጋዮችም) በሰ ብአዊ ልሳን አመስግነዋል። የሕይወት ባለቤት የፍጥረት ሁሉ ጌታ ነውና ፍጥረት ሁሉ ያመሰ ግነዋልና። የተወለዱ ብቻ ሳይሆኑ በማኅፀን (በጽንስ ደረጃ) ያሉ ሕፃናትም ያመስግ ኑታል። (ሉቃ.፭፥፶፩–፲፱፥ ፴፰–፴፰)

አዎ እግዚአብሔርን በጌትነቱ የማያመ ሰግኑ፤ እግዚአብሔር በውነተኛ መንገድ ሲመሰገን ደስ የማይላቸው፤ ለአምልኮቱ የማይቀኑ፤ በቀና ሃይማኖት የሚያገለግሉትን፤ የሚያመሰግኑትን፤ የሚያጥላሉ፤ የሚነቅፉና የሚያሰናክሉ፤ የነበረውና ያለው የማያስ ደስታቸው፤ ሁል ጊዜ በእንግዳ ትምህርት የሚወሰዱ ሰዎች አሉ። ያወቁትና ያመኑበት ወገኖች ለክብሩ ለጌትነቱ ለምለም ቅጠልና ሽቱ ያለው የጠጅ ሣር በመጐዝጐዝ ወይም በኅብረ ቀለማት ያጌጠ ዕቅፍ አበባ በመያዝ ብቻ ሳይሆን ልብሳቸውን አንጥፈው ሲቀበሉት፤ አፋቸውን ያልፈቱ ሕፃናት ሲያመሰግኑት፤ መንፈስ ቅንዓት ያደረባቸው ወገኖች «ሊቅ ኢትሰምዕኑ ዘይብሉ እሉ ሕፃናት መምህር እነዚህ ሕፃናት የሚሉትን አትሰማምን? ዝም እንዲሉ ዝም እንዲያሰኙ ደቀ መዛሙርትህን ገሥጻቸው» ነበር ያሉት። ጌታ ወደከተማዋ በደረሰ ጊዜ የሚያሳዝን እንጂ የሚያስደስት የሚያስለቅስ እንጂ የሚያጽናና መልካም የሕይወት ሥዕል አልታየውም። «ወሶበ ርእያ ለሀገር በከየ ላዕሌሃ» አገሪቱን ዓይቶ አለቀሰላት፤ አውቀሽስ ቢሆን የይቅርታሽ ቀን የሰላምሽ ጊዜ ዛሬ ነበር፤ ግን አላወቅሽም፤ ዕውቀትሽ ከዓይንሽ ፊት ተሠውሮአል። ከዕውቀት ተገተሻል። ስለዚህ ጠላቶችሽ ከበው የሚሠ ፍሩብሽ ጊዜ ይደርሳል፤ ይከትሙብሻል፤ ዙሪያሽን ያጥሩታል፤ ከዓራቱ ማዕዘን ይሰበ ሰቡብሻል ይጥሉሻል፤ ልጆችሽንም ካንቺ ጋራ እንዳንቺ ይጥሉአቸዋል። ደንጊያ በደንጊያ ላይ አይተውልሽም የይቅርታሽን ቀን አላወቅሽምና» በማለት የኢየሩሳሌም ከተማ የነበረባትን ጉድለትና ያልታያትን የሰላም ቀን ወደፊትም ይመጣባት ዘንድ ያለውን ጥፋት አስመልክቶ ተናገረ። ከተማውን ዘልቆ ወደ ቤተ መቅደሱ በገባ ጊዜ ያገኘው ሁኔታም በከተማው ከነበረው የከፋ እንጂ የተሻለ አልነበረም። ቤተ መቅደሱ የሻጮችና ለዋጮች የነጋዴዎችና አትራፊዎች ገበያ ሆኖ ነበር። ምንም ሠርተው ምንም ሆነው ተሯሩጠው ያተረፉ የሚደሰቱበት፤ የከሠሩ የሚያዝኑበት የንግድ ማዕከል ቀማኞችና ወንበዴዎች፤ ሌቦችና ሸፋጮች የመሸጉበት የአመጽ ዋሻ ሆኖ ነበር። ጌታችንን ከልብ ያሳዘነው፤ የትዕግሥትን ባለቤት እጅግ ያስቆጣውና ለቅጣት ያነሳሳው ጥፋት ነበር። የስሙ መመስገኛ የጌትነቱ መመስከሪያ በሆነ ቤተ እግዚአብሔር የሚያስነቅፍ የሚያስ ነውርና ስመ እግዚአብሔርን የሚያሰድብ ሥራ እንዳይኖር በብርቱ ያስጠነቅቀናል።

«እግዚአብሔር ፈታሒ በጽድቅ ኮናኒ በርትዕ ነው፤ ኃያል ነው፤ ታጋሽም ነው፤ ሰው ባጠፋና በበደለ ቍጥር መዓትን ላምጣ አይልም፤ ሰው ከስሕተት መንገዱ ባይጸጸት ከገቢረ ኀጢአት ወደ ገቢረ ጽድቅ ባይመለስ ግን ሰይፎ ይመልህ በስብአ ትካት በሶብአ ሰዶም በሰብአ ገሞራ የመዘዘውን ሰይፉን ሰይፈ መዓቱን ይመዛል» እንደ ተባለ (መዝ.፯፥፲፩) ጌታ በዕለተ ሆሣዕና በቤተ መቅደስ የተመለከተው ጥፋት በትዕግሥት የሚታለፍ ይቅርታ የሚገባው ሆኖ አል ተገኘም። ስለዚህም የሺያጮችንና ለዋጮችን ገንዘባቸውን በተነባቸው፤ መደብራቸውን አፈረሰባቸው፤ የሸቀጥ መደርደሪያ ጠረጴዛቸውን ገለባበጠው፤ በማይገባው ቦታ የማይገባ ሥራ ይሠሩ የነበሩትን ሁሉ ከአፀደ ቤተ መቅደስ አስወጥቶ አባረራቸው። ቤተ መቅደስ ምን እንደሆነች ለምን እንደ ተሠራች የሚፈጸምባት ተግባር ምን እንደሆነ ግልፅ በማድረግ «ቤቴ የጸሎት ቤት ትባላለች» ብሉ አስተማራቸው።

ጌታችን ያልወደደው፤ ያልተቀበለውና በዝምታ ያላለፈው አሳፋሪ ድርጊት በረድ ኤትና በምስጋና በሚኖርበት ቤተ እግዚአ ብሔር የሚፈጸመውን ሥርዓት፤ የሚሠዋውን መሥዋዕት፤ የሚታየውን ሥርዓተ አምልኮት መንቀፍና አፍራሽ የሆነ ጥያቄ ማቅረብን ነበር። «እናንተ ዝም ብትሉ እነዚህ ድንጋዮች ይጮኹሉ ያመስግናሉ» የሚል መልስ ነበር የተሰጠው።



www.ethiopianorthodox.org

ዛሬም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አምልኮቱ ሳይጓደል፣ እምነቱ ሥርዓቱ ሳይፋለስ፣ ባህሉ ትውፊቱ ሳይካለስ፣ የነበረውና ያለው ተጠብቆ ሲፈጸም የሚታየው ያው የነበረው፣ ያለውና የሚኖረው ነው። ክርስቶስ ትናንት የነበረው ዛሬ ያለውና ለዘለዓለም የሚኖረው ቀዳማዊና ደኅራዊ አምላክ ነው። ቤተ መቅደሱ በረድኤት እድሮ ሲመሰገንበት የሚኖረው ቤቱ ነው። በሱ ፈቃድና ትእዛዝ እንጂ በሰው ፈቃድና ሥልጣን የተሠራ አይደለም። ሰው በፈለገው ጊዜ ሊያንጸው፣ ባልፈለገ ጊዜ ሊያፈርሰው የሚችልም አይደለም።

እንደ ሕጉ እንደትምህርቱ ከ፵ ከ፹ ቀን አንስቶ በመንፈቅ እና በዓመት ዕድሜ ከሚቆጠሩ ሕፃናት ከሰባ ሰማንያ ዓመታት በላይ የሚታዩ አረጋውያን ሁሉ በአንድነት ተሰብስበው «ሆሣዕና በአርያም፣ ቡሩክ ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ሥምረቱ ለሰብእ» እያሉ በማኅሌት፣ በይባቤ፣ በዝማሬ፣ በቅዳሴ ሲያመሰግኑበት ይኖራሉ «ሌባ ላመሉ ዳቦ ይልሳል» እንዲሉ ብእውነት መንገድ ተጉዘው መዝለቅ የማይሳካላቸው መናፍቃንና ቢጽ ሐሳውያን «ሕፃናትን ተው፣ ወደኔ ይምጡ አትከልክሉ» ያለውን የጌታ ቃል ባለማስተዋል፣ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ጠንቅቀው ባለመማርና ባለማወቅ የመሰላቸውን አግድመው የሚናገሩ ወገኖች ሕፃናት በሕፃንንታቸው ሀብተ ወልድና ስመክርስትና አግኝተው፣ የክርስ ቶስን ቤተሰብነት በጥምቀት በር ገብተው፣ ከሚያመሰግኑት ጋር እያመሰገኑ በሥጋው በደሙ ምግብነት በመንፈስ ቅዱስ ሞግዚትነት እንዳያድጉ፣ ልጆችን ከወላጆች ከክርስቶስ ቤተሰብነት ነጥለው፣ ለሞት፣ ለኃጢአት አመቻችተው ለመስጠት የሚጥሩ የእንክርዳድ ገበሬዎች ብዙ ናቸው። ከነዚህ መጠንቀቅ፣ መጠበቅ፣ ተንኮላቸውን ማወቅ፣ ከነሱ መለየት መራቅ ያስፈልጋል።

ከሥሩ ከመሠረቱ፣ ከማለዳው ከጠዋቱ፣ ከእሸቱ ከጡቱ የመልካም ቤተሰብ አስተዳደግ ያልጎበኛቸው በሕግ በሥርዓት መኖርን ያለመዱ፣ ሲቆነጠጡ ሳይሆን ሲቆጡአቸው የሚያለቅሱ፣ በምክርና በተግሣጽ ሳይሆን በወተትና በፍትፍት አካላዊ ጤንነታቸውና አፍአዊ ንጽሕናቸው ተጠብቆላቸው በሠፈው ተለቀው ያደጉ ሰዎች ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን መሸከም ያስቸግራቸዋል፣ ይከብዳቸዋል። ህልውናቸው ሜዳ ሙሉ ስለሆነ ጀርባቸውን ለሥርዓት ቀንበር አያስነኩም፤ ይዘላሉ፣ የለመዱት «ዛሬ እንብላ እንጠጣ ነገ እንሞታለን» የሚሉ ብዙ ሰዎች በሚሄዱበት ሠፊ ጎዳና እያወኩ መጓዝ ስለሆነ በወንጌል የተገለጠውን ቀጭኑን መንገድ ጠባቡን በር አይወዱትም። ጾሙ፣ ጸሎቱ፤ ቁመቱ፤ ስግደቱ ይከብዳቸዋል፤ ከዚህ ለማምለጥ «በጸጋው ድነናል» የሚል ባዶ መፈክር ወደ ተለጠፈበት የግብዞች ሠፈር ይዳበላሉ። በዚህም ምክንያት ሕገ ትሩፋት ወንጌል ሲማሩአት ቁልቁለት፣ ሲፈጽሙአት አቀበት፣ ሲሰሙአት ሜዳ፣ በተግባር ሲገልጹአት ዳገት ለምትሆንባቸው ሰዎች የሥረገላ ቀንበር ባልለመደችው ግልገል እንስሳ (በውርንጭላ) ተመስላ ተነገረች። ሕገ ትሩፋት ወንጌል ምን ጊዜም «በጸጋው» ድነናል በማለት ከሥነ ምግባር መሥመር እየወጡ ለሚመጻደቁ ወገኖች የማትለመድ ሕግ ሆና ትኖራለች።

ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ኢየሩሳሌም ከተማና በከተማዋ፣ ወደነበረች ቤተ መቅደስ በተጠጋ ጊዜ ከተማውም ቤተ መቅደሱም ሰማያዊውን ንጉሥ ለመቀበልና ለማስተናገድ የተሰማሙና የተመቻቹ አልነበሩም። ከከተማዋ ነዋሪዎችና ከቤተ መቅደሱ አገልጋዮች ብዙዎቹ በተፈ ጸመው ገቢረ ተአምራትና በተመለከቱት የሕፃናት ምስጋና መንፈስ ቅንዓት አድሮ ባቸው ይህ ለምን ይሆናል? ደቀ መዛሙ ርትህን ገሥጻቸው ሲሉ ራሳቸውን የሚገሥ ጹበት ጎሊና፣ ነውራቸውን የሚመለከቱበት ዓይን፣ ሥራቸውን የሚመረምሩበት ልቡና አልነበራቸውም። በሁላችንም ጉልቶ የሚታየው በኛ ዓይን ፊት ያለውን ጋሬጣ ሳናስተውል በሌላው ዓይን ያለውን ጉድፍ እናውጣ የማለት ጠባይ ነው።

ያን ጊዜ በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ የተፈጸመው ዓይነቱ ጥፋት እንዳይፈጸምና ቅጣቱ እንዳይከተል እንዲያውም ከአፀደ ቤተ ክርስቲያን ወጥቶ ለከተማውና ለገጠሩ ነዋሪ ሕዝብ የሚተርፍ መቅሠፍት ከቤተ መቅደስ እንዳይጀመር በቤተ መቅደስ የምናገለግል በአፀደ ቤተ ክርስቲያን ተሰብስበን የምንገኝ ሁሉ ይህን ተግሣጽና ትምህርት አዘውትረን ልንጠነቀቅበት፣ ልንማርበትና ልንመከርበት፣ ልናስተውለውና ልንመራበት ይገባል (ሕዝ.፱፥፮)።

በቤተ እግዚአብሔር የማይገባ ሥራ በመሥራት ሌሎች የሚነቅፉብን ሥራ እንዳይኖር በኛም ምክንያት የእግዚአብሔር ስም እንዳይነቀፍ ረድኤቱና ክብሩ መንፈሳዊ ሀብቱና በረከቱ ከምሥዋው ከመንበሩ፣ ከአፀደ ቤተ ክርስቲያን እንዳይነሳ (እንዳይለይ) ሥራችንን ልንመረምር ልናስተውልና በጥንቃቄ ልንመላለስ ያስፈልጋል። ቁጣውን የሚያመጣብን ክፉው ሥራችን፣ ከመዓቱና ከቅጣቱ የሚያድነን መልካሙ ሥራችን እስከሆነ ድረስ አምልኮታችንን በምንገልጽበት፣ ጸሎታችንን፣ መዓዛ ዕጣናችን በምናሳርግበት፣ መሥዋዕት በምናቀርብበት ቤተ መቅደስ ብቻ ሳይሆን የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ሰውነታችን የኃጢአት ሸቀጥ መደርደሪያ እንዳይሆን መጠበቅ ነው። በሻጮችና ለዋጮች፣ በሌቦችና ቀማኞች ገበያ የታየው ዓይነት የነውር ሥራ በሰውነታችን እንዳይኖር ሕይወታችንን ለመልካም ሥራ ልናሠለጥነው ይገባል።

ጌታ ወደ ከተማ ወደ ቤተ መቅደስም ገብቶ ነበር፤ ሁለቱም ቦታዎች አልተመ ቻቹለትም፣ ከአመጽ ከበደል ነጽተው ደስ ብሎት፣ ደስ ተሰኝቶ ገብቶ የሚያድርባቸው ሆነው ባለመገኘታቸው ትቶአቸው ከከተማው ወጥቶ ሁከትና ጫጫታ፣ አታሞና እንቢልታ፣ በማይሰማበት ሰላምና ፀጥታ በሠፈነበት፣ ንጹሕ አየር በሚነፍስበት ቦታ በቢታንያ አደረ።

ረድኤተ እግዚአብሔር ሰላምና በረከት ከቤታችን፣ ከከተማችን ይልቁንም ከአፀደ ቤተ ክርስቲያናችን ከመቅደሳችን እንዳይለይ ሥራችንን እንመርምር፣ ሰውነታችንን እናንፃ የሰላማችንን ቀን እናስተውል። ✣





**መ**ጋቢ ምሥጢር ያሬድ ካሣ ቤተክርስቲያናችን ካፈራቻቸው ታላላቅ ሊቃውንት አንዱና በመጀመርያው ረድፍ የሚሰለፉ አባት ናቸው። በመሆኑም በብዙዎች ምሑራን ዘንድ «ዳግማዊ አራት ዓይና ጐሹ» እየተባሉ ነው የሚጠሩት። መጋቢ ምሥጢር ያሬድ ዓይነሥውር ቢሆኑም አዕምሮአቸው ከማንም ዓይናማ የተሻለ የእውቀት ብርሃን ምንጭ ነው ማለት ይቻላል። እኚህ የዜማ፣ የድጓ፣ የአቋቋም ባለሞያ የቅኔና የሐዲሳት መምህር በአሁኑ ወቅት በትግራይ ሀገረ ስብከት መቀሌ ከተማ በመምህርነት በማገልገል ላይ ናቸው። መምህር ያሬድ እንደበተ ርቱዕ ልዩ የግጥም ችሎታና የታሪክ ዕውቀት ባለቤትም ናቸው።

# የተሰቀለው ተነሥቶአል

ስለ ኃጢአታችን በሥጋው
በእንጨት ላይ ተሰቀለ
፩ጴጥ.፪፥፳፬

**በ**ቤተክርስትያናችን የዘመን አቈጣጠር ቀመር መሠረት ጾመ ነነዌን መነሻ አድርገው በተውሳክ ከሚ ወጡ፣ ማለት ከዚህ በላይ አይወጡም ከዚህ በታች አይወርዱም በሚለው ቀመራቸው መመላለሻቸው ፴፭ ፴፭ ቀን፣ እንዲሆን ከተወሰነላቸው የሐዲስ ኪዳን አፅዋማትና በዓላት አንዱ ስቅለት እንደሆነ ይታወቃል። ስለዚህ ከመጋቢት ፳፬ እስከ ሚያዝያ ፳፰ ባሉት ፴፭ ዕለታት ወይም ፭ቱ ሳምንታት ከሚውሉ ዕለታተ ዓርብ መካከል አንዱን ዓርብ ዓርብ ስቅለት ብለን በጾም፣ በጸሎት፣ በሐዘን፣ በስግደት፣ መጻሕፍትን በማንበብ ቃለ እግዚአብሔር በመስማት የምና ከብረው በዓል ጌታችን አምላካችን አዳኛችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህ ነው ተብሎ ሊነገር የማይቻል ስፍር፣ ቊጥር፣ ልክ፣ መጠን የሌለው ጸዋ ትወ መከራ ተቀብሎ አዳም ከነልጆቹ ከወደቀበት የኃጢአት አዘቅት፣ ከገባበት ባሕረ እሳት ለማውጣት፣ ሕይወቱን አሳልፎ በመስቀል ተሰቅሎ መሞቱን አምነን፣ ያደረገውን ቸርነት እየመሰከርን፣ ለመስቀሉ፣ ለስቅለቱ ያለንን ሃይማኖታዊ ፍቅር የምንገ ልፅበት፣ ክብር ምስጋና የምናቀ ርብበት ዕለት ነው።

ስቅለት ማለት ቃል በቃል ሲተረ ጎም መስቀል ማንጠልጠል (መሰቀል መንጠልጠል) ማለትን ሲያሰማ የመስ ቀል ትርጓሜ ደግሞ መስቀያ ማንጠ ልጠያ! የሚሰቀለው የሚንጠለ ጠለው! አካል የሚሰቀልበት የሚንጠ ለጠልበት ዕንጨት ብረት የመሰለው ሁሉ ሊሆን ይችላል። እንግዲህ መስቀል መሳሪያው ማድረጊያው ስቅለት ድርጊቱ አድራጎቱ ነው።

እንዲህ ሲባል የመስቀል ትርጓሜ በዚህ ብቻ የሚያበቃ አይደለም። ክርስቶስ ሰው ሆኖ ሥጋ ለብሶ ነገረ ትስብእቱን፣ ምሥጢረ ድኅነቱን፣ ለማረጋገጥ የፈፀማቸው ሥራዎች በሙሉ ሰው በመሆኑ፣ ሥጋ በመልበሱ የደረሰበት ሰብአዊ ፈተና ያሳየው ፍፁም ትሕትና መስቀል እንደሚባል መገንዘብ ያሻል። ይሁንና ከክርስቶስ በፊት መስቀል (ስቅለት) ሽፍቶች፣ ወንበዴዎች፣ ጨካኞች፣ ነብሰገዳዮች በጠቅላላው ከባድ ከባድ ወንጀል የፈጸሙ ዓመፀኞች በሞት የሚቀጡበት እጅግ አስደንጋጭና አስፈሪ አሰቃቂና አሳፋሪ ነገር ነበር።

ሌላው ሞት ማለት በድንጋይ ተደብድቦ፣ በእሳት ተለብልቦ፣ በሰይፍ ተከልሎ፣ ወደ አንበሶች ጉድጓድ ተጥሎ የሚሞቱት ሞት የሚያዝናና የሚያስደስት ሆኖ አይደለም። ከዚያ በባሰ አስፈሪነቱን አሰቃቂነቱን ለመግለፅ ያህል እንጂ። አስፈሪነቱንና አሰቃቂነቱን በበለጠ ከባድ ሊያደርገው የቻለው ደግሞ በዕንጨት ተሰቅሎ የሚሞት ሁሉ ርጉም ነው የሚል በመጽሐፍ የተጻፈ የማያልፍ ዘለዓለማዊ መርገም ስለነበረው ነው። (ዘዳግም ም.፳፩ ቁ.፳፫ ገላትያ ም. ፫ ቁ.፲፫።) አዎን ክርስቶስ እንደ ሌባ ሲሰርቅ ተይዞ፣ እንደ ወንበዴ ሲቀማ ተገኝቶ፣ እንደ ጻድቃን እንደ ሰማዕታት ክብር ሽቶ አልተሰቀለም። ታዲያ ለምን ተሰቀለ ቢባል:-

ሀ. «ተለቈ ምስለገበርተ ዓመፃ» ከወ ንበዴዎች ጋራ ተቈጠረ የሚለ ውን ቃለ መጽሐፍ ለመፈጸም።

ለ. መርገሙን ወደ በረከት ለመለወጥ።

ሐ. እኛን ከመርገም ለማዳን በዚህ አስፈሪ አሰቃቂ በሆነው መርገም በተመላበት ዕፀ መስቀል ተሰቅሎ ሊሞት መረጠ፣ ሐዋርያት፣ ሰማዕታት ሌሎቹም ብዙ የእግዚአብሔር አማኞች ምንም ኃጢአት ሳይሠሩ ሀልዎተ እግዚ አብሔርን እያስተማሩ፣ የክርስ ቶስ ፍጹም አምላክነቱን ዘለዓለ ማዊ ደኅንነቱን እየመሰከሩ፣ በመ ስቀል ተሰቅለው በገመድ ተንጠ ልጥለው ሙተዋል። ክርስቶስ በመስቀል ተሰቅሎ፣ ሙቶ፣ ያን



www.ethiopianorthodox.org

መርገም ባያጠፋው ኖሮ እነዚህ የእግዚአብሔር አማኞች ሐዋርያት፣ ሰማዕታት፣ ምንም እንኳን ባይሰርቁ፣ ባይቀሙ፣ ኃጢአት ባይሠሩ እንኳ በዕንጨት ተሰቅለው በመሞታቸው ብቻ ርጉማን ከመባል ባልዳኑም ነበር፤ ከመርገሙም ነፃ ባልሆኑ ነበር። ምክንያቱም መጽሐፍ እገሌ እገሌ ሳይል አንዱን ካንዱ ሳየለይ በዕንጨት ተሰቅሎ የሚሞት ሁሉ ርጉም ነው ብሎዋልና።

ስለዚህ ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በዕንጨት ተሰቅሎ የሚሞት ሁሉ ርጉም ነው የሚል ተጽፏል ካለ በኋላ «ወለነሰ ክርስቶስ ተሳየጠነ እመርገማ ለኦሪት በዘወድአ ወፆረ በእንቲአነ መርገማ» ስለኛ መርገምዋን ፈፅሞ ታግሶ በተቀበለ ገንዘብ እኛን ግን ክርስቶስ ከኦሪት መርገም በወርቀ ደሙ ዋጅቶናል፤ ነፃ አውጥቶናል ሲል የተናገረው። ስለሆነም ዕዳ መርገም የሌለበት ንጹሐ ባሕርይ ኢየሱስ ክርስቶስ በዕንጨት ተሰቅሎ የሚሞት ሁሉ ርጉም ነው የሚለውን መርገም ሳይፈራ ግንድ ተሸክሞ፣ ጨርቅ አገልድሞ፣ መታየትን ሳይሰቀቅ ልብስን ጥሎ እራቁቱን መሆኑን ሳያፍር፣ ሐፍረትን ንቆ፣ በመስቀሉ መርገሙን ሻረው፣ አጠፋው ፍርሐቱን አራቀው፤ አስወገደው። ስለዚህ ተከታዮቹ ሐዋርያት ሰማዕታት በስሙ እየተጠሩ፣ እሱን እያስተማሩ፣ ስለ እኛ መከራ መቀበሉን፣ መሰቀሉም፣ መሞቱን እየመሰከሩ በመስቀል ተሰቅለው ቢሞቱ ደስ ይላቸው ነበር።

ይኸውም የሞቱ ተሳታፊዎች ለመሆን ያበቃናል የሚል እምነት ስለያዙ ነው። እንዲያውም ከሐዋርያትም ሆነ ከሰማዕታት አንዳንዶቹ በሚሰቀሉበት ወቅት እንደ ጌታችን ክርስቶስ ወደ ላይ አቅንታችሁ አትስቀሉን፤ ወደ ቁልቁል አድርጋችሁ (አዘቅዝቃችሁ) ስቀሉን። እያሉ ቁልቁል እንዲሰቅሉዋቸው ሰቃዮቻቸውን ይለምኑ፤ ይማልዱ፤ እንደ ነበር በቤተክርስትያን ታሪክ በሰፊው ተጽፎአል። እንግዲህ ከክርስቶስ ወዲህ መስቀል የስጋት፣ የኃዘን፣ የጥላቻ፣ የመርገም፣ ምልክት መሆኑ ቀርቶ የደስታ፣ የሰላም፣ የፍቅር፣ የበረከት፣ የነፃነት፣ የሕይወት ምልክት ሆኖአል። ቀድሞ ሰዎች የመስቀል ነገር ሲነሳ ይፈሩ ይደነግጡ ይርዱ ይንቀጠቀጡ ነበር፤ ዛሬ ግን እኛ ክርስትያኖች የመስቀል ነገር በተነሳ ጊዜ ልባችን በመንፈሳዊ ደስታ ይሞላል፤ ስሜታችን በክርስቶስ ፍቅር ይቀሰቀሳል፣ ሕይወታችን በፍጹም እምነት ይታደሳል። ከክርስቶስ በፊት ሰዎች መስቀል ሲያዩ ይሸሹ ይበረግጉ ነበር፤ ዛሬ ግን «ለመስቀልከ ንሰግድ ኦሊቅነ ወለትንሣኤከ ቅድስት ንሴብሀ ኵልነ ይእዜኒ ወዘልፈኒ» መምህራችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ለመስቀልህ እንሰግዳለን፣ ክብርት ልዩ ለምትሆን ትንሣኤህም ሁላችን ምስጋና እናቀርባለን፣ እንዘምራለን፣ እያልን ለመስቀሉ የምንሰግድበት የምንዘምርበት ይልቁንም የመስቀሉን በረከት ለማግኘት መስቀሉን ለመሳም (ለመሳለም) የምንጓጓበት እርስ በርሳችን የምንጋፋበት ጊዜ ነው።

በአንፃሩ ጠላቶቻችን አጋንንት በመስቀል ድል ተነስተዋልና ኃይላቸው ደክሞአልና፣ ገዥነታቸው ቀርቶአልና፣ ፈፅመው ተቀጥተዋልና መስቀሉን ሲያዩ ይሸሻሉ፤ ይበረግጋሉ፤ ይባረራሉ፤ ከመስቀሉ በፊት መቆም አይቻላቸውም። ሐዋርያው ጳውሎስ ለቈላስይስ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ «ከባለ ጋራችን ከዲያብሎስ የዕዳችንን መጽሐፍ ደመሰሰው፣ ከመካከላችንም አስወገደው። በመስቀሉም ቀጣው፣ ቸነከረው፣ እራቁቱን ሆኖ በመሰቀሉ ሊቃነ አጋንንትን ሠራዊተ አጋንንትን አሳፈራቸው» ሲል ፈፅሞ እንደደመሰሳቸው፣ እንደቀጣቸው ተናግሮአል። በዚህ መሠረት ስቅለቱ ለጠላቶቻችን ጥፋት ለኛ ድኅነት ለጠላቶቻችን ስደት፣ ሞት፣ ለኛ ሕይወት፣ ነፃነት ነው።

ምንም እንኳ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወቱን አሳልፎ የሰጠበት የሞተበት ቢሆንም እኛ ግን ድነንበታልና እናከብረዋለን፤ ከመስቀሉ ጥላ ላይ ሁነን ሃይማኖታችንን እንመሰክርበታለን «ገብረ ሰላመ በመስቀሉ» በመስቀሉ ሰላምን አደረገ እያልን ሰላምን እንሰብክበታለን፤ የምስራች እንናገርበታለን፤ ቀደም ሲል «ስቅልተ ትሬእያ እስራኤል ለሕይወትከ ወኢ.ትት አመና» እስራኤል ሆይ ሕይወትህን ተሰቅላ ተንጠልጥላ ታያታለህ ነገር ግን አታምንባትም ትብሎ ትንቢት ተነግሮ ነበር ዘጸ.፳፰፥፷፮። ይህም እስራኤል ሕይወታቸው ክርስቶስን በቀራንዮ አደባባይ ተሰቅሎ እያዩት እንዳላመኑበት እንዳልተጠቀሙበት የሚገልፅ ረቂቅ ጥልቅ ምሥጢር ነው። ከዚህም አልፎ ሕይወታቸውን ክርስቶስን ራሳቸው እንደሚሰቅሉት በሕይወታቸው በክርስቶስ እንደሚያፌዙ የሚያረጋግጥ ነበር። ይኸው ትንቢት ተፈፅሞ ክርስቶስ በግልፅ ተሰቀለ፤ እስራኤል (አይሁድ) ሕይወታቸውን ተሰቅሎ አዩት፤ አፌዙበት፤ ሌላውን የሚያድን ራሱን ግን ማዳን አይቻለውም፤ ከመስቀሉ ይውረድና አይተን እንመንበት እያሉ አሽሟጠጡት፤ እሱ ግን «አባቴ ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁትምና ይቅር በላቸው ኃጢአታቸውን አስተሥርይላቸው» እያለ ጸለየላቸው።

በመሠረቱ ክርስቶስ የጠፋውን ሊፈልግ የተጎዳውን ሊያድን መጣ እንጂ ለበቀል ለጥፋት አልመጣምና ጠላቶቹን እንኳ ሊበቀላቸው አልፈለገም። ለሰደቡት ላሽሟጠጡት ለገፉት ለገረፉት፣ ለቸነከሩት ለሰቀሉት መስቀል ላይ ሆኖ መጸለዩ ማንም ይሁን ማን ሊጠፋ የማይፈልግ ይቅር ባይ አምላክ መሆኑን አረጋገጠ። ጠላቶቻችሁን ውደዱ ለጠላቶቻችሁ ጸልዩላቸው ብሎ ያስተማረውን ትምህርት ብሩህ ለማድረግ ጠላትን መውደድ፣ ለጠላት መጸለይ፣ ማለት እንዴት እንደሆነ በተግባር አሳየ። ጥንቱስ ቢሆን ክርስቶስ የተሰቀለው፣ የሞተው፣ ለጠላቶቹ አይደለምን? ሰው ከልብ ለሚያምነው ወዳጁ ወገኑ ለሚለው ወንድሙ የአቅሙን ያህል ለመርዳት ይሞክር ይሆናል። ገፋም ቢል የመከራው የችግሩ ተሳታፊ ለመሆን ያለውን ፈቃድ ይገልጻል። ይህንን የሚፈፅመው መላው የሰው ልጅ ሳይሆን አልፎ አልፎ የሚገኙ አንዳንድ ቅን አስተሳሰብ ያላቸው ደጋግ ሰዎች መሆናቸውን ሳንረሳ ነው።

ስለ ወዳጁ ጨክኖ የሚሞት ሰው ይገኝ እንደሆን ምናልባት ከማለት በቀር በርግጠኝነት መናገር አይቻልም። ስለ ጠላቱ ግን ደፍሮ የሚሞት ሰው ማግኘቱ ይቅርና ቅንጣት ታህል ትንሽ መልካም ሐሳብ ለጠላቱ የሚያስብ ሰው ማግኘቱ ፈፅሞ የሚታሰብ አይደለም። ክርስቶስ ግን ስለ ጠላቶቹ ተሰቅሎ ሞተ። እግዚአብሔር በባሕርይ ልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት ይቅር ብሎ ጠላቶቹን ታረቃቸው። ስለዚህ ነገር ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ይላል «እኛ ኃጢአተኞች ጠላቶቹ ስንሆን ስለ ኃጢአታችን ይሞት ዘንድ ክርስቶስ በጊዜው (በቀጠሮው) መጣ። እኛ ኃጢአተኞች ስንሆን እነሆ እግዚአብሔር እንደ ወደደን መጠን እዩ፤ ክርስቶስ ስለኛ ሞተ።

እኛ የእግዚአብሔር ጠላቶቹ ስንሆን በልጁ ሞት ይቅር ካለን፣ (ከታረቀን) በልጁ ሕይወት በትንሣኤውማ እንደምን ያከብረን ይሆን? እንደምን ይቅር ይለን ይሆን?» ይላል (ሮሜ ፭፥፰–፲፩) ዳሩ ግን የሰው ልጅ የሚወደው የሚያድነው እግዚአብሔርን ጠልቶ የሚጠላው፣ የሚያጠፋው፣ ሰይጣንን ወደደ። እንዲህ ማለት ለሕይወቱ ለክብሩ ምክንያት የሚሆነውን ቃለ እግዚአብሔር አልሰማም ብሎ የሚጠቀምበትን ትእዛዝ አፈረሰ፤ ለሞቱ ለጥፋቱ ምክንያት የሚሆነውን የሰይጣን ቃል ተቀብሎ የሚጎዳበትን ትእዛዝ ፈጸመ። እግዚአብሔር ግን ከጠላኝ ብሎ ሰውን አልተወውም፤ እስከ መጨረሻው ወደደው፤ በፍጹም ፍቅሩ ተከተለው። ጠፍቶት እንዳይቀር እየፈለገው ወደዚህ ዓለም መጣ። ባገኘውም ጊዜ በተራ ነገር ሳይሆን በመስቀል እስከ መሞት ደርሶ እጅግ ጥልቅ የሆነ ፍጹም ፍቅሩን ገለጸለት። በደሙ ዋጀው፣ በሚገባ ዳኝነት በእውነተኛ ፍርድ ለመስቀሉ ካሣ አድርጎ በልጅነት ተቀበለው። ከወደቀበት የኃጢአት አዘቅት በሐብለ ፍቅሩ ስቦ፣ ጎትቶ፣ ወደ ጥንት ቦታው ወደ ገነት መለሰው። ከገባበት ባሕረ እሳት በመስቀሉ ትርከዛ እየቀዘፈ አሻግሮ ፍጹም ጸጥታ ወደ ሰፈነበት የሕይወት ወደብ አደረሰው። ሰው ወዳጅ እግዚአብሔር ወዶ የፈጠረውን ሰው አሁንም በማይመረመር ፍቅሩ ወዶ አዳነው።

«ሙሴ እርዌ ምድርን በምድረ በዳ እንደ ሰቀለው እንዲሁም ክርስቶስ ይሰቀል ዘንድ አለው። በሱ የሚያምን ሁሉ እንዳይጎዳ ለዘለዓለሙ ይድናል እንጂ። እግዚአብሔር ዓለሙን እንዲህ ወዶታልና ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው አንድ ልጁን የሁሉ ቤዛ አድርጎ ለሞት አሳልፎ እስኪሰጥ ድረስ።» (ዮሐ.፫፥፲፬–፲፯)

«እሱ ወደደን እንጂ እኛ የወደድነው አይደለም። ኃጢአታችንን ያስተሰርይልን ዘንድ ልጁን ወደዚህ ዓለም ሰደደው» (፩ዮሐ.፬፥፲–፲፪) «እንግዲህ ስለዚህ ምን እንላለን? እግዚአብሔር ከኛ ጋራ ካለ ማን ይቃወመናል? ለልጁስ ስንኳን አላዘነለትም ስለሁላችን ለሕመም፣ ለሞት አሳልፎ ሰጠው እንጂ። እንዲህ ከሆነ ሁሉ የማይሰጠን ምንድነው» (ሮሜ. ምዕ.፰፥፴፩–፴፫)።

እንግዲህ መጻሕፍት በሙሉ እግዚአብሔር በኛ ላይ ያለው ፍቅሩ ምን ያህል ፍጹም እንደሆነ ባንድነት ተስማምተው ተባብረው ነግረውናል።

እንግዲያውስ በዓለ ስቅለቱን በምናከብርበት ጊዜ ፍጹም ፍቅሩን እናስታውስ፤ ያደረገልንን ታላቅ ቸርነት እናስብ፤ እግዚአብሔርን ከመውደድ ጋራ ወንድሞቻችንን እንውደድ፤ የኛ የክርስቲያኖች መለዮአችን፣ መታወቂያችን፣ ፍቅር በመሆኑ እርስ በርሳችን እንፋቀር። «እርስ በርሳችሁ የተፋቀራችሁ እንደሆነ የኔ ደቀ መዛሙርት መሆናችሁን ሰው ሁሉ ያውቃችኋል» ብሏልና። (ዮሐ. ፲፫፥፴፭) እርስ በርሳችን ካልተፋቀርን ግን መለዮአችንን ስለጣልን መታወቂያችንን ስለ ረሳን የማን ወገኖች መሆናችን በምን ይታወቃል? ማንነታችንን አጠያያቂ ያደርገዋል። ስለዚህ ይህን እርስ በርሳችን የመፋቀሩን ጉዳይ አጥብቀን ልናስብበት ይገባል። ያለ እሱ እውነተኛ ክርስትያን ነኝ የክርስቶስ ወገን ነኝ ማለት ስለማይቻል ነው።

## የትንሣኤው ምሥጢር

መልአኩም ሴቶችን አላቸው «እናንተስ አትፍሩ የተሰቀለውን ኢየሱስን እንድትሹ አውቃለሁና ተነሥቶአል ከዚህም የለም» (ማቴ.፳፰፥፭)

ስቅለትንና ትንሣኤን ለያይቶ ነጣጥሎ ማየት አይቻልም። ስቅለት ያለ ትንሣኤ ትንሣኤ ያለ ስቅለት አይሆንም። ስቅለት ሲነሣ ትንሣኤ፣ ትንሣኤ ሲነሣ ስቅለት መነሳቱ የማይቀር ነው። የሁለቱም ታሪክ የተፈጸመው በአንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሆኖ የተፈጸመበትን ወቅት አንድ ጊዜ በመሆኑ ነው። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምንም ኃጢአት የማይሠራ ከኃጢአት ሁሉ የራቀ ንጹሐ ባሕርይ አምላክ ቢሆንም በአዳም ሐጢአት በአይሁድ ግፊት እንደ ኃጢአተኛ ታይቶ እንደ ከባድ ወንጀለኛ ተቈጥሮ በተድበሰበሰ በጲላጦስ ፍርድ መሰቀሉ ይታወቃል። በፍርድ የተሰቀለ አንድ ወንጀለኛን ከመስቀሉ አውርዶ ለመቅበር ቅጣቱን የፈረደውን ባለሥልጣን ማስፈቀድ ግዴታ ነበር።

በዚህ መሠረት ዮሴፍና ኒቆዲሞስ ከመስቀሉ አውርደው ለመቅበር እንዲፈቅድላቸው ጲላጦስን ለመኑና ፈቀደላቸው። ከመስቀሉ አውርደው ብርሃንን እንደ ልብስ የሚጎናጸፈው እሱን በልብሰ ገርዜን ገነዙት። ሰማይንና ምድርን፣ በውስጣቸው ያሉትን ፍጥረታት በሙሉ በመኽል እጁ የያዘ ጌታን እንደ ማንም ሰው ተሸክመው ወደ መቃብር ወሰዱት። ምድርን የፈጠረ በምድር ውስጥ ተቀበረ። በሦስተኛው ቀን መግነዙን ፍቱልኝ፣ ድንጋዩን አንሱልኝ፣ መቃብሩን ክፈቱልኝ ሳይል በገዛ ሥልጣኑ በመለኮታዊ ኃይሉ ከሙታን ተለይቶ ተነሣ። ሞት ሊይዘው ሊገታው አይችልምና ሥልጣኑን በሞት ላይ አሳየ። ሞትና መቃብር በሱ ላይ ምንም ሥልጣን ስለሌላቸው የተለመደው ሥራቸውን መሥራት አልቻሉም። በሞቱ ሞትን እንዳሸነፈው በትንሣኤውም መቃብርን አሸነፈው። «በምድር ላይ ኃጢአትን አሳፈረ። በመስቀል ላይ መርገምን ሻረ። በሲኦል ሞትን አጠፋ። በመቃብር፥ ሙስና መቃብርን፣ ማለት በመቃብር ፈርሶ በስብሶ መቅረትን ደመሰሰ ተብሎአልና።» (አትናቴዎስ፣ ቢንያሚ በሃይማኖተ



www.ethiopianorthodox.org

አበው) የትንሣኤው ምሥጢር በመጀመሪያ ለመላእክት ተገለፀላቸው። ቀጥሎ ለሴቶች ታያቸው። ከዚያም ለሐዋርያት ተበሰረላቸው። ከሐዋርያትም ለሕዝቡ፣ ለአሕዛቡ ለዓለም ሁሉ ተሰበከላቸው።

መቸስ የትንሣኤው ምሥጢር ክርስቶስ በማያዳግም ሁኔታ በማያጠራጥር መንገድ ማንነቱን ያሳወቀበት፣ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ያስመሰከረበት፣ ፍጹም አምላክነቱን ያረጋገጠበት፣ የመጨረሻ ኃይል ነው። «እፎ ኢይከውኖ ወልዶ ዘበአማን እንዘ ይከውኖ ሰማዕተ ትንሣኤ ሙታን» ከሙታን ተለይቶ መነሳቱ እማኝ ምስክር ሲሆነው፣ ክርስቶስ በእውነት የአብ የባሕርይ ልጁ እንደምን አይባል»? ይላል ቄርሎስ በሃይማኖተ አበው። በዚህ ታላቅ መለኮታዊ ኃይል የተከናወነውን የትንሣኤውን ምሥጢር ሰውሮ ለማስቀረት አይሁድ እንደ ልማዳቸው መድከማቸው፣ ተንኮል መሥራታቸው አልቀረም። ተንኮላቸውንም ለማስፈጸም ከጲላጦስ ዘንድ ሄደው ያ በሕይወተ ሥጋ ሳለ በሦስተኛው ቀን እነሣለሁ ሲል ሰምተናል። አሁንም ደቀ መዛሙርቱ ሌሊት መጥተው ሥጋውን ሰርቀው ወስደው ተነሣ እያሉ ለሕዝቡ እንዳያስተምሩ መቃብሩን አፅንተው የሚጠብቁ ወታደሮችን እዘዝ አሉት። ከቀደመች ክፋቱ የኋላ ክፋቱ የፀናች ትሆናለች አሉት። ጲላጦስም እንደምታውቁት አድርጋችሁ አስጠብቁ አላቸው። እነሱም መቃብሩን አፅንተው የሚጠብቁ አራት አዛገሮች (አለቆች) ያሉአቸው ወታደሮችን አዘጋጁ። አፅንተውም እንዲጠብቁ ጥብቅ ትእዛዝ አዘዙዋቸው። መቃብሩንም ጠንካራ በሆነ ቍልፍ ቈለፉት።

ይሁንና እነዚህ መቃብሩን አፅንተው ይጠብቃሉ የተባሉት ወታደሮች የክርስቶስን ትንሣኤ ማስቀረት የማይችሉ፣ እንዳይነሣ ለመከልከል የማያስችል አንዳች ኃይል የሌላቸው ደካሞች ነበሩ። እሱን መጠበቅ ቀርቶ እራሳቸውን መጠበቅ አልቻሉም። የትንሣኤውንም ብርሃን ባዩ ጊዜ ከግርማው የተነሣ ተሸበሩ፣ ደንግጠውም ወደቁ። እንደ አይሁድ ከንቱ ሐሳብ በድን እንዳይሰረቅ ይጠብቃሉ ሲባሉ ራሳቸው በድን ሆኑ። ይገርማል ሕያወ ባሕርይ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን በሕይወተ ሥጋ ሳለ በሦስተኛው ቀን እነሳለሁ ብሎ እንደ ተናገረ ቃሉን አክብሮ በሦስተኛው ቀን ትንሣኤውን ገለጠ። ነቢዩ ዳዊት «አሕዛብ ለምን ዶለቱ?፣ «ሕዝቡ ለምን ከንቱ ነገር ተናገሩ»? የምድር ነገሥታት ለምን ተነሡ? አለቆቹ ካህናቱ በእግዚአብሔር እና በመሲሑ ላይ ተባብረው ለምን ተሰበሰቡ»፣ ብሎ የተናገረው ትንቢት ደረሰ ተፈጸመ። መዝ.፪፥፩–፫።

አሕዛብ የተባሉ ሮማውያኑ ወታደሮች ናቸው። ሕዝብ የተባሉት አይሁድ ናቸው። ነገሥታቱ ሄሮድስ፣ ጲላጦስ ናቸው። ካህናቱ እነ ሐና እነ ቀያፋ ናቸው። እነዚህ ሁሉ በእግዚአብሔር አብና በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ዶለቱ፣ አድማ መቱ፣ ከንቱ ነገር ተናገሩ፣ ክፉ ምክር መከሩ። ዳሩ ግን አድማቸው ዱለታቸውና ምክራቸው መና ሆኖ ቀረ። ፈርሶ፣ በስብሶ ይቀራል መስሎዋቸው ነበር፣ ተነሣባቸው። በትንሣኤው ጠላቶቹ ሁሉ አፈሩ ራሳቸውን ቀበሩ። በትንሣኤው ያመኑ ወገኖቹ ደቀ መዛሙርቱ ደግሞ ደስ ብሎዋቸው ተፅናኑ፣ ራሳቸውን አቀኑ፣ ትንሣኤውን ለማየት ስላበቃቸው ፈጣሪያቸውን አመሰገኑ፣ ክርስቶስ ከተነሣ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ሐዋርያት እሱ ነው አይደለም? እያሉ እንዳይጠራጠሩ፣ መንታ ሐሳብ ይዘው እንዳይቀሩ፣ ትንሣኤውን ለማስረዳት በተለያየ መንግድ ራሱን ገለጸላቸው።

ሀ. በዝግቤት ገብቶ ሰላም ለናንተ ይሁን በማለቱ፣

ለ. የተወጋ ጎኑን፣ የተቸነከረ እጁን፣ እግሩን፣ የተገረፈ ሰውነቱን፣ በማሳየቱ እንዲዳስሱት በማድረጉ።

ሐ. ያቀረቡለትን ምግብ በፊታቸው እያዩት በመብላቱ።

መ. አርባ ቀን ከነሱ ጋራ እየወጣ እየገባ በመቆየቱ። (ዮሐ.፳፥፲፱–፳፪፣ ሉቃ. ፳፬፥፴–፴፫፣ ዮሐ. ፳፩፥፲፩–፲፫)።

ከሞተ በኋላ በብዙ ተአምራት ሕያው እንደሆነ ራሱን የገለጸላቸው እሊህ ናቸው። የሐዋ.ሥራ ፩፥፫። ሐዋርያትም ትንሣኤውን ተረድተው አምላክነቱን አምነው የትንሣኤውን ኃይል ለመመስከር በቅተዋል። ዓርባ ቀን ከሱ ጋራ የበላን የጠጣን እኛ ነን። በይሁዳ፣ በሰማርያ፣ በገሊላ ባደረገው ተአምራት ሁሉ ምስክሮች ነን። የሐዋ.ሥራ ፲፥፴፱–፵፪። ቅድመ ዓለም የነበረ የእሱን ነገር እንነግራችኋለን በጆሮአችን የሰማነው እሱ ነው፣ በዓይናችንም ያየነው እርሱ ነው፣ ስለ ሕይወት ነገር ማለት ትንሣኤውን ለመረዳት እጆቻችንን የዳሰሱት የተረዳነው እሱ ነው፣ እያሉ መስክሮዋል። ፩ዮሐ.፩፥፩ በዚህ መንገድ ነው የትንሣኤው ነገር ከሐዋርያት ጀምሮ እስከ እኛ የደረሰው። ዛሬም እንደ ሐዋርያት ትንሣኤን ለመመስከር «ትንሣኤከ ለእለ አመነ ብርሃንከ ፈኑ ዲቤነ» ትንሣኤህን ለምናምን ብርሃንህን ላክልን (ግልፅልን) እያልን በዓለ ትንሣኤውን በደስታ በሃይማኖት እናከብራለን እንግዲህ የትንሣኤውን በዓል ስናከብር ትዝ ሊለን የሚገባው የራሳችን ትንሣኤ መኖሩ ነው። ክርስቶስ መነሣቱ ኃይሉን ለመግለፅ ብቻ ሳይሆን ለኛም ትንሣኤ በኵር ለመሆን ነው። ስለዚህ ትንሣኤያችን ትንሣኤ ዘለክብር እንዲሆን ካሁኑ መዘጋጀት ያስፈልገናል። በዓለ ትንሣኤው የሰላም የደስታ በዓል እንዲሆንልን እመኛለሁ አገራችንን እግዚአብሔር በተለመደው ቸርነቱ ይጠብቅልን። አሜን። ✣



# ሕገ እግዚአብሔር ይጠበቅ

ከአባ ገሪማ ሊቀ ጳጳስ
የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ልዩ ጽ/ቤትና የውጭ ግንኙነት የበላይ ኃላፊ



**ሕ**ግ፣ ዕውቀትና ዕውነት የሆነ አድርግ፣ አታድርግ፣ የሚል የተወሰነ ወሳኝ ሥርዓት ነው።

ከዚህም ጋር አታድርግ የሚለው ሕግ ሲሆን፣ አድርግ የሚለው ትእዛዝ መሆኑ ይታወቃል። (ዘጸ.፳፥ ፩–፲፯፣ ዘሌዋ.፲፱፥፲፰፣ ዘዳግ. ፮፥፭–፱፣ ማቴ.፭፥፳፩–፵፰)።

እግዚአብሔር ዓለሙንና ሕዝቡን የሚያስተዳድረውም በዚሁ በሠራው ሕግ ነው። ይህም እንደ ሰው ሠራሽ ሕግ ጊዜ እየታየ የሚለወጥ፣ የሚለዋወጥ አይደለም፣ ሰማይንና ምድርን አሳልፎ የሚኖር ነው እንጂ (ማቴ. ፳፬፥፴፭)።

ሕገ እግዚአብሔር የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ያለውን ሁሉ አጠቃሎ የያዘ ነው።

ዓለም ከተፈጠረ፣ ዘመን ከተቆጠረ ጀምሮ ሦስት ሕግጋት በቅደም ተከተል ተያይዘው የመጡ መሆናቸውን እናውቃለን። ይዞታቸውና አቋማቸውም በመጽሐፍ ቅዱስ ተጠቃሎና ተመዝግቦ ይገኛል።

እነዚህም ሦስት ሕግጋት የሚባሉት:-

፩ኛ. ሕገ አበው (ሕገ ልቡና)

፪ኛ. ሕገ ኦሪት

፫ኛ. ሕገ ወንጌል ናቸው።

በሕገ አበው፣ በሕገ ኦሪት፣ በሕገ ወንጌል በሦስቱም ሕግጋት እግዚአብሔር አምላክ አንድ ነው። በዚህ ምክንያት ስለ እግዚአብሔርነቱ በመጽሐፍ ቅዱስ የተነገረውን ሁሉ በልባችን የምናምንበት፣ በአፋችን የምንታመንበት መግለጫ፣ ሃይማኖት ይባላል። ሃይማኖት ማለት በዓይን የማይታየውን በእጅ የማይዳሰሰውን፣ የልዑል እግዚአብሔርን ሀልዎት ይህ እንዴት ይሆናል ማለት ሳይኖር በሙሉ ልብ አምኖ መቀበል ነው።

በዘመነ ሕገ አበው ጻድቁ ኖኅና ከጊዜ በኋላም ሎጥ በየጊዜያቸው ከደረሰው የተለያየ ጥፋት በእግዚአብሔር ቸርነት ከእነቤተሰባቸው ለመትረፍ የቻሉት እግዚአብሔርን አምነው ሕገ አበውን ጠብቀው በመኖራቸው መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል።

በሕገ ኦሪትም እግዚአብሔር በሲና ተራራ ከሙሴ ጋር የተነጋገረውን በፈጸመ ጊዜ በእግዚአብሔር ጣት የተጻፈባቸው ከድንጋይ የሆኑ ሁለቱን የምስክር ጽላት «እግዚአብሔር ለሙሴ ከሰጠው ዐሠርቱ ቃላተ ኦሪት መካከል አንዱ «አታመንዝር» የሚል መሆኑን ተረድተናል።

ከዚህም ጋር ለሕገ ወንጌል መሠረት የሆኑት ስድስቱ ቃላተ ወንጌል ከማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ ፭ ከቁጥር ፳፩–፵፰ ተመዝግበው እናገኛቸዋለን። ከእነዚህም መካከል ከቁጥር ፳፯–፴፪ የምናገኘው «አታመንዝር እንደ ተባለ ሰምታችኋል» የሚል ነው።

ይህም ሕገ እግዚአብሔር ባለመከበሩ በመላው ዓለም በሰው ሕይወት ላይ ጥፋት እየደረሰ ይታያል።

ሁላችንም ከሕግ በታች መሆናችንን ስለምናውቅ ሕግ በሰው ሕይወት ላይ ሥልጣን የሚኖረው ሰው በሕይወት እስከ አለ ድረስ ብቻ መሆኑን ደኅና አድርገን እንረዳለን።

ከታሪክ እንደምንረዳውና ከዕይታም እንደምንመለከተው በዓለማችን አስደንጋጭና አስፈሪ የሆኑ ብዙ ክስተቶች በየጊዜው ተፈጥረዋል፣ ይፈጠራሉም። በተፈጥሮ የሚከሰቱና ሰው ሠራሽ የሆኑ ብዙ መቅሰፍቶችም በምድር ዙሪያ ይታያሉ። ድርቅ፣ የመሬት መናወጥና የውሀ መጥለቅለቅ፣ ጦርነትና ረሀብ፣ በሽታና እልቂት፣ ስደትና ድህነት እነዚህንም የመሳሰሉ አደጋዎችና የጥፋት ወጥመዶች በሰው ዘር ተከታታይ ትውልድ ሕይወት ላይ የማይለካ ጉዳት አድርሰዋል፣ እያደረሱም ነው። የሰው ልጅ ከአቅሙ በላይ የሆኑ ብዙ ችግሮችንና ፈተናዎችን እየተቋቋመ ለዘመናት ተጕዟል። የየዘመኑ የጥፋት ክስተቶች የየራሳቸው የሆነ ስም ጠባይና ግብርም አላቸው።

ፈተና በብዙ መንገድ ሊመጣ ይችላል፣ ይሁንና ፈተና ራሱ ኃጢአት አይደለም፣ ሰው ሲፈተን በምኞቱም ሲወድቅ ኃጢአትን ይሠራል፣ ግን ፈተናን ታግሶ የሚጸና ሰው እርሱ የተባረከ ነው።

«ብፁዓን እለ ንጹሐን በፍኖቶሙ፣ ወእለ የሐውሩ በሕገ እግዚአብሔር» በመንገዳቸው ንጹሐን የሆኑ በእግዚአብሔርም ሕግ የሚሔዱ ምስጉኖች ናቸው (መዝ.፻፲፰፥፩) ይላል ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት።

የእግዚአብሔርን ሕግ መከተል፣ የእግዚአብሔርን ሕግ መጠበቅ ያስመሰግናል፣ በረከትን ያሰጣል፣ ድኅነትንም ያስገኛል።

ሰው ሁሉ የእግዚአብሔር ሕግ መልካም መሆኑን መምህር ሳያስፈልገው በተፈጥሮ ባሕርዩ ያውቃል።



www.ethiopianorthodox.org

ለመልካም ነገር ተቃራኒ የሆነውን ሁሉ ሲሠራ ኅሊናው ይነግረዋል። ኅሊና ክፉውንና በጎውን ለይተን የምናውቅበት አመዛዛኝ ዳኛ ነው። ኅሊና ሰብእ ከሕግ የወጣ ሥራ ሲፈጸም የአደጋ ድምፅን ይሰጣል።

በዚህ ዓለም ለሚኖር ሰው ሁሉ ጥፋትን የማድረግ ምክንያትና መነሻ የሚሆኑ ድርጊቶች ከፊቱ ባይዘረጉና ባያጋጥሙት ኑሮ አንድን ነገር ማድረግ እንደማይችልና አሁን በዓለም የሚታዩት በሕገ ሥጋ የሚደረጉት የሰው ልጅ ሥጋውያን ድርጊቶች ሁሉ ወደመታየት ደረጃ ሳይደርሱ በቀሩ ነበር።

ሰው በልቡናው የእግዚአብሔር ሕግ መልካምና ትክክለኛ መሆኑን ቢያውቅም ከባሕርዩ ድክመት የተነሣ በጎውን ትቶ መጥፎውን ይከተላል። በዚህም ምክንያት በፈተና ወጥመድ ይያዛል። የፈተናው ሸክም ሲከብደውና ሲያስጨንቀው እግዚአብሔር ፈተነኝ ይላል፤ ግን እግዚአብሔር ማንንም በክፉ አይፈትንም። እያንዳንዱ ወዶ በሚከተለው ሥራ ይፈተናል ተብሏልና። (ያዕ.፩፥፲፪–፲፰) ያም ሆኖ የስነ ፍጥረት ባለቤት የሆነው እግዚአብሔር ሰዎችን ከሚደርስባቸው የችግር ወጥመድ ለማውጣትና ከጭንቀታቸውም ለማዳን ሁል ጊዜ ፈቃደኛና ቸር ጠባቂ ነው። ወደ እርሱ የሚመለሱ ሁሉ ይድናሉ፤ ሰውም ከእርሱ በመማር ችግር የደረሰበትን ሰው የመርዳት ግዴታ አለበት።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ይህን የሰው ዘር አጥፊ የሆነ በሽታ ከተከሠተበትና ዜናውም ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ ባሏት የትምህርት አውታሮችና የአሠራር መዋቅሮች ሁሉ የማስተማር ጥረቷን በቀዳሚነት ቀጥላ ቆይታለች። ብዙ መቶ ሺህ ለሆኑት ካህናትና በሚሊዮን ለሚቆጠሩ ተከታዮቿ ምእመናን በቃልና በጽሑፍ ሰፊ ትምህርት ስትሰጥ ቆይታለች፤ አሁንም ቀጥላለች።

ስለዚህ ታላቅ የሕይወት አድን ዘመቻ በሀገራችን ካሉ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ከሃይማኖት ተቋሞች ጋር በመተባበር በሕዝባዊ መድረክ የሚገኙ የወንጌል መምህራንን እያሰባሰበች በብዙ የትምህርት ዐውደ ጥናቶች ተሳትፋለች፤ እየተሳተፈችም ነው።

በርግጥ ኃላፊነቱ የሁሉም ሰው ነው ተብሏል። የሃይማኖትም ጉዳይ አለበት ሃይማኖት የፈጣሪን ህልውና ማወቅና በስሙ ማመን ብቻ አይደለም፤ መታመንም ያስፈልጋል። ላመኑበትና ለሚከተሉት የሃይማኖት ሕግ መገዛት፤ የእግዚአብሔርን ቃል መስማትና ሰምቶ በሥራ መግለፅ የአማንያን ሃይማኖታዊ ግዴታ ነው። ሕግጋት ሰውን የሚጠብቁት የሚጠበቁትን ያህል ነው። በእግዚአብሔር የሚያምን ሰው የእግዚአብሔርን ሕግ መጠበቅ፡ ትእዛዙን መፈጸምና በሥርዓቱ መኖር አለበት።

በሃይማኖት ዓለም የሚኖር ሰው ሁሉ፤ የእግዚአብሔር ሕግ መልካም እንደሆነ ያውቃል ብለናል። ግን መልካም የሆነውን ደጉን ሕግ የመፈጸም ፍላጎት ቢኖረውም የማይወደውን በመሥራቱ ለአደጋና ለጥፋት ይጋለጣል። በተፈጥሮ የአኗኗር ሥርዓት ለመረዳዳት፤ ዘር ለመተካትና በሕገ ወጥ መንገድ ከሚፈጸም ፍትወት (ሩካቤ) ለመጠበቅ በተፈቀደው «አንድ ወንድ ለአንዲት ሴት፡ አንዲት ሴት ለአንድ ወንድ» ለሚለው ሕግ ሁሉም ራሱን ቢያስገዛ፡ ሕይወቱን ይጠብቃል፤ ኅብረተሰቡንም ከጥፋት ያድናል። በኅብረተሰብ አኗኗር ከሚታዩ የጥፋት ክስተቶች አብዛኞቹ የእምነት ጉድለት ውጤቶች መሆናቸውንም ጭምር በውል ማጤን ያስፈልጋል።

ይሁንና ችግሩ ካልቀረ ዘንድ በሚቻለው ሁሉ በመታገል የጥፋት መንገዶችን ለመዝጋት በኅብረት መሥራት ይኖርብናል። ለበሽታው ያልተጋለጡት ወንድሞችና እኅቶች እስከ መጨረሻው እንዲጠበቁ፤ በወጥመዱ የገቡ ሕሙማንም የመጽናናትና የመዳን ተስፋን እንዲያገኙ በርኅራኄና በፍቅር ቀርበን መርዳት ሰብአዊም ሃይማኖታዊም ግዴታችን ነው። በበሽታው የተያዙትን ወገኖች መርዳት ማለት «ወንድምህን እንደ ራስህ አድርገህ ውደድ» የተባለውን ሕግ መፈጸም ነው። በተፈጥሮ መሰል የሆነውን ሰው ሁሉ መውደድና መርዳት ያስፈልገናልና። የክርስትና ሃይማኖት ትምህርት መሠረታዊ ትርጉም ፍቅር፤ ሰላም፤ ርኅራኄ፤ መጽናናት፡ ፈውስ፤ ደኅንነት ስለሆነ ቃሉን በተግባር የመግለፅ ግዴታ አለብን። እግዚአብሔር ፍጥረቱን ሁሉ ይወዳል፤ ይልቁንም ለሰው የላቀ ፍቅር አለው። ሰው ሕጉንና ሥርዓቱን አፍርሶ በበደለ ጊዜ አንድና የሚወደውን የባሕርይ ልጁን ካሣ አድርጎ ሰጥቷል። ከዚህ የበለጠ ፍቅር የለምና የእግዚአብሔርን ልጅ ከዙፋኑ ያወረደው፤ በሰው ሥጋ እንዲገለጥ ያደረገው ፍቅር ነው። ሰውም ይህን ምሳሌ መከተል አለበት። እግዚአብሔር ምን ጊዜም ሰዎችን ይወዳልና።

እግዚአብሔር የሚጠላው ኃጢአትን እንጂ ኃጢአተኞችን አይደለም ተብሏል። እርሱ ተፈጥሮአችንንና የባሕርያችንን ደካማነት ሁሉ ያውቃል። እርሱን የሚያሳዝነው በደላችንን አለመረዳት፤ በኃጢአታችን አለመጸጸትና በንስሐ ወደ እርሱ ለመመለስ አለመወሰናችን ነው። ከበደል ለመራቅ በብርቱ መጠንቀቅ፡ በሕጉና በትእዛዙ ጸንቶ ለመኖር ጥረት ማድረግ ከሁሉ ሰው የሚፈለግ ቀዳሚ ተግባርና ግዴታ ነው። ስህተት ከተፈጸመም ዘንድ በንስሐ መመለስ



አማራጭ የሌለው ሌላው የሕይወት መንገድ ነው። እግዚአብሔር ቸር ስለሆነ ጠፍተው ወደ እርሱ የሚመለሱትን ሁሉ ይቀበላቸዋል። ከተናቁት፡ ከተጠሉትና በብቸኝነት ዓለም ከሚጨነቁት ጋር ይኖራል። ያጽናናቸዋል፡ ያረጋጋቸዋል፤ ከጭንቀታቸው የሚወጡበትን መንገድ ይመራቸዋል። የጨለማ የብቸኛነት ሕይወታቸውን ያበራላቸዋል።

እንግዲህ የአሰቃቂውን የኤድስ በሽታ የመዛመት ባሕርዩንና ቀሳፊ ጠባዩን ከሩቅ በመፍራት በሕመሙ የተያዙትን ወገኖች ለመሸሽና ለማግለል የሚደረግ ጥረትና ስሜት ይኖራል። ሕሙማኑ ከሌላው በተለየ መንገድ በፈጸሙት ኃጢአትና በደል እንደመጣባቸው ተደርጎ የሚገመትበትም ሁኔታ ይኖራል። መታየት ያለበት ቁም ነገር ግን ከዚህ ሁሉ በብዙ መልኩ የተለየ መሆኑን ነው። በሽተኞቹ በአንድ ወይም በሌላ መንገድ ለበሽታው ተጋልጠዋል። ከመሆኑ በፊት ይፈሩትና ይጠሉት በነበረው ጠላት ወጥመድ ውስጥ ገብተዋል። ስለሆነም መጽናናትንና መረዳትን ይፈልጋሉ፤ በእነርሱ የደረሰው በሌላው ሊደርስ ከሚችለው የተለየ አይሆንም። በሽታው የሚዛመትበትን መንገድ አውቆና ተረድቶ ሕገ እግዚአብሔርን ከመጠበቅና የራስን የሕይወት ጉዞ ከመመርመር ጋር የኤድስ ሕሙማንን መርዳት ያስፈልጋል። የእኛ ሕይወት ከእነርሱ ሊለይ አይችልምና።

በአንድ ወቅት ለተከሰተውና ለሚከሰተው ችግር ለአሠራር አመች ይሆን ዘንድ ትኩረት በመስጠት፤ ሁሉም ተባብሮ ጊዜ ያመጣውን ችግር ማስወገድ ይኖርበታል።

እንግዲህ ያለፈውንና የጊዜውን ሕይወታችንን መነሻ በማድረግ ወይንም ከአለፈውና ከአሁኑ ሕይወታችን በመማር የአሁኑንና የወደፊቱን ሕይወታችንን ጤናማ ማድረግ የሚቻለው በአሁኑና በሚቀጥለው ትውልድ ጥረት ስለሆነና ስለሚሆን የአሁኑንና የሚቀጥለውን ትውልድ ለዚህ አላማ በትምህርት ማዘጋጀቱና ብቁ ማድረጉ አማራጭ የማይገኝለት በመሆኑ ከግለ ሰብእና ከቤተ ሰብእ ጀምሮ ሁሉም ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይጠበቅበታል።

ሕገ እግዚአብሔርን ጠብቆ በመኖር የርስታችን፤ የታሪካችንና የግብራችን ወራሽና ቆራሽ የሆነ ጤነኛ ትውልድ መተካትና ማሳደግ የሚቻለው፤ ሁሉም ተግባብቶና ተመካክሮ ሲሠራ ብቻ መሆኑ ግልፅ ነው።

ስለሞት ማሰብ ለማንም ሰው ቢሆን ቀላል ነገር አይሆንም። የምንኖረው ሞት የሁሉ ዕድል ፈንታ በሆነበት ዓለም ነውና። መጽሐፍ ቅዱስ «ለሰዎች አንድ ጊዜ መሞት ተመደበላቸው» ይላል (ዕብ.፱፥፳፯) ይህም በየዕለቱ በዓይናችን የምናየው ነውና።

በያለንበት፤ ሰው ሁሉ ሲሞት እንመለከታለን። ተመልካቹም ተራውን ጠብቆ ይሞታል። ፍርዱ በዚህ ብቻ አይቆምም። ከሞተ ሥጋ በኋላም በኃጢአት ላይ የሚሰጥ የእግዚአብሔር ፍርድ አለ። «ለሰዎች አንድ ጊዜ መሞት፤ ከእርሱ በኋላም ፍርድ ተመደበላቸው» ይላል። (ዕብ.፱፥፳፯)

ስለሆነም ወገኖቻችን ባላቸው የእምነት ተስፋ ተረጋግተውና ተጽናንተው መኖር እንዲችሉ መመሪያና ምክር ይሆናቸው ዘንድ ይህን ትምህርታዊ መልእክት እናስተላልፋለን።

የገደለውን ጥሎ፤ የቆመውን አመንምኖ ለመግደል በተለያየ ምክንያት ከሰውነት የሚጣበቅ መድኃኒት የለሽ ክፉ በሽታ በሀገር ደረጃ በበለጠ የተስፋፋው በከተሞቻችን መሆኑን ከዜና ማሰራጫ መስማት ችለናል።

ከዚህ አንፃር በተለይ የከተማ ኗሪዎች የሆን ሁሉ ሕይወታችንን ለመምራትና ጤንነታችንን በበለጠ ለመጠበቅ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርብናል።

ይህም የትምህርት ሒደት ከዘመነ አበው ጀምሮ የራቁትን ለማቅረብ፤ የቀረቡትንም ለማገልገልና ለመመገብ የትውፊት ውርስ ሆኖ ቆይቷል።

ስለዚህ ደዌ፤ በየጊዜው ከተጻፈውና ከተሰጠውም ትምህርት ዕውቀትን በማገኘት፤

- እያንዳንዱ ሰው ሕይወቱን በመጠበቅ፤
- በዚሁ አስከፊ በሽታ የተያዙ ወገኖችንም በመንከባከብ፤
- በአጠቃላይም የደዌውን ጎጂ ባሕርይ ሁሉም ኅብረተሰብ ተገንዝቦ

የተሰጠውን መመሪያ፡ ትምህርትና ምክር በተግባር እንደሚያረጋግጥ እምነታችን ጽኑ ነው።

እግዚአብሔር ለሰው ልጅ መልካሙን እንደሚያስብለት ሁሉ ሰውም ፈጣሪው እግዚአብሔርን የሚያስብ ቢሆን ኖሮ ህልውናው በሰመረ ነበር።

ስለዚህ እግዚአብሔር አምላካችን ምሕረቱን፤ ቸርነቱን እንዲያደርግልን አዘውትረን በጸሎት እንጠይቀው።

እግዚአብሔር አምላካችን ለሕዝባችን፤ ለሀገራችንና ለዓለሙ ሁሉ ሰላሙን፤ ፍቅሩን፤ ጤንነቱን ይስጥልን።

✣ ✣ ✣



www.ethiopianorthodox.org

ትምህርተ ሃይማኖት

# ትምህርተ ሃይማኖት



በመምህር ኤልያስ አብርሃ

## የሃይማኖት ትርጉም

ሃይማኖት ማለት፣ ለዓለም ፈጣሪ አለው ብሎ ማመን ነው። ትምህርተ ሃይማኖት ማለት ደግሞ፣ ሃይማኖትን የሚማሩበት፣ የሚያስተ ምሩበት፣ የሃይማኖት ትምህርት ማለት ነው።

## የሃይማኖት መገኛ:-

ሃይማኖት የተገኘው ከባለቤቱ ከእግዚአ ብሔር ሲሆን ዓላማውም ሰዎች በሃይማኖት አማካኝነት ማንነቱን አውቀው፣ በእምነት ወደ እርሱ በመቅረብ፣ የዘለዓለም ሕይወት ለማግኘት እንዲችሉ ነው። ይህንን በሚከተ ለው ሁኔታ ገልጦታል።

### ሀ. በተፈጥሮ

«ስለ እግዚአብሔር ሊታወቅ የሚቻለው በእነርሱ ዘንድ ግልፕ ነውና። የማይታየው ባህርይ እርሱም የዘለዓለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሠሩት ታውቆ ግልፕ ሆኖ ይታያልና» ሮሜ.፩፥፲፱–፳፩።

«ሕግ የሌላቸው አሕዛብ ከባሕርያቸው የሕግን ትእዛዝ ሲያደርጉ እነዚያ ሕግ ባይኖራቸው እንኳ ለራሳቸው ሕግ ናቸውና እነርሱም ኅሊናቸው ሲመሰክርላቸው፣ አሳባ ቸውም እርስ በርሳቸው ሲካሰስ ወይም ሲያመ ካኝ በልባቸው የተጻፈውን የሕግ ሥራ ያሳ ያሉ።» ሲል እግዚአብሔር እርሱነቱን አው ቀው ሊያምኑበት የሚያስችል ዕውቀት በሰዎች ልቡና ጽፎ ያስቀመጠውና በተፈጥሮ የሥራ ክንዋኔም ያጠናከረው መሆኑን በግልፅ ያሳያል ሮሜ.፪፥፲፬–፲፭።

### ለ. ራሱን በመግለጥ

«እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ» ዘጸ.፳፥፪–፫። «ያመነ የተጠመቀም ይድናል ያላመነ ያልተጠመቀ ግን ይፈረድበታል» ሲል ራሱን ገልጦ ሃይማኖት መግለጡን እናስተው ላለን (ማር.፲፮፥፲፮)።

እንግዲህ በዚህ መልኩ ሃይማኖት ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ሊገናኝበት፣ የዘለዓለም ሕይወትም ሊወርስበት፣ እግዚአብሔር በራሱ በጥንተ ፍጥረት፣ በሥነ ፍጥረትና ራሱን በመ ግለጥ የገለጠው ከእግዚአብሔር የተገኘ ነው። ጻድቅ በእምነት ይኖራል ዕን.፪፥፬።

## ባሕርየ እግዚአብሔር

ሃይማኖት ብዙ ክፍልና ዘርፍ ያለው ቢሆንም ዋና ዋናዎቹ ክፍሎች የሚከተሉት ናቸው። እነርሱም:-

### ሀ. የእግዚአብሔር ህልውና።

«ተራሮች ሳይወለዱ፣ ምድርም፣ ዓለ ምም ሳይሠሩ፣ (ሳይፈጠሩ) ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ድረስ አንተ ነህ» መዝ.፹፱፥፪። «አንተ ግን ያው አንተ ነህ፣ ዓመቶችህም ከቶ አያልቁም» (መዝ.፻፩፥፳፯)።

«እግዚአብሔር እንዲህ ይላል እኔ ፊተኛ ነኝ፣ እኔም ኋለኛ ነኝ። ከእኔ ሌላም አምላክ የለም። እንደ እኔ ያለ ማን ነው? ይነሣና ይጥራ ይናገርም» ኢሳ.፵፬፥፮–፯። «ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ የነበረውና የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ፣ ያለው አምላክ» ራእ.፬፥፰።

በዚህም መሠረት እግዚአብሔር መጀመ ሪያውና መጨረሻው ከዚህ እስከዚህ ድረስ ነው ተብሎ ሊወሰን በማይችል ህልውና ወይም አኗኗር የነበረ ያለና የሚኖር መሆኑን ማመን ያስፈልጋል። እግዚአብሔርን አለማወ ቅ ስንፍናና ጭፍን የጨለማ ጉዞ እንጂ ጥበብ አይደለም። «ሰነፍ በልቡ አምላክ የለም ይላል» ተብሎ ተጽፎአልና (መዝ.፲፫፥፩)።

### ለ. የእግዚአብሔር ኵነት ወይም አኗኋን

«የእግዚአብሔር ቸርነት ምድርን ሞላ በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች ጸኑ። ሠራ ዊታቸውም ሁሉ በአፉ እስትንፋስ» መዝ.፴፪፥፭–፮።

«እግዚአብሔርም አለ ሰውን በመል ካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር» ዘፍ. ፩፥፳፮። «እግዚአብሔር አምላክም አለ። እነሆ አዳም መልካምንና ክፉን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ» ዘፍ.፫፥፳፪።

«እግዚአብሔርም አለ...ኑ፣ እንውረድ፣ አንዱ የአንዱን ነገር እንዳይሰማው ቋንቋ ቸውን በዚያ እንደባልቀው» ዘፍ.፲፩፥፮–፯። «እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመ ቃችኋቸው...ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው» ማቴ.፳፰፥፳።

«በመጀመሪያ ቃል ነበረ፣ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ቃልም እግዚአ ብሔር ነው። ይህ በመጀመሪያው በእግዚአ ብሔር ዘንድ ነበረ» ዮሐ.፩፥፩–፫።

«እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ እመኑኝ» ዮሐ.፲፬፥፲፩። «ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል» ዮሐ.፲፭፥፳፮።

እንግዲህ በነኝህ ጥቅሶች መሠረት እግዚአብሔር በሁኔታው የተለየ ሦስትነትና አንድነት እንዳለው እናስተውላለን። እግዚአብ ሔር አንድ ሲሆን ሦስት፣ ሦስት ሲሆን አንድ ነው። ይህም ማለት እግዚአብሔር በአካል፣ በስም፣ በግብርና በኩነታት ሦስት ሲሆን በባሕ ርይ በህልውና፣ በሥልጣንና በመሳሰሉት አንድ ነው ማለት ነው።

### ሀ. የአካል ሦስትነት

ለአብ ፍጹም አካል፣ ፍጹም ገጽ፣ ፍጹም መልክዕ አለው። ለወልድም ፍጹም አካል ፍጹም ገጽ ፍጹም መልክዕ አለው። ለመንፈስ ቅዱስም ፍጹም አካል፣ ፍጹም ገጽ፣ ፍጹም መልክዕ አለው። (ሃይማኖተ አበው ዘአቡሊዲስ)

### ለ. የግብር ሦስትነት

የአብ ግብሩ መውለድ ማሥረፅ ነው።

የወልድ ግብሩ መወለድ ነው።

የመንፈስ ቅዱስ ግብሩ መሥረፅ ነው።



### ሐ. የስም ሦስት

አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ነው።

### መ. የኵነታት ሦስትነት

ኵነታት ማለት ልብነት፣ ቃልነት፣ ሕይወትነት ናቸው። በዚህም መሠረት የአብ ከዊንነቱ ልብነት ሆኖ ለወልድና ለመንፈስ ቅዱስ ልባቸው ነው። የወልድ ከዊንነቱ ቃልነት ሆኖ ለአብና ለመንፈስ ቅዱስ ቃላቸው ነው። የመንፈስ ቅዱስም ከዊንነቱ ሕይወትነት ሆኖ ለአብና ለወልድ ሕይወታቸው ነው። ይህንን ሊቃውንት አስፍተው ሲናገሩ እንዲህ በማለት ገልጸውታል። አብ አልተወለደም፣ ዓለም ሁሉ ሳይፈጠር ወልድን የወለደ ነው እንጂ፣ ወልድም ዓለም ሁሉ ሳይፈጠር ከእግ ዚአብሔር አብ ተወለደ፣ መንፈስ ቅዱስም ዓለም ሁሉ ሳይፈጠር ከእግዚአብሔር አብ ሠረፀ። (ሃይማኖት አበው ዘቅዱስ አትናቴዎስ ምዕራፍ ፳፫ ክፍል ፩ ቁጥር ፫)

አብም ለወልድና ለመንፈስ ቅዱስ ልቡናቸው ነው። ወልድም ለአብና ለመንፈስ ቅዱስ ቃላቸው ነው። መንፈስ ቅዱስም ለአብና ለወልድ ሕይወታቸው ነው። (ሃይማ ኖተ አበው ዘአቡሊዲስ ምዕራፍ ፴፱ ክፍል ፪ ቁጥር ፰፣) ባሕርያቸው በእውነት አንድ ሲሆን በመልክዕ፣ በአካል፣ ፍጹማን የሚሆኑ ሦስት ገጻት እንደሆኑ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን። (ሃይማኖተ አበው ዘአቡ ሊዲስ ምዕራፍ ፴፰ ክፍል ፪ ቁጥር ፫)። የእግ ዚአብሔር ሦስትነቱ በዚህ መልኩ ሲገለጽ አንድነቱ ደግሞ እንመለከታለን።

እነዚህ ሦስቱ ኵነታት በህልውና ሲዋ ሐዱ እንዲህ ነው። አብ ልባቸው ስለሆነ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ውስጥ አለ፣ ከቃሉ ከወልድ ከሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ አይለ ይም፣ ለምሳሌ የሰው ነፍስ ልብነቷ ከቃል ነቷና ከሕይወትነቷ ሊለይ እንደማይቻል። ወልድ ቃላቸው ስለሆነ በአብ በመንፈስ ቅዱስ ውስጥ አለ፣ ከልቡ ከአብ ከሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ አይለይም፣ የነፍስ ቃልነቷ ከልብነቷና ከሕይወትነቷ ሊለይ እንደማይቻል። መንፈስ ቅዱስ ሕይወታቸው ስለሆነ በአብና በወልድ ውስጥ አለ፣ ከልቡ ከአብ ከቃሉ ከወልድ አይለይም። የነፍስ ሕይወትነቷ ከልብነቷና ከቃልነቷ ሊለይ እንደማይቻል። ከዚህ የምን ረዳው ዋና ቁም ነገር የሰው ነፍስ በአኳኋን ሦስትነት ስላላት ሦስት እንደማትባል ሁሉ እግዚአብሔርም በስም፣ በግብር፣ በአካልና በኩነታት ሦስትነት ቢኖረውም በህልውና፣ በባሕርይና በሥልጣን ሦስት አይባልም። ነፍስ አንዲት እንድትባል እግዚአብሔርም በህልውና አንድ ይባላል። የአብ፣ የወልድ፣ የመንፈስ ቅዱስ ባሕርያቸው አንድ ነው። መንግሥታቸው አንድ ነው። ፈቃዳቸው አንድ ነው። ፈጽሞ መለየት ሳይኖርባቸው የሦስቱም አሳባቸው አንድ ነው። አብ በወል ድና በመንፈስ ቅዱስ አለና፣ ወልድም በአብና በመንፈስ ቅዱስ አለና፣ መንፈስ ቅዱስም በአብና በወልድ አለና። (ሃይማኖተ አበው ዘአቡሊዲስ ምዕራፍ ፲፰ ክፍል ፪ ቁጥር ፬)።

ከዚህ በላይ በተገለጸው መሠረት እግዚ አብሔር በአካል ሦስት ቢሆንም በባሕርይ፣ በህልውና አንድ ስለሆነ፣ አንድ እግዚአብሔር ይባላል። «እስራኤል ሆይ፣ ስማ፣ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው» ዘዳ.፮፥፬። ስለዚህ እግዚአብሔርን ስናምን አንድነቱንና ሦስትነቱን አውቀን በማመን መሆን ይገባል።

### ሀ. የእግዚአብሔር ከሃሊነት

«በውኑ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለን?» ዘፍ.፲፰፥፲፬፣ ሉቃ.፩፥፴፯። «...በሰማይም ሠራዊት በምድርም ላይ በሚኖሩ መካከል እንደ ፈቃዱ ያደርጋል፣ እጁንም የሚከለክላት ወይም ምንታደርጋለህ? የሚለው የለም» ዳን.፬፥፴፭።

«ሁሉን ታደርግ ዘንድ ቻይ እንደሆንህ አሳብህም ይከለከል ዘንድ ከቶ እንደማይቻል አወቅሁ» ኢዮ.፵፪፥፪ «በሰማይና በምድር በባሕርና በጥልቆች ሁሉ እግዚአብሔር የወደደውን ሁሉ አደረገ» መዝ.፻፴፬፥፮። እግዚአብሔር ሁሉን ለማድረግ የሚችል ሁሉን ቻይ መሆኑን በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ምስክርነት በከሃሊነቱ ማመን ማሳመን ያስፈልጋል።

### ለ. የእግዚአብሔር ጥበብና ዕውቀት

«ጥበብና ኃይል ለእርሱ ነውና የእግዚ አብሔር ስም ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ይባረክ» ዳን.፪፥፳። «የእግዚአብሔር ባለጠግ ነትና ጥበብ እውቀቱም እንዴት ጥልቅ ነው፣ ፍርዱ እንዴት የማይመረመር ነው ለመን ገዱም ፍለጋ የለውም» ሮሜ.፲፩፥፴፫። «እኛን በሚቆጣጠር በእርሱ ዓይኖች ፊት ሁሉ ነገር የተራቆተና የተገለጠ ነው እንጂ በእርሱ ፊት የተሠወረ ፍጥረት የለም» ዕብ.፬፥፲፫።

በዚህ ሁሉ የእግዚአብሔር ጥበቡና ዕውቀቱ የማይመረመር ረቂቅና ጥልቅ ሁሉም ነገር በፊቱ የተገለጸ ያለፈውንም ሆነ የሚመጣ የማይሠወረው መሆኑን አምነን ልናመልከው ይገባል።

### ሐ. የእግዚአብሔር ፍቅርና ቸርነት

«እግዚአብሔር ፍቅር ነው» ፩ዮሐ. ፬፥፲፮። «በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና» ዮሐ.፫፥፲፮። «ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሣ በበደላችን ሙታን እንኳ በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወት ሰጠን» ኤፌ.፪፥፭። «ወይስ የእግዚ አብሔር ቸርነት ወደ ንስሐ እንዲመራህ ሳታውቅ የቸርነቱንና የመቻሉን የትዕግሥ ቱንም ባለጠግነት ትንቃለህን?» ሮሜ.፪፥፬። «እርሱ በክፉዎችና በበጎዎች ላይ ፀሐይን ያወጣል በጻድቃንና በኃጢአተኞችም ላይ ዝናሙን ያዘንማልና» ማቴ.፭፥፵፭። «አባታ ችሁ ርኅሩኅ እንደሆነ ርኅሩኆች ሁኑ» ሉቃ.፮፥፴፮።

ዓለማችን በብዙ ዓመፅና ግፍ የተሞላች ስትሆን ውላ ማደርዋ ከዚህ ላይ ካየነው ከእግዚአብሔር ፍቅርና ቸርነት መሆኑን በሚገባ ማመን ያስፈልጋል። ያለዚያማ ዳዊት በመዝ.፻፳፱፥፫ «አቤቱ ኃጢአትንስ ብትጠ ባበቅ አቤቱ ማን ይቆማል?» ብሎ እንደ ተናገረው መዋሉ ማደሩ ቀርቶ ለአፍታ እንኳ መቆም የሚችል አልነበረም። ስለሆነም የእግዚአብሔር ፍቅርና ቸርነት እጅግ ትልቅና ሰፊ መሆኑን አምነን ፍቅሩንና ቸርነቱን በንስሐ ልንጠቀምበት ያስፈልጋል።

### መ. የእግዚአብሔር ምሉእነት

«እኔ የቅርብ አምላክ ነኝ እንጂ የሩቅ አምላክ አይደለሁም። ሰው በስውር ቢሸሸግ





www.ethiopianorthodox.org

እኔ አላየውምን? ሰማይንና ምድርንስ የምላሁ እኔ አይደለሁምን?» ኤር.፳፫፥፳፫–፳፬።

«ወደ ሲኦልም ብወርድ በዚያ አለህ» መዝ.፻፴፰፥፰ እግዚአብሔር በባሕርዩ መንፈስ ከመሆኑም በላይ ስፋቱ ምላቱ ከዚህ እስከ ዚህ ነው ተብሎ አይወሰንም። ሰማይንና ምድርን መልቶ ከዚህ በተረፈ እርሱ ባወቀ እንጂ በፍጡራን አይወሰንም፤ በመሆኑም የትም ቦታ ሆኖ ሰው ቢሸሽግ ከእግዚአብሔር አይሠወርምና ምሉዕነቱንና ስፉሕነቱን አምነን ልናመልከው ይገባል።

## ሠ. የእግዚአብሔር መንፈስነት

«እግዚአብሔር መንፈስ ነው የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ይገባል (ዮሐ.፬፥፳፬)። ጌታ ግን መንፈስ ነው፤ የጌታም መንፈስ ባለበት በዚያ አርነት አለ።» ፪ቆሮ.፫፥፲፯።

እግዚአብሔር አካል ያለው መሆኑ ቢታወቅም እንኳ እጅግ የረቀቀ መንፈስ ስለሆነ በፍጡራን ዓይን ፈጽሞ ሊታይ አይችልም። ለዚህም ነው መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም ብሎ ዮሐንስ የጻፈልን ዮሐ.፩፥፲፰።

ስለሆነም እግዚአብሔር በአካሉ፤ በአሳቡ በሥራው ሁሉ እጅግ በጣም የረቀቀ መሆኑን አውቀን ልናምን ይገባል።

## ረ. የእግዚአብሔር ፈጣሪነት

«በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ» ዘፍ.፩፥፩። «አቤቱ አንተ ከጥንት ምድርን መሠረትሁ ሰማያትም የእጅህ ሥራ ናቸው» መዝ.፻፩፥፳፭። «እጄም ምድርን መሠረታለች ቀኜም ሰማያትን ዘርግታለች» ኢሳ.፵፰፥፲፫። «ጌታችንና አምላካችን ሆይ አንተ ሁሉን ፈጥረሃልና ስለፈቃድህም ሆነዋልና ተፈጥረውማል ራእ.፬፥፲፩።

በሰማይም ሆነ በምድር ያለው፤ የሚታየውም ሆነ የማይታየው ሁሉ እግዚአብሔር ፈጠረው አስገኘውም፤ ይለናል ቅዱስ መጽሐፍ፤ ስለሆነም እግዚአብሔር የፍጥረታት ሁሉ ፈጣሪ መሆኑን አምነን ልንገዛለት ያስፈልጋል።

## ሰ. የእግዚአብሔር ጥበቃና መግቦት

«እግዚአብሔር ከተማን ካልጠበቀ ጠባቂ በከንቱ ይደክማል» መዝ.፻፳፮፥፩። «የሚጠብቅህም አይተኛም እግዚአብሔር ይጠብቅሃል ነፍስህንም ከክፉ ሁሉ ይጠብቃል» መዝ.፻፳፥፫–፯።

«የእናንተስ የራሳችሁ ጠጉር ሁሉ እንኳ ተቆጥሮአል» ማቴ.፲፥፴። እግዚአብሔር ዓለምን ፈጥሮ እንዲሁ አልተወውም የእያንዳንዱ ፍጡር የራሱ ጠጉር ስንኳ ሳይቀር በእግዚአብሔር ዘንድ ተቆጥሮ የታወቀና የሚጠበቅ ነው። ስለሆነም ተፈጥሮና በውስጧ ያሉ ፍጡራን ሁሉ በእግዚአብሔር ጥበቃ ሥር ናቸውና በየትኛውም ጊዜና ቦታ ለሚጠብቀን ፈጣሪ ክብር እየሰጠን ልንታዘዘው ይገባል። እግዚአብሔር ሲጠብቀን እንዲሁ በደረቁም አይደለም። ምግባችንንም ሁሉ በየጊዜው በመስጠት ነው። «የሁሉ ዓይን አንተን ተስፋ ያደርጋል፤ አንተም ምግባቸውን በየጊዜው ትሰጣቸዋለህ። አንተ እጅህን ትዘረጋለህ፤ ሕይወት ላለውም ሁሉ መልካምን ታጠግባለህ» መዝ.፻፵፬፥፲፭–፲፮።

«የዕለት እንጀራችንን ስጠን ዛሬ» ማቴ.፮፥፲፩። ስለዚህ በየጊዜውና በየሰዓቱ በየትኛውም ቦታ እየመገበ የሚጠብቀን እግዚአብሔር መሆኑን አውቀንና አምነን በሃይማኖት ጸንተን ልንኖር ይገባል።

## ሸ. የእግዚአብሔር ፍጹምነት

«እኔ እግዚአብሔር አልለወጥም» ሚል.፫፥፮። «እግዚአብሔር የተስፋውን ቃል ለሚወርሱ ፈቃዱ እንደማይለወጥ አብልጦ ሊያሳያቸው ፈቀደ» ዕብ.፮፥፲፯።

«እንግዲህ የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደሆነ እናንተም ፍጹማን ሁኑ» ማቴ.፭፥፵፰። የእግዚአብሔር ፍጹምነት ማቆሚያ ዳር ድንበር ሳይኖረው በሁሉም ሥራው የሚሆን ነው። ይህም ማለት በሚናገረው፤ በሚፈርደው፤ በሚሠራው ሁሉ ምንም ዓይነት ጉድለት ሳይኖረው በብቃት ይፈጽማል ማለት ነው።

ስለሆነም በሚሠራው ሁሉ አይጸጸትም ሐሰትን ይናገር ዘንድ እግዚአብሔር ሰው አይደለም። ይጸጸትም ዘንድ የሰው ልጅ አይደለም። «እርሱ ያለውን አያደርገውምን? የተናገረውንስ አይፈጽመውምን?» ዘኁ.፳፫፥፲፱።

በዚህም መሠረት እግዚአብሔር በቃሉ፤ በፍርዱ፤ በሥራው ሁሉ ፍጹም መሆኑን ማመን ይገባናል።

## ቀ. የእግዚአብሔር አዳኝነት

«ከግብጻውያንም እጅ አድናቸው ዘንድ...ወረድሁ» ዘጸ.፫፥፰። «አንተ የእኔ ነህ በውሀ ውስጥ ባለፍህ ጊዜ ከአንተ ጋር እሆናለሁ፤ በወንዞችም ባለፍህ ጊዜ አያስጥሙህም፤ በእሳትም ውስጥ በሄድህ ጊዜ አትቃጠልም፤ ነበልባሉም አይፈጅህም፤ እኔ የእሥራኤል ቅዱስ አምላክህ እግዚአብሔር መድኀኒትህ ነኝ» ኢሳ.፵፫፥፩–፫።

«እኔ አድንህ ዘንድ ከአንተ ጋር ነኝና ከፊታቸው አትፍራ ይላል እግዚአብሔር» ኤር.፩፥፰።

«ከእኔም በቀር አምላክ እንደሌለ እዩ፤ እኔ እገድላለሁ፤ አድንማለሁ። እኔ እመታለሁ፤ እፈውስማለሁ ከእጄም የሚያድን የለም» ዘዳ.፴፪፥፴፱።

በነኝህ ጥቅሶች መሠረት ማዳን መታደግ የእግዚአብሔር አምላካዊ ሥልጣን ስለሆነ ትድግናውን፤ አዳኝነቱን በማመን በየትኛውም ጊዜና ቦታ ብንሆን ፍጹም ማዳን ሊያደርግ የሚችል መሆኑን አምነን፤ እርሱንም በመማጸን ጸንተን፤ በሃይማኖት ልንኖር ያስፈልጋል።

እንግዲህ እስከ አሁን የተመለከትናቸው ሁሉ እግዚአብሔር በሁኔታው ከፍጡራን አስተሳሰብ በላይ ሆኖ ማንም ሊደርስበት በማይችል ባሕርይ ያለና በሁኔታ ሁሉ ፍጹምቻይና ኃያል ምጡቅ ጥልቅ መሆኑን ነው።

ስለሆነም እግዚአብሔርን ስናምን እሱነቱን በተቻለ መጠን ተገንዝበን መሆን ስላለበት ከዚህ በላይ ያየናቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ መረጃዎች በውል አውቀን የሚገባውን ክብር ሰጥተን እንደፈቃዱ ልናምነውና ልናመልከው ይገባናል። ✣



# ወመግደሌ ፀር

ይህ ዓምድ መናፍቃንና አጽራረ ቤተክርስቲያንን የሚያጋልጡ ጽሑፎች የሚቀርቡበት፤ የእመቤታችን፤ የጻድቃንና የሰማዕታት አማላጅነት ተራዳኢነት የሚተነተንበት ይሆናል።



በዲያብሎስ የማታለልና የአመፅ ሥራ በኃጢአት የወደቀውን ልጅነቱንና ክብሩን የአጣውን ሰውን ወደ ነበረ ልጅነቱና ክብሩ ለመመለስ ከሥላሴ አንዱ አካል እግዚአብሔር ወልድ (ቃል) በአብና በመንፈስ ቅዱስ፤ በራሱም ፈቃድ ሰው ሆነ። በዚህም አምላካዊ ጥበብ የዲያብሎስ የክህደትና የአመፅ ሥራ ፈረሰ፤ ተናደ፤ ተወገደ። ይህም ሰውን የማዳን ሥራ በራሱ በጎ ፈቃድና ሰዎችም በውድቀታቸውና ከፈጣሪቸው አምላክ በመለየታቸው ጸጸታቸውን በጸሎትና በመሥዋዕት ወደ ፈጣሪያቸው ስላቀረቡ የተፈጸመ ነው።

ስለዚህም የማዳን ሥራ የእግዚአብሔር ሰው መሆን ለጠፋ የሰው ሕይወት ወሳኝ ስለነበር እግዚአብሔር በራሱና ከሰው በመረጣቸው ነቢያት ሰውን የማዳን ሥራ መርሐ ግብሩን ሰው ከመሆኑ በፊት ተናግሮና አናግሮ እንደ ነበር በሚቀጥሉት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃዎች ወደ ብዙ የትርጉም ትንተና ሳንገባ በአጭር በአጭሩ እንመለከታለን።

ሀ. ቅድመ ሥጋዌ እግዚአብሔር ሰውን ለማዳን ሰው እንደሚሆን የተነገሩ ትንቢቶች:-

፩. «እግዚአብሔርም አለ እነሆ አዳም ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ» ኦሪ.ዘፍ.፫፥፳፪ በዚህ ትንቢት እግዚአብሔር አዳም ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ ሲል እግዚአብሔር አይቀልድም፤ አያፌዝም፤ የማይሆነውንና የማያደርገውንም አይናገርም። የራሱ ያልሆነውን የሰውን ደካማ ባሕርይ ባሕርዩ አድርጎ ሰው እንደሚሆንና ሰውን እንደሚያድን በግልፅ የተናገረው ቃል ነው።

፪. «የእግዚአብሔርም ክብር ይገለጣል ሥጋ ለባሹም ሁሉ በአንድነት ያየዋል» ኢሳ.፵፥፭ የእግዚ

## የዲያብሎስን ሥራ ይሽር ዘንድ የእግዚአብሔር ልጅ ሰው ሆነ።

ቀሲስ ታደሰ አይፎክሩ የሊቃውንት ጉባኤ ባል

አብሔርም ክብር ይገለጣል ሥጋ ለባሹም ሁሉ በአንድነት ያየዋል የተባለው የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጁ እግዚአብሔር ወልድ ነው፤ ሥጋን የተዋሐደና ሰው በዓይኑ ያየው ከሦስቱ አካላት አንዱ እግዚአብሔር ወልድ ብቻ ሰው ስለሆነ ነው።

፫. «እናንተም የምትፈልጉት ጌታ በድንገት ወደ መቅደሱ ይመጣል» ሚል.፪፥፫ የምትፈልጉት ጌታ ወደ መቅደሱ ይመጣል ሲል ቤቱን ሥሩልኝ እኔም በዚያ እገኛለሁ ብሎ ወደ አሠራው ቤተ መቅደስ ሥጋን ለብሶ የገባ ጌታ እግዚአብሔር ወልድ ብቻ ነው (ዘጸ.፳፭፥፰፤ ሐጌ.፩፥፰፤ ሉቃ.፪፥፵፱) ተመልከት። ሌላ በመቅደስ መኖርና መመለክ የሚገባው ማንም የለም።

፬. «ከአንቺ ግን አወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ ከዘለዓለም የሆነ የእስራኤል ገዢ የሚሆን ይወጣል» (ሚክያስ ፭፥፪–፫)። አወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ ከዘለዓለም የሆነ ሲል ከፍጥረታት በፊት በቅድምና የነበረ ሰው የሆነ አምላክ እግዚአብሔር ወልድ መሆኑን በግልፅ ያመለክታል።

፭. «ስለዚህ ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል፤ እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች» (ኢሳ.፯፥፲፬)። ድንግል ትፀንሳለች ስሙንም አማኑኤል ትለዋለች ሲል ነቢዩ ስለማን ነው የተናገረው? ስለ እግዚአብሔር ወልድ ሰው መሆን ነው፤ አማኑኤል ማለት ስመ አምላክ ነው እግዚአብሔር ከሰው ጋር፤ ሰው የሆነ አምላክ ማለት ነው። በዚህ ስም ድፍረት ከአልሆነ በቀር ሰው ሊጠራበት አይችልም ድንግልም ትፀንሳለች የተባለች በሐዲስ ኪዳን መልአኩ ቅዱስ ገብርኤልና ወንጌላውያን እንደ ገለጿት የእግዚአብሔር አማኑኤል እናት ቅድስት ድንግል ማርያም ናት፤ አምላክን በተዋሕዶ በሥጋ የወለደች ድንግል እርሷ ብቻ ነች ከእርሷ በቀር አልነበረችም አትኖርምም። ሊሆንም አይችልም።

፮. «ሕፃን ተወልዶልናልና ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል ስሙም ድንቅ፤ መካር፤ ኃያል አምላክ፤ የዘለዓለም አባት» (ኢሳ.፱፥፮)። ኃያል አምላክ የዘለዓለም አባት ሕፃን ተወልዶ ተሰጥቶናል የተባለው ማነው? ሰው የሆነው የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጁ እግዚአብሔር ወልድ ነው። ለአመኑበት ሁሉ የዘለዓለም



www.ethiopianorthodox.org

አባትና የቤተ ክርስቲያን ራስና ገዥ የአብ የባሕርይ ልጅና የቅድስት ድንግል የማርያም ልጅ እግዚአብሔር ወልድ ብቻ ነው። ነቢዩ ስለሌላ ስለማንም አልተናገረም፣ የዘለዓለም ገዥና አባት ከእግዚአብሔር ወልድ በቀር ማንም የለም።

፯. «ተመለከትሁ የሚረዳም አልተገኘም የሚያግዝም አልተገኘምና ተደነቅሁ፣ ስለዚህ የገዛ ክንዴ መድኃኒት አመጣልኝ» (ኢሳ. ፷፫፥፭፤ ፳፰፥፲፮) የፅናውን የማዕዘን ድንጋይ የሚያምን አያፍርም የገዛ ክንዴ እና የማዕዘን ድንጋይ የተሳለው እዱ መዝራዕቱ የተባለ የአብ ክንዱ የድኅነት መሠረትና ማዕዘን ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን በግልፅ ያሳየናል፣ እሱንም የባሕርይ አምላክ መሆኑን አምኖ የተቀበለ እንደማያፍር አረጋግጦልናል።

፰. «ቃሉን ላከ ፈወሳቸውም፣ ከጥፋታቸውም አዳናቸው» (መዝ. ፻፮፥፳) ቃሉን ላከ የተባለው ማነው? እግዚአብሔር አብ ነው። ቃሉስ የተባለ ማነው? አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድ ነው። የእግዚአብሔር አብና የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ቃላቸው እግዚአብሔር ወልድ ስለሆነ ነቢዩ ቃሉን ላከና ፈወሳቸው አለ፣ በእግዚአብሔር አካላዊ ቃል በወልድ ሰው መሆንም እምነው የተፈወሱት ሕይወት የአገኙት የሰው ልጆች ናቸውና።

ለ. በትንቢቱ መሠረት በእግዚአብሔር ወልድ ሰው መሆን የመልአኩና የወንጌላውያን ምስክርነት:-

፩. «የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ልጁን ላከ ከሴትም ተወለደ» (ገላ.፬፥፬፤ ዘፍ.፫፥፲፭) እግዚአብሔር ሰውን ለማዳን የወሰነው ጊዜ ሲፈጸም የባሕርይ ልጁን ወልድን በተለየ አካሉ ለሥጋ ላከው፣ ላከው ሲባልም በእግዚአብሔር ዘንድ መበላለጥ ኑሮ አንዱ አንዱን የሚልክ ሆኖ አይደለም በፈቃድ አንድ ናቸው፣ ለሰው ድኅነት የሥላሴ ፈቃድ አንድ መሆኑን ለመግለፅ ሐዋርያ የተጠቀመበት ቋንቋ ነው። ሴት የተባለችውም ድንግል ማርያም ናት ፆታዋንና ከሴት የተወለደው ራስህን ይቀጠቅጣል አንተም ሰኮናውን ትቀጠቅጣለህ ያለውን ትንቢታዊ ቃል ለማሳየት እንጂ ሐዋርያው የቅድስት ማርያምን ድንግልናና ስሟን ዘንግቶት አይደለም። (ማቴ .፩፥፲፰–፳፭) ተመልከት።

፪. «መልአኩም እንዲህ አላት እነሆ ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ ስሙንም ኢየሱስ ትዪዋለሽ ከአንቺም የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም» (ሉቃ.፩፥፳፮–፴፭፤ ፪፥፰–፲፬) የተጻፈውን በማስተዋል ተመልከት። ኢየሱስ:- ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ የተባለውና ለመንግሥቱ ፍጻሜ የለውም ተብሎ በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤልና በወንጌላውያን የተመሠከረው የአብ አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድ ነው። ቅዱሳን መላእክትና ወንጌላውያን ምስክርነት የሰጡትና የጻፉት ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነትና ሰው መሆን ነው። በዚህም የራሱን ሰው የመሆን ቀጠሮና የነቢያትን ትንቢት እሙን መሆኑን በማገናዘብ አረጋግጠዋል።

፫. «ያ ቃል ቀዳማዊ ነው። ያ ቃል በእግዚአብሔር አብ ዘንድ ነበረ። ያ ቃል እግዚአብሔር ነው። ሁሉ በእርሱ ሆነ ከሆነውም አንዳች ስንኳን ያለ እርሱ አልሆነም። ቃልም ሥጋ ሆነ ፀጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ አደረ» (ዮሐ.፩፥፩–፫ እና ቁ.፲፬) ያለውን በማስተዋል ተመልከት። ሰውን ለማዳን ሰው የሆነው ከሁሉ በፊት በቅድምና የነበረው አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድ ነው። የአብና የመንፈስ ቅዱስ ቃላቸው ስለሆነ ዓለም የተፈጠረው በእርሱ ቃልነት በመሆኑ ሁሉ በእርሱ ተፈጠረ አለ ወንጌላዊ ሁሉ በእርሱ ከተፈጠረም አካላዊ ቃል ወልድ አምላክ መሆኑን ያሳየናል። ሕይወትም በእርሱ ዘንድ ስለነበረች ለሰው ሕይወት ለመሆንና ሕይወት ለመስጠት ሰው ሆነ፣ ሰውም ስለሆነ ፍጡር ነው ማለት አይደለም። እርሱ የፈጠረውን ሥጋ ከዲያብሎስ ግዛት ነፃ ለማውጣት የፈጠረውን ሥጋ ተዋሕዶ በሥጋ ተገለጠ እንጂ፣ ፍጡር አይደለም። ሰውን ለማዳን ሰው በሆነው በባሕርይ አምላክ በአካላዊ ቃል በእግዚአብሔር ወልድ ላይ ከዚህ የተለየ አመለካከትና ትርጉም የሚሰጥ ከአለ ጥናት የጎደለውና ሰይጣናዊ ትርጉም ነው።

፬. ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «እነሱም አባቶችን ናቸው ከእነሱ ክርስቶስ በሥጋ ተወለደ። እርሱም ከሁሉ በላይ ሆኖ ለዘለዓለም የተባረከ አምላክ ነው» በማለት (ሮሜ.፱፥፭) ስለ ክርስቶስ አምላክነትና ሰው መሆን በግልፅ ጽፎአል።

፭. ወንጌላዊ ዮሐንስም በመልእክቱ «የእግዚአብሔር ልጅ እንዲመጣ እናውቃለን፣ እርሱም እውነተኛ አምላክና የዘለዓለም ሕይወት ነው» (፩ዮሐ.፭፥፳፤ ራእ. ፩፥፲፯–፲፰፤ ፳፪፥፲፪፤ ዮሐ.፫፥፲፫፤ ፭፥፳፯–፳፯) እነዚህን ጥቅሶች በማስተዋል ተመልከት። የእግዚአብሔር ወልድ የክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት የሚመሰክሩ ምስክሮች ናቸው። ለእግዚአብሔር ወልድ ሰው መሆን ከነቢያትና ከሐዋርያት የበለጠ ምሥክር የለም። እኛም ከዲያብሎስ ቁራኝነት ነፃ የወጣነውና ሕይወት የአገኘነው ሰው በሆነው አምላክ በአብ አካላዊ ቃል በእግዚአብሔር ወልድ መሆኑን እናምናለን እንመሰክራለንም። ስለዚህም ነው ቅዱስ ጳውሎስ በሐዋ. ሥራ ፳፥፳፰ «በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቋት ዘንድ ተጠንቀቁ ያለው» ምክንያቱም የክርስቶስን አምላክነት የሚክዱ ዘባቾች እንደሚመጡ ያውቅ ነበርና ነው። ሐዋርያው ግን ክርስቶስ ማን እንደሆነ በውል ያውቅ ስለነበር በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ጠብቁ አለ፣ አብና መንፈስ ቅዱስ በተለየ አካላቸው ሰው ስለአልሆኑ ደም የላቸውም በዚህ ጥቅስ እግዚአብሔር ተብሎ የተጠራው በተለየ አካሉ ከባሕርይ አባቱ ከአብ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ሳይለይ በዕሪና (በአንድነት) እንዳለ የሰውን ነፍስና ሥጋ ተዋሕዶ ሰው ሁኖ የታየ በተለየ አካሉ እግዚአብሔር ወልድ ነው። «እርሱም ራሱ ፊተኛውና መጨረሻው ሕያውም እኔ ነኝ ሞቼም ነበርሁ እነሆም ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ድረስ ሕያው ነኝ የሞትና የሲኦል መክፈቻም አለኝ» ሲል ቀዳማዊና ደኀራዊ ዘለዓለማዊ አምላክና በሞትና በሕይወት ሥልጣን ያለው እርሱ ብቻ መሆኑን በግልፅ ተናግሮአል። (ራእ.፩፥፲፯–፲፰፤ ፩ጴጥ.፫፥፲፰–፲፱፤ ሮሜ. ፲፥፱፤ ራእ.፳፪፥፲፪)።

እግዚአብሔር አብም ስለ ባሕርይ ልጁ ስለ እግዚአብሔር ወልድ አምላክነትና ሰው መሆን እንዲህ በማለት መስክሮአል። በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው እርሱን ስሙት (ማቴ.፫፥፲፯–፲፰፤ ፲፯፥፭፤ ሉቃ.፫፥፳፩–፳፪፤ ኢሳ. ፷፫፥፭፤ ፳፰፥፲፮፤ ፵፥፭)።

ሐ. እግዚአብሔር ወልድ ስለ ራሱ የባሕርይ አምላክነትና ሰው መሆን የገለጸው ትምህርት:-

፩. «እግዚአብሔር አባታችሁ ከሆነ በወደዳችሁኝም ነበር እኔ ከእግዚአብሔር ወጥቼ መጥቻለሁና እርሱ ላከኝ እንጂ ከእራሴ አልመጣሁም» በማለት ከአብ አካል ዘእምአካል ባሕርይ ዘእምባሕርይ ቅድመ ዓለም እንደተወለደና በፈቃድም ከባሕርይ አባቱ ከአብና ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አንድ ስለሆኑ ሰውን ከዲያብሎስ ቁራኝነት ነፃ ለማውጣት ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ ሰው ሆኖ በሚያስ ትምርበት ጊዜ ለአይሁድ ማንነቱን በግልፅ ተናግሮአል። (ዮሐ.፰፥፵፪፤ ፲፮፥፳፰)።

፪. «እኔ ለእውነት ልመሰክር ለዚህ ተወልጃለሁ፣ ስለዚህም ወደ ዓለም መጥቻለሁ ከእውነት የሆነ ሁሉ ድምጼን ይሰማል» በማለት ቅድመ ዓለም ከአብ ያለ እናት፣ ድኅረ ዓለም ከቅድስት ድንግል ማርያም ያለ አባት መወለዱን በመግለጽ ሰውን ለማዳን ሰው የሆነ አምላክ መሆኑን ሰማያዊ ልደቱንና ምድራዊ ልደቱን እርሱ ራሱ በጲላጦስ ፊት ተናግሮአል። ዮሐ.፲፰፥፴፯፤ ፲፥፴፮–፴፰፤ ሉቃ. ፪፥፵፱ ወዘተ.

፫. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዓይኑን ያበራለትን እውር አግኝቶ አንተ በእግዚአብሔር ልጅ ታምናለህን አለው። እርሱም አምንበት ዘንድ እርሱ ማነው? አለው። ኢየሱስም ከአንተ ጋር የሚነጋገረው ነው በማለት ከእግዚአብሔር የሆነ የእግዚአብሔር ልጅነቱን ዓይኑን ለአበራለት ዕውር አስረድቶአል (ዮሐ.፱፥፴፭–፴፯)። እንዲሁም በጸሎተ ኅሙስ በአደረገው ጸሎት «አሁንም አባት ሆይ ዓለም ሳይፈጠር በአንተ ዘንድ በነበረኝ ክብር አንተ በራስህ ዘንድ አክብረኝ» ሲል ቀዳማዊነቱንና ከአብ ጋር በህልውናና በክብር አንድ መሆኑን ሥጋ ለብሶ ሳለ በአደረገው ጸሎት ቀዳማዊ አምላክነቱን ገልጾአል። (ዮሐ.፲፯፥፭)።

፬. «እውነት እውነት እላችኋለሁ ቃሌን የሚጠብቅ ቢኖር ለዘለዓለም ሞትን አያይም» ቢላቸው:- አይሁድ አብርሃም ሞተ ነቢያትም ሞቱ አንተ ቃሌን የሚጠብቅ ቢኖር ለዘለዓለም ሞትን አይቀምስም ትላለህ? አንተ ከሞተ ከአብርሃምና ከሞቱ ከነቢያት ትበልጣለህን? ቢሉት አባታችሁ አብርሃም ቀኔን ያይ ዘንድ ሐሴት አደረገ አየም ደስም አለው ቢላቸው አይሁድ ገና ሃምሳ ዓመት ያልሆነህ አብርሃምን አይተኸዋልን አሉት ኢየሱስም «እውነት እውነት እላችኋለሁ አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ» ቢላቸው እንደ ሰውነቱ ሊወግሩት ድንጋይ አነሱ እርሱ ግን አምላክ ነውና በመካከላቸው እያአለ ተሠወራቸው (ዮሐ.፰፥፶፩–፶፱)። በዚህ የሕይወት ቃል መሠረት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከፍጥረታት በፊት በቅድምና የነበረና የአብርሃም ፈጣሪ እንደ ነበረና ከአብርሃም ዘር ሥጋና ነፍስን ነስቶ ሰው እንደሆነና በሰውነቱ ስለተገለጠ እንደ አሁኑ ትውልድ አይሁድ የክርስቶስን ማንነት ሊገነዘቡ ባለመቻላቸው ሊወግሩት ድንጋይ አነሱ፣ እርሱ ግን በቅድምና የነበረ የአለና የሚኖር መሆኑን በዚህ የወንጌል መልእክት እራሱን ገልጦ አስረድቶአል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ይህን ስለ አወቀ ነው «ኢየሱስ ክርስቶስ ዘትማልም ወዮም ወከመ ውእቱ እስከ ለዓለም» ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትናና ዛሬ እስከ ዘለዓለምም ያው ነው ያለው (ዕብ. ፲፫፥፰፤ ራእ.፩፥፲፯–፲፰)። በዚህ መልእክት ኢየሱስ ክርስቶስ የነበረና ያለ የሚኖርም የባሕርይ አምላክ እንደሆነ እንገነዘባለን።

ለዚህም ነው እራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ልባችሁ አይታወክ በእግዚአብሔር እመኑ በእኔም ደግሞ እመኑ እውነት እውነት እላችኋለሁ በእኔ የሚያምን የዘለዓለም ሕይወት አለው።» በማለት የዘለዓለም ሕይወት ሰጪና የባሕርይ አምላክ መሆኑን የገለጸው። የጊዜው ትውልድ ይህ አልዋጥልህ ብሎት ነው በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ የተለያየ ትርጉም በመስጠት ልቡ እየታወከ የአለው። እርሱ ግን «በእኔ የተነሣ ልባችሁ አይታወክ በእኔ እመኑ በአብም እመኑ በእኔ የሚያምን የዘለዓለም ሕይወት አለውና» በማለት የሕይወት ጥሪውን ያስተላለፈው። (ዮሐ.፮፥፵፯፤ ፲፬፥፩)።

በዚህ መሠረት ሰውን ለማዳን ሰው የሆነውን የባሕርይ አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስን በአምላክነቱና በአባትነቱ፣ በሕይወትነቱም የማያምን ትውልድ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርስም። «በልጁ የሚያምን የዘለዓለም ሕይወት አለው በልጁ የማያምን ግን የእግዚአብሔር ቁጣ በእርሱ ላይ ይኖራል እንጂ ሕይወትን አያይም» ተብሎ የተጻፈው (ዮሐ.፫፥፴፮) ተመልከት።

የሕይወትና የክብር ባለቤት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእርሱን ማንነት የምናውቅበት አስተዋይ ልቡና ይስጠን አሜን። ✣


www.ethiopianorthodox.org

እኔም ወጣት ነበርኩ።

# እኔም ወጣት ነበርኩ

የዛሬው እንግዳችን ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ናቸው። ዘጠና አንድ ዓመታቸውን ፈጽመው ዘጠና ሁለተኛቸውን ይዘዋል። ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ዕድሜአቸውን በሙሉ ያሳለፉት በመማር በማስተማርና ቤተክርስቲያንን በማገልገል ነው። የዲቁና ማዕረግ ከተቀበሉ ጀምሮ እስከ ዛሬ ለ፹ ዓመታት ያህል ቤተክርስቲያናቸውን በቅንነትና በትጋት ያገለገሉና አሁንም በማገልገል ላይ ያሉ የቤተክርስቲያናችን ቅርስ ናቸው። የሚገርመው ብፁዕነታቸው ዛሬም ጉልበታቸው ብርቱ ከመሆኑም በላይ ያለ ምንም ችግር ማስተማር፣ መቀደስ፣ ማንበብ መቻላቸው ነው።

ልናነጋግራቸው በሄድን ጊዜ የተቀበሉን በደስታና በአባታዊ ስሜት ነበር። የመጣንበትን ዓላማ ከነገርናቸው በኋላ በስሜት ተመስጠው «ልጆቼ እናንተን የጠራችሁ መንፈስ ቅዱስ ነው ከሞትን በኋላ፣ እንደዚህ ነበር፣ እንደዛ ነው፤ ማለቱ ምን ዋጋ አለው?» ነበር ያሉን። የብፁዕ አቡነ ሚካኤል ታሪክና መንፈሳዊ የሕይወት ጉዞ ረዥም ብቻ ሳይሆን ተሰምቶና ተነገር የማይጠገብም ጭምር ነው። ካለን ውስን ቦታ የተነሳ ግን ያቀረብነው ጨምቀንና ቆንጥረን ነው። እንደዛም ሁና አንባቢዎቻችን ከብፁዕነታቸው ቃለ ምልልስ በቂ ትምህርትና መመሪያ ታገኛላችሁ የሚል እምነት አለን። መልካም ንባብ።



ፈለገ ጥበብ – ብፁዕ አባታችን የትና መች እንደተወለዱና ስለ ልጅነት ጊዜ እድገትዎ ቢገልጹልን?

ብፁዕ አቡነ ሚካኤል – በሰሜን ጐንደር ሳንገ ቆላ ወገራ ልዩ ስሙ አየር በአታ ማርያም ከሚባል ሥፍራ ታኅሣሥ ፰ ቀን ማታ (የእመቤታችን ዋዜማ) ፲፱፻፲፩ ዓ.ም ነው የተወለድኩት። የስዕለት ልጅ ነኝ። አባቴ ገብረእግዚአብሔር እናቴ አምባይቱ መርሻ ይባላሉ። እናቴ የባላባት ልጅ ናቸው። አብዛኛው ትምህርቴን የተማርኩት ከዛው ከተወለድኩበት አካባቢ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ነው፤ መምህሬ አለቃ ተካልኝ የሚባሉ የታወቁ ሊቅ ነበሩ፤ ከግብፃዊው ከአቡነ ማቴዎስ ዘንድ በ፲፪ ዓመቴ ዲቁና ተቀበልኩኝ። ከሙዳሴ ማርያም ጀምሮ ዜማው፣ ጾመ ድጓው፣ አቋቋሙ መስተጋቡኡ ከሳቸው ነው የተማርኩት። በ፲፰ ዓመቴ መነኮስኩ፤ ፳፪ ዓመት ሲሞላኝ አሁንም ከግብፃዊው አቡነ ቄርሎስ እጅ ቅስና ተቀበልኩኝ።

ፈለገ ጥበብ – በዛ ዕድሜዎ እንዴት መነኮሱ?

ብፁዕ አቡነ ሚካኤል – መንፈስ ቅዱስ ነው አነሳስቶ የወሰደኝ፣ አብረንታንት (ዋልድባ) ነው የመነኮስኩት፤ አንድ ጓደኛ ነበረኝ በወልቃይት ጠገዴ በኩል አድርገን ነበር የመጣነው። እዛ ስንደርስ ሕፃናቱ መላእክት መስለው ሲቀድሱ ስናይ ዛሬ ካልመነኮስን አልናቸው። የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ ነው። እነርሱ ግን እናንተ አሁን ሕፃናት ናችሁ አናመነኩስም አሉን። እንግዲያውስ አባ ጣዕመክርስቶስ ዘንድ እንሄዳለን ስንላቸው ይሄዱብናል ብለው እመነ

## ቤተክርስቲያንን ከ፸ ዓመታት በላይ ያገለገሉ አባት

ኮሱን። ከዛ እዛ ዋልድባ አካባቢ ዳልሻ ኪዳነ ምሕረት የሚባል ሌላ ገዳም አለ፤ መመንኮሳችንን ሲሰሙ ጊዜ ወደኛ ኑ ብለው ወሰዱን። ገዳሙ ሀብታም ነው፤ ብቻ ወባ አለበት። ዳልሻ ኪዳነ ምሕረት እያለን ዳባት ድረስ እየወጣን እንቀድስ ጀመር። ያኔ ባላባ ቶች መነኮሳትን በጣም ይወዳሉ። ያም ያም እየመጣ ያለብሰናል፤ ይሸልመናል።

ፈለገ ጥበብ – ከዛስ የት ነበር የሄዱት?

ብፁዕ አቡነ ሚካኤል – ከዛማ ቅዳሴ ልማር ወደ ደብረ አባይ ሄድኩኝ፤ እዛም መንፈስ ቅዱስ ነው የወሰደኝ። ታድያ ወደ ደብረ አባይ ለመሄድ ስነሳ የነበርኩበት ገዳም



አበምኔት በዘበኛ አስያዙኝ። አበምኔቱ መምህር ገብረ ሥላሴ ይባላሉ። የጐጃም ተወላጅ ናቸው የታወቁ ሊቅ ነበሩ። በኋላ ሰቋር ገዳም የሚባል አለ፤ ያኔ በዘጠኝ ደወል የተከፋፈለ ነበር። (ጳጳስ ከሆንኩ በኋላ የአንድነት ገዳም አድርጌዋለሁ) ወደዛ መሄዴ ነው አልኩና በጠለምት በኩል አድርጌ በአብረንታንት ተሻግሬ ደብረ አባይ ገባሁ። ደብረ አባይ ከዋናው ምስክር የኔታ ገብረኪዳን ዘንድ ቅዳሴ መማሬን ቀጠልኩ፤ ቢሆንም ኪዳነ ምሕረቶች መጡና የቅዳሴ ትምህርቴን አቋርጠው መልሰው ይዘውኝ ሄዱ። እዛ ዳልሽ ኪዳነ ምሕረት የአበምኔቱ ተከታይ ሆኜ ስቀመጥ በ፲፱፻፳፭ ዓ.ም ይመስለኛል ልዕልት ዘነበወርቅ ሞቱ ተባለና አበምኔቱ ጃንሆይን እግዚአብሔር ያጥናዎት ለማለት ወደ አዲስ አበባ ሲመጡ እኔም ተከትየ መጣሁና እዚሁ ቀረሁ።

ፈለገ ጥበብ – የቅዳሴው ትምህርት በዚሁ ተቋረጠ ማለት ነው?

ብፁዕ አቡነ ሚካኤል – ምን ይቋረጣል እግዚአብሔር ለእሱ አዘጋጅቶኝ የለ? እዚህ ስመጣ የደብረ አባይ የቅዳሴ ምስክር የኔታ



ገብረኪዳን በአታ መጥተው ሲያስተምሩ አገኘሁዋቸው። አንድ ቀን ስንገናኝ «አንተ ለምን አትማርም የመነኩሴ ዘዋሪ» ሲሉኝ ጊዜ ገባሁ። ቅዳሴውን አጠናቅቄ አስመስክሬ የሳቸው ረዳት ሁኜ ማስተማር ጀመርኩ። በዚህ ላይ እንዳለሁ ኢጣሊያ ሀገራችንን ወረረ። በዚህን ጊዜ አቡነ ፊልጶስ ያኔ ሊቀ ሊቃውንት ነበሩ ማይጨው ከኛ ጋር ትዘምታለህ ብለው እኔና ሌላ መነኩሴ አብረን ወደማይጨው ዘመትን።

በማይጨው ዘመቻ ብዙ ፈተና ነው የደረሰብን፣ ጃንሆይም ሕይወቴን እዚህ አጠፋታለሁ ብለው ነበር። መኳንንቱ፣ ሹማምንቱ ሊቃውንቱ ናቸው አውግዘው ለምነው ሕዝቡን በመርዝ ከምናስጨርሰው ቆስ ብለን እንዋጋለን ብለው የተመለስነው።

ፈለገ ጥበብ – ብፁዕ አባታችን ወደ ልጅነት ጊዜዎ እንመልስዎትና የቆሎ ተማሪ ሳሉ ምን ዓይነት ባሕርይ ነበርዎት ማለት ዝምተኛ፣ ተጫዋች፣ ወዘተ?

ብፁዕ አቡነ ሚካኤል – ሕፃን ሳለሁ ሰው ሁሉ ይሻኝ ነበር፣ እንዳው መልኬ ጥሩ ነበር ይባላል። የመነኮስኩ ጊዜ እናቴ የሞትኩ ያክል ፊትዋን ነጭታለች። በልጅነቴ በፈረስ፣ በበቅሎ፣ መሄድን እወድ ነበር። አሁን ድረስ ደስ ይለኛል። ዋናም እወዳለሁ። ከዚህ በተረፈ እንደ ሌላው ተማሪ ለምኜ አላውቅም እኔና ውሻ እንተዋወቅም፣ በልጅነቴ የተማርኩት ከናት አባቴ ቤት ሁኜ ነው። በኋላም ደብረ አባይ ስማር፣ ገዳሙ ነበር የሚረዳኝ፣ ቅኔ ስማር ግን መስፍን የሚባል የሸዋ ሰው ነበር ቅኔ ዘራፊ ነው ዜማ ግን አያውቅም። እሱ ነበር እየለመነ የሚያበላኝ።

ፈለገ ጥበብ – በአምስቱ ዓመት የጠላት ወረራ ወቅት እርስዎ የት ነበሩ?

ብፁዕ አቡነ ሚካኤል – ከማይጨው ስንመለስ እኔ ላስታ ላይ ታምሜ ቀረሁ፤ እንደ ተሻለኝ ወደ አዲስ አበባ ልመጣ አስቤ ነበር። አንድ ባሕታዊ መጣና ወደ አዲስ አበባ አትሂድ አርፈህ ተቀመጥ እህል ውሀ እዚህ ነው አለኝና ቅዳሴ እያስተማርኩ ተቀመጥኩ። ቄሱም ዲያቆኑም ከበበኝ። ታድያ በአንድ በኩል ቅዳሴ እያስተማርኩ በሌላ በኩል እኔ ራሴ ቅኔ እማር ጀመር። የኔታ ወልደየስ የተባሉ የአገባብ መምህር ነበሩ። ጋፋት ማርያም ትባላለች የጐንደሩ አቡነ ሚካኤልም እዛ ነው የተማሩት፤ እኔም እዛው የኔታ ወልደየስ ከተባሉ የአገባብ መምህር፤ ቅኔ ተቀኘሁ። በቅኔ ብዙ ደከሜአለሁ። በኋላ መጽሐፍተ ሐዲሳትንና ባሕረ ሐሳብንም ተምሬአለሁ።

ፈለገ ጠበብ – ከነፃነት በኋላስ?

ብፁዕ አቡነ ሚካኤል – ጠላት ሲባረር ሀገሬው አስገድዶኝ እዛው ላስታ ብልባላ ጊዮርጊስ ከተባለ ትልቅ ደብር ተሹሜ ነበር። ጃንሆይ ሲመለሱ በርካታ ደቀመዛሙርት (ተማሪዎቼን) አስከትዩ ወደ አዲስ አበባ ጉዞ ጀመርኩኝ። በኋላ መንገድ ላይ በእግር መሄድ አመቺ ሳይሆን ሲቀር ወደ አዲስ አበባ በመኪና መጣሁ። ስመጣ ወደ ላስታ እመለሳለሁ ብዩ ነበር። እዚሁ እንደ ደረስኩ ግን አቡነ ዮሐንስ (ያኔ ሊቀ ሊቃውንት ገብረ መስቀል) በአታ ቅዳሴ አስትምር አሉኝ። አስተማሪየ የኔታ ገብረኪዳን እዚህ ሦስት ዓመት ካስተማሩ በኋላ ሽማግሌ ስለ ነበሩ ሀገሬ ሄጄ እሞታለሁ ብለው ወደ ደብረ አባይ ተመልሰው ነበር። እኔ በሳቸው ቦታ ሁኜ ለአሥር ዓመት ያህል አስትምሬአለሁ።

በኋላ፣ ከጊዜ ብዛት የጠፋ (የረሳሁት) ነገር ይኖራል፣ ቅዳሴ ብዙ ነገር ብዙ ሐተታ አለው፣ ጭረቱ፣ ድፋቱ፣ ደረቱ፣ መቸም የደብረ አባይ ቅዳሴ ምርጥ ቢሆንም አስቸጋሪ ነውና ብዩ ወደ ደብረ አባይ ሄድኩኝ። ዘመዶቼ ደብረ አባይ መምጣቴን ሲሰሙ በቅሎ ይዘው መጥተው ካልወሰድንህ አሉ። እንደ ምንም ብዩ ሦስት ወር ቆየሁ። ታድያ ያኔ መምህሬ «አንተ ልጅ ቅዳሴ ክፍልህ ነው ይህን ያህል ጊዜ ስትቀመጥ የአዲስ አበባ ወዝ አልወሰደህም» ብለው መረቁኝ። ከሀገሬ ከወጣሁ ፲፬ ዓመት ሆኖኝ ነበር። ወደ ቤቴ ስመለስ እናትና አባቴ መንኩሰው አገኘሁዋቸው። ከቤተሰቦቼ ጋር ፴ ቀናት ያህል ቆይቼ ወደ አዲስ አበባ መጣሁ። እንደ መጣሁ የቅድስት ማርያም አስተዳዳሪ ሆንኩኝ። እዚሁ ከመጣሁ በኋላም አልፎ አልፎ ወደ ጐንደርና ዳልሻ ኪዳነ ምሕረት መመላለሴን አላቋረጥኩም ነበር።

ፈለገ ጥበብ – የቅድስት ማርያም ቆይታዎ እንዴት ነበር?

ብፁዕ አቡነ ሚካኤል – ቅድስት ማርያም እያለሁ ከአስተዳዳሪነት በተጨማሪ በአቡነ ቀሲስነትም እሠራ ነበር። በዛው ላይ ቅዳሴ አስትምራለሁ፤ ያኔ ታዲያ፣ ቄሱም ዲያቆኑም አስገድጄ ነበር የማበጥረው፤ እን ዳው ሰነፉ ጉበዙ በራእይ ይታየኝ ነበር። ማንንም ዝም ብሎ አይቀድስም። አንተ ትችላለህ፤ አንተ ይቀርሃል ተማር፤ መልስህ ከልስህ ና እለዋለሁ።

ፈለገ ጥበብ – የችሎታ ጉዳይ ከተነሳ በእናንተ ጊዜ ቅስናና ዲቁና ስትሰጡ ፈተናው (መመዘኛው) እንዴት ነበር?

ብፁዕ አቡነ ሚካኤል – ፈተና በሚገባ አለ። አምስቱ አዕማደ ምሥጢር፣ ቅዳሴው፣ ኪዳናቱን፣ ጸሎተ ሱን፣ ግብረ ሐዋርያውን ሁሉን አስነብበን ነው እንጂ እንደ ዛሬው ማግበስበስ የለም። ዛሬ ፈተናው ብር ብቻ ነው። አቡነ ባስልዮስ ገንዘብ እንዳትቀበሉ እያሉ በጣም ይቆጣጠሩን ነበር። እኛም ራሳችን ዲቁና፣ ቅስና፣ ስንቀበል እንደዚሁ ተፈትነን ነው። ለምሳሌ እኛ መነኮሳት ከትምህርቱ በተጨማሪ ገዳም መኖራችንን አስመስክረን ተመርምረን ነው የተቀ በልነው።

ፈለገ ጥበብ – ወደ ኋላ እንመልስዎትና በቅድስት ማርያም ለምን ያህል ጊዜ አገለገሉ? ከዛ በኋላስ የት ነው የተመደቡት?

ብፁዕ አቡነ ሚካኤል – ቅድስት ማርያም ለስድስት ዓመታት ያህል ነው የሠራሁት፤ ከዛ በኋላ ወደ መንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል ሄድኩኝ። እዛም ለአራት ዓመታት ያህል አገለግያለሁ። የአለቃ ቢሮውን ጨምሮ ዕቃቤቱ ሌላው እኔ ነኝ ያሠራሁት። በዛ ላይ ጃንሆይን አስፈቅጄ ቤተክርስቲያኑን አሳድሼዋለሁ። ከመንበረ መንግሥት በኋላ ወደ ጵጵስና ነው የሄድኩት፤ ጳጳስ የሆንኩት በ፲፱፻፶፪ ዓ.ም ሐምሌ ወር ውስጥ ነው።

ፈለገ ጥበብ – በእናንተ ጊዜ የነበረው የጵጵስና አመራረጥ ምን ይመስላል?

ብፁዕ አቡነ ሚካኤል – በኛ ጊዜ ምርጫው በሁለት ነገር ላይ የተመረኮዘ ነበር፤ በአገልግሎትና በትምህርት። ያኔ የተመረጥነው በድምፅ ነው። አድባራቱ ሁሉ ተሰብስበው ድምፅ ሰጥተው ነው የሾሙን። በእርግጥ ከምርጫው ከመኳንንቱም ከመሳፍንቱም ይጨመሩበታል፤ ያኔ ለውድድር የቀረብነው አሥራ አራት ነበርን፣ ሰባቱ ሲቀሩ ሰባት አለፍን።

ፈለገ ጥበብ – ጳጳስ ከሆኑ በኋላ ሥራ የጀመሩት የት ነው?

ብፁዕ አቡነ ሚካኤል – ወደ ቦረና ነው የሄድኩት፤ እዛም ብዙ ሠርቻለሁ። ሁለት ሺሕ ያህል ሰዎችን አጥምቄአለሁ፤ ወልደ ገብርኤል፣ ወለተሚካኤል ብሎ ማጥመቅ ብቻ ሳይሆን ከሀገሬው ተወላጆች ብዙዎ ችን አስትምሬ ለዲቁናና ለቅስና ማዕረግ አድርሻለሁ። ጳጳስ ሆኜም ቢሆን ቅዳሴ ማስተማሬን አላቋረጥኩም ነበር። ከዛ በፊት በአገልጋይ እጦት ተዘግተው የነበሩ በርካታ አብያተ ክርስቲያናት ከማስከፈቴም በላይ አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናትን አሠርቻለሁ። በዛው ላይ ከዚህ ከአዲስ አበባ ከሥላሴ ሠልጥነው የወጡትን መምህራን መርጬ በመውሰድ ሕዝቡ እንዲማር አድርጌአለሁ።

አስታውሳለሁ በወቅቱ ሚሲዮናች ሥራችን አዲስ ሆኖባቸው ነው መሰለኝ፣ ኦርቶዶክስም ማስተማር ጀመረች፤ ይሉ ነበር። ከቦረና በኋላ አርሲ ለአንድ ዓመት ተኩል ያህል አገልግያለሁ። ከአርሲ በኋላ ወደ ኤርትራ ነበር የተመደብኩት። ኤርትራ ከ፲፱፻፶፱ እስከ ፲፱፻፷፭ ዓ.ም ሥራ ላይ ቆይቻለሁ።

ፈለገ ጥበብ – በኤርትራ ለዚህን ያህል ረዥም ጊዜ ያገለገሉ ጳጳስ እርስዎ ብቻ ነዎት ይባላል፤ ምክንያቱ ምንድነው?

ብፁዕ አቡነ ሚካኤል – ዋናው ምክንያት ከሕዝቡ ጋር ተግባብቶ በመሥራቴ ይመስለኛል። ከሁሉ በላይ ደግሞ የአቅሜን ያህል ሥራ በመሥራቴ ነው። እኔ እስመራ ስሄድ መንበረ ጵጵስና፣ ቢሮ፣ አልነበረም። መንበረ ጵጵስናው፣ ጽ/ቤቱ ቢሮው፣



www.ethiopianorthodox.org

የስብከተ ወንጌል አዳራሹ ያሠራሁት እኔ ነኝ። እኔ ኤርትራ ተመድቤ ስሄድ በአሥመራ ስድስት አብያተ ክርስቲያናት ብቻ ነበሩ። አሁን ግን ከሃያ በላይ ደርሰዋል። በመሠረቱ የኤርትራ ሰው የውጭ ሰው አይወድም፤ እኔ ግን ሥራዬን የምሠራው ከአስተዳዳሪዎቹ ከሀገር ሽማግሌዎች ጋር በመመካከር ስለነበር ችግር አላጋጠመኝም። በዛው ላይ የተጣሉትን አስታርቃለሁ፤ አቤቱታ ሲቀርብልኝ በአፋጣኝ ውሳኔ እሰጣለሁ። ከጠቅላይ ቤተክህነት መልስ የሚያስፈልገው ጉዳይ

እንደሆነ አላወቅኩም፤ ለካ ሽፍቶች (በረኸኞች) ናቸው። «ይቀመጡ ይቀመጡ አባቴ» አሉኝ። ያኔ ሊገድሉኝ ይችሉ ነበር። ግን እነርሱ ምንም አላሉኝም። ምናልባት ጳጳስ ብንገድል ሕዝቡ ይቆጣል ብለው ይሆናል፤ እኔም ብሆን ከፖለቲካው አልገባም፤ ሕዝቡም ይወደኛል፤ ያን ዕለት አጠገቤ አንዱን እስላም ሚኒስትር አንተ የንጉሡ ደጋፊ ነህ ብለው ገደሉት። ሌሎችንም ገድ ለዋል። እኔን ግን ሌላ ጊዜም ቢሆን አይተናኮሉኝም። እንዲያውም ወደ ቤተክርስቲያን ብቻዬን ነው



እንኳን ቢሆን ነገሩ እንደሚጎተት ስለማውቅ እዛው በራሴ ነበር የምወስነው። ሕዝቡ ደግሞ የዚህ ዓይነት ቀልጣፋ ውሳኔና መፍትሔ የሚሰጠውን ይፈልጋል።

ፈለገ ጥበብ — በኤርትራ ቆይታዎ ያጋጠመዎት የማይረሱት አጋጣሚ ይኖራል?

ብፁዕ አቡነ ሚካኤል — የቤቴ ጠባቂ ኤርትራዊ ነበር፤ አንድ ቀን እርሱ ነው የጠቆማቸው ይባላል በረኸኞቹ ቤቴ ገቡ። ስመጣ አርዊብርቴንም መስቀሉቼንም ሰብስበው፤ ታላቅ እህቴ እኔ ጋር ነበረች እርስዋንም ጥላሁን የሚባልም ነበር እነር ሱንም አስረዋል። ስገባ ነገሩ ምን ድነው ብዬ ከዘራዬን አንስቼ ልማታ፤ እኔ እነማን

ሌሊት የምሄደው። ወደ ሌላ ቦታም እንደ ዚሁ። ታድያ እኔ ለራሴ እንደዚህ ባደርግም የመንግሥት ባለሥልጣ ናትን እመክራቸው ነበር።

ፈለገ ጥበብ — በአሁኑ ቤትዎ ሳሎን ጃንሆይ ኒሻን ይሁን ሌላ ሲሸልምዎት የሚያሳይ ትልቅ ፎቶግራፍ ይታያል ሽልማቱ ምንድነው? ቦታውስ የት ነበር?

ብፁዕ አቡነ ሚካኤል — ጥሩ ጥያቄ ነው፤ ያኔ አሥመራ ነበርኩኝ፤ ከኔ ጋር የተሾሙት እነ አቡነ አብርሃም እነ አቡነ ዮሴፍ፤ አቡነ ሰላማ ሁሉ ሊቀ ጳጳስ ሲባሉ እኔ ሊቀ ጳጳስ አልተባልኩም ነበር። ምክንያቱም አቡነ አትናትዮስ እዛ አሥመራ ነበሩ፤

እሳቸው በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የሊቀ ጵጵስና ማዕርግ የተሰጣቸው አባት ናቸው። ማስተዳደሩን ከሕዝቡ ጋር ተስማምተው መኖሩን ግን አልቻሉበትም ነበር። ስለዚህ እሳቸው እያሉ ሊቀ ጳጳስ ብባል ፖለቲካው ሊበላሽ ሆነ። ወደ ሌላ ቦታ እንዳልዛወር ደግሞ ጃንሆይ ሀገሩን ደህና አድርገው ይዘውታል፤ ከሕዝቡ ጋር ተስማምተዋል፤ ከቤተክርስቲያን የማይለዩ በጠባያቸውም በአስተዳደራቸውም ጥሩ ስለሆኑ ከዚያ እንዲለዩ አንፈልግም አሉ። በመጨረሻ የሊቀ ጳጳስ ማዕርግ ይሰጣቸው ግን ሹመቱ በአዋጅ (በይፋ) እንዳይነገር ተባለ። ፎቶግራፉ የሚያሳየው በታላቁ የታችኛው ቤተ መንግሥት የሊቀ ጵጵስና ማዕርግ ሲሸልሙኝ ነው። አቡነ አትናቴዎስ ከሞቱ በኋላ ነው በይፋ የኤርትራ ሊቀ ጳጳስ የተባልኩኝ።

ፈለገ ጥበብ — ብፁዕነትዎ በተማሪነት፣ በመምህርነትና በጵጵስና ለብዙ ጊዜ ያገለገሉ በመሆንዎ ስለ አብነት ት/ቤቶቻችን ጠለቅ ያለ ግንዛቤ አለዎት፤ በአሁኑ ጊዜ እየተዳከሙ የመጡትን የአብነት ት/ቤቶ ቻችንን ጨርሰው ከመጥፋታቸው በፊት ምን መደረግ አለበት ይላሉ?

ብፁዕ አቡነ ሚካኤል — እኔ ከቅዱስ ፓትርያርኩ ፊት ሳይቀር ሁል ጊዜ የምለው የብሉይ፤ የሐዲሳት፤ የአቋቋም፣ የቅዳሴ፣ የዜማ፤ የቅኔ የሁሉም መምህራን ቅርሶቻችን ስለሆኑ በቂ እንክብካቤ ሊደረግላቸው ይገባል ነው። በቂ ደመወዝ ይሰጣቸው ነው የምለው። የሚማሩት ደቀመዛ ሙርትም ቢሆን በጥንቃቄ እየተመረጡ ይማሩ፤ የጸዋትወ ዜማ፣ የቅ ዳሴው የቅኔው፣ በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ባህል እንዳይፋለስ በጥንቃቄ ሊያዝ ይገባል ባይ ነኝ። በውጭ ሀገር እገሌ ምሁር ነው እገሌ ሊቅ ነው እየተባለ ሲደነቁ ስሰማ እቀናለሁ። የኛን ሊቃውንት ዛሬ ተንከባክበን ካልያዝናቸው ነገ ቤተክርስ ቲያናችን አትኖርም።

መቼም እኔ ከመናገር ወደኋላ ብየ አላውቅም፤ ብቻ አሁን ሰውነቴ እየደከመ መጣ፤ በአክሱም፣ በጐንደር፤ በጐጃም፣ በተምቤን የነበሩ ሊቃውንት እኮ እየጠፉ ነው፤ አንድ ጊዜ ያጋጠመኝን ልንገራችሁ፣ ባሕረ ሐሳብ ውስጥ የፀሐይ፣ የጨረቃ የምንለው አቆጣጠር አለ፤ ታድያ አንድ ጊዜ ጐንደር ሄድኩኝና እስቲ ልጠይቅ ብል የሚመልስልኝ ጠፋ። መምህር ወልደሰማያት የሚባሉ ነበሩ ሞተዋል ተባለ። በሳቸው ቦታ የተተካ የለም። ጐንደር ብዙ ሊቃውንት የምታፈራ ሀገር ነበረች። የበቁ፣ የመጠቁ ሊቃውንት በነበሩባት ሀገር እንደዚህ ሆኖ መታየቱ ያሳዝናል።

ፈለገ ጥበብ — ብፁዕነትዎ እስከ አሁን ካዩዋቸው ወይም በዝና ከሚያውቋቸው ገዳማት ይበልጥ የሚያደንቋቸው ካሉ ቢነግሩን?

ብፁዕ አቡነ ሚካኤል — ገዳማቶቻችን ሁሉም የሚደነቁ ናቸው፤ የትኛው ከየትኛው ይመረጣል ብላ ችሁ ነው? ለምሳሌ ከተባልኩኝ ግን ደብረ አባይ ጥሩ ነው፤ የትምህርት ቅርሳችን ባህላችን አሟልቶ የያዘ ነው። የታወቁ ሊቃውንት መምህራን፣ የነበሩበት፣ የቅኔ፣ የዜማ፣ የመጽሐፍ፣ የቅዳሴ፣ በተለይ የተጣራ የቅዳሴ ምስክር ደብረ አባይ ነው።

ከዛ ቀጥሎ የማደንቀው የምንኩስና፣ የብህትውና ሕይወት አሟልቶ የያዘው አብረ ንታንት (ዋልድባ) ገዳምን ነው። ከአቡነ ዮሐንስ ጀምሮ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የበቁ ባህታውያን የነበሩበት ታላቅ ገዳም ነው፤ ደብረ ዳሞም ትልቅ የተከበረ ገዳም ነው፤ ደብረ በንኩል እኔ ባላየውም ጥሩ የአንድነት ገዳም መሆኑን ሰምቻለሁ።

ፈለገ ጥበብ — በአሁኑ ጊዜ ያሉ መነኮሳት የጥንቱን ሥርዓት እየተው፣ በየገዳማቱ የሚገባቸውን አገልግሎትና ተመክሮ ሳይፈጽሙ ወደ ከተማዎች ሲፈልሱ ይታያሉ፤ በዚህ ላይ ያለዎት አስተያየት ከነመፍትሔው ቢጠቁሙን?

ብፁዕ አቡነ ሚካኤል — እንደ ሕጉ ከሆነ አንድ መነኩሴ ከነበረበት ገዳም ወደሌላ መዛወር የሚችለው ትምህርት ለመማር፣ ተጨማሪ ዕው ቀት ለመቅሰም መሆን አለበት። የዛሬው ግን መነኩሶ ወደ ትምህርት በመ ገስገስ ፈንታ ወደ ገንዘብ መሮጥ ሆነ። ስለዚህ ጠበቅ ያለ ቁጥጥር ያስፈ ልጋል። ትምህርት ለሚፈልገው ወደ ትምህርት፣ ካልፈለገ ግን ከገዳሙ መውጣት የለበትም። ዛሬ እኛ ጳጳሳት የተሸከምነው ሸክም ትልቅ ነው። የዛሬ ጵጵስና አስቸጋሪ ነው፤ ቤተክርስ ቲያናችን ፈተና ላይ ናት፤ በአንድ በኩል ካቶሊኮችና ፕሮቴ ስታንቶች በሌላ በኩል እስላሞች ከበዋታል። መንፈሳዊ ት/ቤቶች በብዛት ተከፍተው ወጣቱ እንዲማር ካልተደረገ ቤተክርስ ቲያናችን መድከሟ አይቀሬ ነው። እኔ ሁል ጊዜ በተደጋጋሚ የምናገረው ነገር አለ፤ እንዳዘንኩ ነው የምኖረው፤ አንድ ቀን እስትምሮ ሰብኮ መሄድ ዋጋ የለውም። ከመሠ ረቱ ነው መጠናከር ያለበት። የአብነት ት/ቤቶቻችን መጠናከር አለባቸው።

ፈለገ ጥበብ — አሁን ያነሱትን የመነኮ ሳትም ሆነ በሌሎች ወሳኝ ጉዳዮች ላይ ቅዱስ ሲኖዶስ ጠበቅ ያለ መመሪያና ሕግ እንዲያወጣ በአባል ነትዎ ያደረጉት ጥረት አለ?

ብፁዕ አቡነ ሚካኤል — አዎን አናገ ራለሁ፣ እንዳውም እኔ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ጊዜ ጀምሮ የቤተክርስቲያናችን ሕገ ደንብ ለማውጣትም ሆነ የወጡት ሕጐችን ለማስፈጸም ቅዱስ ሲኖዶስ ብቻውን በቂ አይደለም እያልኩ ስከራከር ቆይቻለሁ። ከቅዱስ ሲኖዶስ ጋር ምሁራን፣ በምእመናን ዘንድ ተደማጭነት ያላቸው የሕዝብ ተወካዮች፤ በአንድነት ሆነው ተከራክረው ተወያይተው ጨምቀው የሚያወጡት ሃሳብ ነው መሆን ያለበት። በተረፈ አሥራ አምስትና ሃያ ጳጳሳት ብቻችን ሆነን እንዲህ ይሁን ብንል አስቸጋሪ ነው። የኛ ቅርሶች ምእመናን ናቸው፤ ስለዚህ ምእመናንን በፍቅር መያዝ ማስተማር ያስፈልጋል። ድሮ ከላይ ሆኖ ቤተክርስቲያንዋን የሚቆጣጠራት መንግሥት ነበር። የበላይ ጠባቂዋ ጃንሆይ ነበሩ። አሁን ኃላፊነቱ ሁሉ በኛ ላይ ወድቋል፤ ይህንን ኃላፊነት በሚገባ ለመወጣት ከተፈለገ ቤተክርስቲያን ምእመናኗን ምእመናንም ቤተክርስቲያናቸውን ማቀፍ ያስፈልጋቸዋል።

ፈለገ ጥበብ — ስለ ጃንሆይ ካነሱ ዘንድ አንድ ነገር እንጠይቅዎት። አንዳንድ ሰዎች አፄ ኃይለሥላሴ የተለያዩ የሃይማኖት ድርጅቶች በነፃ እንዲንቀሳቀሱ በመፍቀድና ቤተክርስቲያንዋ ራስዋን ትቻል በሚል አስተሳሰብ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እንድትዳከም አድርገዋል ሲሉ ሌሎች ደግሞ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በራስዋ ፓትርያርክ እንድትመራ ከማድረጋ ቸውም በላይ ቤተክርስቲያንዋ እንድታድግ ሁለገብ እገዛ በማበርከት ታላቅ ውለታ ፈጽመዋል ይላሉ። የስዎ ሃሳብ የትኛውን ይደግፋል?

ብፁዕ አቡነ ሚካኤል — መቼም አፄ ኃይለሥላሴ ብዙ ዘመን ነው የገዙት፣ በዚህ ረዥምም ጊዜ በፍርድም በምንም ያዙት ነገር ሊኖር ይችላል። ግን ጃንሆይ እኔ እስከ ማውቃቸው ድረስ ቤተክርስቲያንንና የቤተክ ርስቲያን አባቶችን ያከብሩ ነበር። በዛው ላይ ቤተክርስቲያንን ይቆጣጠሩዋታል ያግዟ ታል። እንዴ? ከነአፄ ቴዎድሮስ ጀምሮ ቤተክ ርስቲያናችን ራስዋን እንድትችል በራስዋ ፓትርያርክ እንድትመራ ሲደረግ የቆየው ጥረት በዘዴ በብልሃትና በጥንቃቄ፣ ተግባር ላይ የዋሉት አፄ ኃይለሥላሴ እኮ ናቸው።

በዛው ላይ ጉርሻ ይሰጣሉ። ብዙ አብያተ ክርስቲያናትም አሠርተዋል። ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል፤ አክሱም ጽዮንን፤ በየክፍለ ሀገሩም ተዟዙረው ሠርተዋል። የጸሉት ሰውም ነበሩ! የኢትዮጵያ ጥንታውያን የብራና መጻሕፍት ለትውልድ እንዲተላለፉና እንዳይጠፉ እያስተረጐሙ በዘመናዊ መልክ እንዲታተሙ ብዙ ጥረዋል። ለቤተክርስቲያን የሚሆን ርስት ጉልት ሰጥተዋል። ባጭሩ ጃንሆይ ለቤተክርስቲያናችን ጠቃሚዋት እንጂ ጉድዋት አልልም።

ፈለገ ጥበብ — በመጨረሻ ለወጣቱ ትውልድ የሚያስተላልፉት አባታዊ መልእ ክት ካለ?

ብፁዕ አቡነ ሚካኤል — ለወጣቱ የምለውማ እንደ እናንተ እየመጣ አባቶችን ይጠይቅ፤ ከአባቶች ይማር በቤተ ክርስቲያን ጉዳይ የዳር ተመልካች አይሁን ነው፤ በሁሉም የቤተክርስቲያን ሥራ መሳተፍ አለበት። ይልቁንስ እኔ መልእክት ማስተላለፍ የምፈልገው ወጣቱን ለሚመሩ ክፍሎች ነው። በሁሉም አህጉረ ስብከቶች እየሄዱ ወጣቱን ማደራጀት ማስተማር መቆጣጠር ያስፈ ልጋል። ወጣቱን መስለው ከወጣቱ መሃከል ውስጥ ለውስጥ የሚሄዱ አሉ። ስለዚህ ቁጥጥርና ክትትል ያስፈልጋል። ሌሎች እኮ ያልቀናውን ቦታ ካቀኑ ካስተማሩ በኋላ ነው እምጣ የሚሉት፤ እኛ ግን ሳናስተምረው እምጣ እንለዋለን። ካልተማረ ይርቀናል። ስለዚህ ከሁሉ በፊት ማስተማር ይቅደም። ለማጠቃለል በወጣቱ ዘንድ እየታዩ ያሉትን ችግሮች ለመፍታት ቅድም እንዳልኩት የጋራ ውይይት ያስፈልጋል።

ፈለገ ጥበብ — ብፁዕ አባታችን አንድ የረሳነው ነጥብ አለ፤ ለዚህ ማዕረግ ከመድረስዎ በፊት ጳጳስ እሆናለሁ የሚል ግምትና ሀሳብ ነበርዎት?

ብፁዕ አቡነ ሚካኤል — እኔ ምን አውቃለሁ ሁሉ የሆነው በእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። ብቻ ልጅ ሳለሁ ሰዎች ርግብ ከራሱ ላይ ስታርፍ አይተናል፤ ይህ ልጅ ከትልቅ ማዕረግ ይደርሳል ሲሉ ትዝ ይለኛል። ደጃዝማች ደስታ ዘውዱ የተባሉ ዘመዳችንም ከኛ ወገን ጳጳስ የሚሆን አለ ይሉ ነበር። እዚሁ በአታ እያለሁም ራእይ አየን የሚሉ ሰዎች ነበሩ።

ፈለገ ጥበብ — እግዚአብሔር እድሜና ጤና ይስጥልን።

ብፁዕ አቡነ ሚካኤል — ተባረኩ ልጆቼ፤ አሜን። ✣



www.ethiopianorthodox.org

# ሥርዓተ ቤተክርስቲያን



ይህ ርእሰ ነገር በምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ተብለው በሥርዓተ ቀኖና ከሚነገሩት ምሥጢራት አንዱ ነው። በቤተ ክርስቲያናችን ግን ምሥጢራት ተብለው የሚነገሩት አምስት ናቸው።

ንስሐ – በአፈጻጸሙ ረገድ ሲታሰብ ምሥጢራዊ ጠባይ ይኑረው እንጂ በትምህርታዊ ገጽታው በዚህ መልክ አይነገርም።

ይሁንና ጉዳዩ ይህን ያህል አከራካሪ ምክንያት ስለማያስከትልና የምሥራቃውያኑም አባባል በእኛ ይትበሃል ውስጥ እየተለመደ ስለመጣ አሁን ለተነሳንበት መሠረተ ሐሳብ አርእስት አድርገን ተጠቅመንበታል። በመሠረቱ እኛ ልንገልጸው የፈለግነው የንስሐ ሕይወት ምንነት በመሆኑ የላይኛውን ሐተታ በማሳጠር ወደ ፍሬ ነገሩ እናመራለን።

ንስሐ በአዲስ ኪዳን ትምህርት ውስጥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም ስለመምጣቱና ሰው ስለ መሆኑ ሥጋም ስለ መልበሱ ከሚነገሩት ዐበይት ምክንያቶች አንዱ ምክንያት መሆኑ ይታወቃል። ስለሆነም «እኔ ኃጢአተኞችን ወደ ንስሐ ልጠራ ነው እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁም» የሚል ተጽፎ እናነባለን (ማቴ.፱፥፲፫)።

ስለዚህ ንስሐ ከአሠርቱ ትእዛዛት አንዱ ሁኖ በሕግ ወይም በትእዛዝ መልክ ባይጻፍም እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ምሕረቱን ርኅራኄውንና ትእግሥቱን በአጠቃላይ ልግሥናውን የገለጸበት የሚገልጽበትም ታላቅ ሥርዓት ነው። በአርእስቱም ከፍ ብሎ እንደ ተገለጸው ጥልቅና ረቂቅ ምሥጢር ነው። ምሥጢርነቱ ወይም ምሥጢራዊነቱ በጥቂቱም ቢሆን ሊያነጋግር የሚችል ነው።

በዓለማዊ ሕግ በደለኛ ስለ ሠራው በደል በሚሰጠው ፍርድ «የቅጣት ማቃለያ» ወይም የፍርድ ማሻሻያ

## ምሥጢረ ንስሐ

ከንብረ እድ ኃይል ልዑል ወልደገሪማ

የሚባሉ አንቀጾች ቢኖሩም ከቅጣት ነፃ የሆነ ምሕረት የለም። አልፎ አልፎ ምሕረት የሚል ድምፅ ቢሰማም በደለኛው ለተወሰኑ ጊዜያት በቅጣት ላይ ከቆየ በኋላ ይሆናል። የእግዚአብሔር ምሕረት ግን ፍጹም ይቅርታ ስለሆነ ፈጽሞ ከዚህ ይለያል። ኃጢአተኛው በኃጢአቱ ምክንያት ያጣውን ሁሉ ያገኛል። ወደ ቀደመ ክብሩና ወደ ቀደመ ሕይወቱ ይመለሳል። ያለፈው ኃጢአቱና በደሉ ሁሉ ይሠረይለታል። ሴሰኛው እንደ ድንግል ይቆጠራል። ፍጹም ይቅርታና ምሕረት ማለትም እንዲህ ነው።

ንስሐ ስንል ለየት ባለ መንገድ ማየት ቢፈለግ ከፍ ብሎ ለተገለጸው የእግዚአብሔር ምሕረትና ርኅራኄ ቁልፍ ወይም መክፈቻ ነው ማለት ይቻላል። ይህ እንዲሆን (የስብከት) መቅድም፤ (መጀመሪያ) መሆኑን በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ እንመለከታለን። (ማቴ.፫፥፪፤ ፬፥፲፯)

የንስሐ ትምህርት በብሉይ ኪዳን ሰፊውን ምዕራፍ ይዞ የሚገኝና ሥርዓትም ሆኖ የሚነገር ነበር፤ በተለይም በትንቢተ ሕዝቅኤል ላይ «ኃጢአተኛውም ከሠራው ኃጢአት ቢመለስ ፍርድንና ቅን ነገርንም ቢያደርግ ነፍሱን ይጠብቃል አስቦ ከሠራው በደል ሁሉ ተመልሶአልና ፈጽሞ በሕይወት ይኖራል እንጂ አይሞትም» በማለት ያሰፈረው ቃል የንስሐ ሕይወትን ምንነት በጉልህ ያስገነዝባል (ሕዝ.፲፰፥፳፯–፳፱)። ንስሐ ማለት መጸጸት፣ መመለስ፣ መሆኑንም ትርጉሙን በቅርብ መረዳት ይቻላል። በዚሁ መጽሐፍ በምዕራፍ ፴፫ በቁጥር ፲፮ ላይ «የሠራው ኃጢአት ሁሉ አይታሰብበትም» ይላል።

በአንቀጸ ንስሐ እንደ ተገለጸው ንስሐ መናዘዝ፣ ኑዛዜ ማድረግ፣ ወይም ኃጢአትን ለአበ ነፍስ (ለካህን) መንገርና ራስን መግለጥ ነው። ነገር ግን ከዚህ ሰፋ ባለ መንገድ ለማየት የተፈለገ እንደ ሆነ ከቀደመ ክፋትና ዓመፅ ተጸጽቶ መመለስ፣ ኃጢአትን ርኩሰትን እርም ማለት፣ ሁለተኛ በአስከፊ ግብር መንገድ ላይ ላለመገኘት በቊርጥ ሕሊና መወሰንና ቃል መግባት መሆኑን ማየት ይቻላል። ይህ በሆነ ጊዜ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የፈቀደው በጎ ነገር ሁሉ በቀላሉ ይከናወናል የራቀው ይቀርባል የታሰበው ይፈጸማል።

ኃጢአትን ለመምሕረ ንስሐ መንገር ወይም መናዘዝን እንደ ስሕተት የሚቆጥሩና «ሌላ ወኪል ምን ያስፈልጋል፤ እኔ ራሴ በቀጥታ ለእግዚአብሔር አልነግረውም?» ብለው የሚከራከሩ ሰዎች እንዳሉ ይታወቃል። ነገር ግን ሐሳባቸው ከቅዱሳት መጻሕፍት ቃል ውጭ ስለሆነ ፈጽሞ ተቀባይነት የለውም። በዚህ አጋጣሚ ኑዛዜ የሚለውን ቃል ስንመለከት ራስን የመግለጥ ትርጉም ይሰጠናል። ይኸውም በእግዚአብሔር ፊት በሠሩት ኃጢአት ምክንያት ራስን ማሳጣትና የራስን ደካማነት ማሳየት ማለት ነው። ይህ ዓይነት ሁኔታም በዘፈቀደ የሚፈጸም ሜዳዊ ሥርዓት ሳይሆን ከካህኑ ጋር ወይም በክህነት ሥልጣን የሚከናወን ቀኖናዊ ሥርዓት መሆኑን ማስተዋል ይገባል። «ሂድና ራስህን ለካህን አስመርምር ሙሴም እንዳዘዘው መባሕን ለእግዚአብሔር ስጥ» የሚለውን አምላካዊ ቃል በትክክል መመልከት ያስፈልጋል። (ማቴ.፰፥፬)

ንስሐ የእግዚአብሔር ርኅራኄ ወይም የቸርነቱ መግለጫ ነው በምን ልበት ጊዜ ለአንዳንድ ወገኖች እግዚአብሔር ስለ ኃጢአት ምንም እንደማያስብ ወይም ምንም እንደ ማይቆጣጠር መስሎ ሊታያቸው ይችላል። ነገር ግን እግዚአብሔር የማይቆጣጠረውና በዚያም ላይ ፍርድ የማይሰጥበት አንዳችም የበደል ዓይነት አለ ማለት ፈጽሞ አይቻልም። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የሥጋችን ሐሳብ (ፈቃድ) የእግዚአብሔር ጠላት ነው ብሎ እንደ ገለጸው የእግዚአብሔር ፈቃድ ከሥጋ ፈቃድ እጅግ የራቀና የተለየ ስለሆነ ኃጢአት የሠራች ነፍስ ለሞት የተዳረገች እንደሆነች ይታወቃል።

ከዚህም ጋር እግዚአብሔር ቸር ነው በማለት ስለ ርኅራኄው ስንናገር በኃጢአት ምክንያት የሚያስከትለውን የፀና ፍርዱን አቋርጧል ማለት አይደለም። እግዚአብሔር ርኅሩኅ አባት ሲሆን ፈራጅ ዳኛ መሆኑንም መዘንጋት አግባብ አይሆንም። ሲራክ «እግዚአብሔር ቸር ነው እያልክ በኃጢአት ላይ ኃጢአት አትጨምር» በማለት በዚህ በኩል ያለውን ሁኔታ ግልጽ አድርጎታል።

ርኅራኄ (ቸርነት) ለእግዚአብሔር የባሕርይ ገንዘቡ ስለሆነ ወዶ፣ ፈቅዶ ከሚያደርገው በቀር በማንም የሚገደድበት እንዳይደለ ማስተዋል ጠቃሚ ነው። ስለዚህ ነው ንስሐን የቸርነቱ ወይም የምሕረቱ ቁልፍ (መክፈቻ) አድርገን የምንመለከተው። የነነዌን ሰዎች በምናስብበት ጊዜ እግዚአብሔር ራሱ መልእክተኛውን ልኮ የንስሐን ሥርዓት እንዲፈጽሙ ማድረጉ የቸርነቱን ምልአትና ስፋት ከምንገነዘብ በቀር ሌላ ሰው ሰውኛ አስተያየት በላዩ ላይ ለማከል ዓቅም አይኖረንም።

ንስሐ ምሥጢራዊ ቀኖና ሁኖ የሚገኘውም ከዚህና ይህን ከመሳሰሉት ታሪካዊ ሁኔታዎች ጋር ተገናዝቦ ሲታይ ነው።

በሌላ በኩል የንስሐ ትርጉም ስለ ሠሩት ኃጢአት ራስን በራስ መቅጣት ሁኖ ይታያል። ሰው ኃጢአት ከሠራ በደልንም ከፈጸመ ለሠራው ኃጢአትና በደል አጸፋው ሞት መሆኑን አውቆ ራሱን በጸጸት፣ ብሎም የንስሐው ሥርዓት በሚያዝዘው መሠረት ራሱን ለቅጣት ማዘጋጀት ይኖርበታል። ይህ በማድረጉ የእግዚአብሔር ቸርነት አጥርና ቅጥር ወይም ጋሻና መከታ ሁኖ ስለሚጠብቀው ዕድሜው ይረዝማል፤ ሰላም ያገኛል፤ በመጨረሻም የኃጢአት ሥርየት ማግኘትና ርስተ መንግሥተ ሰማያትን የመውረስ ዕድልና ኃይል ይሰጠዋል።

በመሠረቱ ኃጢአት የሚያስከትለው መከራ በአፀደ ነፍስ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን በአፀደ ሥጋም ጭምር መሆኑ ሊታወቅ ይገባል። ሥርየትና ይቅርታ ያላገኘ ወይም በንስሐ ያልተወገደ ኃጢአት የሰውን ኑሮ ለልዩ ልዩ መከራ አሳልፎ ከመስጠቱም በላይ ዕድሜን በማሳጠር ለንስሐ እንዳይበቁ የማድረግም ጠባይ አለው። ለዚህም ነው በኃጢአት ከወደቁ በኋላ ቶሎ መንሣትና ለንስሐ ሥርየት መዘጋጀት የሚያስፈልገው።

በታሪክ መልክ ለማስታወስ ያህል ሁለቱ የኤሊ ልጆች አፍኒንና ፊንሐስ ለንስሐ ሳይበቁ መቀሠፋቸው፣ ሁለቱም የአሮን ልጆች ናዳብና አብዩድ በድንገት መሞታቸው የንስሐን ጥቅም በስፋት ሊያስገነዝበን ይችላል። የኃጢአት ዋጋ ሞት ነውና ከኃጢአት በኋላ በሕይወት የመቆየት ዕድል ማግኘት ደግሞ የእግዚአብሔርን ቸርነት የሚያመለክት በመሆኑ ይህን ተገንዝቦ ፈጥኖ ለንስሐ መዘጋጀት ከሁሉም የሚጠበቅ ክርስቲያናዊ ግዴታ ይሆናል።

ከዚህ ጋር አብሮ መታሰብ የሚገባው ለንስሐ ቀጠሮ መስጠት አላስፈላጊ መሆኑን ነው። በዚህ አጉል አስተሳሰብ የተጐዱ ብዙ ወገኖች በመሆናቸው የቅዱስ ጴጥሮስን የፈያታዊ ዘየማን የማርያም እንተ እፍረትን የንስሐ ጊዜ በምሳሌነት መጠቀም እጅግ አስፈላጊ ነው።

ሰው እግዚአብሔር በወሰነለት ዕድሜ የሚንቀሳቀስ ደካማ ፍጡር እንደ መሆኑ መጠን አብዛኛው የኑሮው ሁኔታ በዕለትና በሰዓት የተወሰነ ስለሆነ ይህን በመሳሰሉ ጉዳዮች ላይ ቀጠሮ ማስረዘሙ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱን የበዛ ሊያደርገው ስለሚችል ቀንም ሆነ ሰዓት የእግዚአብሔር ስጦታዎች መሆናቸውን አውቆ በወቅቱ ተገቢውን እንዲፈጽም ይጠበቅበታል።

(ጥቅስ) «ንስሐ ግቡ፤ ኃጢአትም ዕንቅፋት እንዳይሆንባችሁ ከኃጢአታችሁ ሁሉ ተመለሱ፤ የበደላችሁትን በደል ሁሉ ከእናንተ ጣሉ፤ አዲስ ልብና አዲስ መንፈስም ለእናንተ አድርጉ፤ የእስራኤል ቤት ሆይ ስለምን ትሞታላችሁ? የምዋቹን ሞት አልፈቅድምና ይላል ጌታ እግዚአብሔር ስለዚህ ተመለሱና በሕየወት ኑሩ» (ሕዝ.፲፰፥፴–፴፪)። ✣

www.ethiopianorthodox.org

# ከ ወ ጣ ቱ ለ ወ ጣ ቱ



ወጣት አሐዱ ዓለሙ ተወልዶ ያደገው እዚሁ አዲስ አበባ ወረዳ ፳፭ ቀበሌ ዜሮ ፫ ኮልፌ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ነው። የ፳፯ ዓመቱ ወጣት ከግማሽ በላይ የሚሆነው እድሜውን ያሳለፈው በብርሃናተ ዓለም ጴጥሮስ ወጳውሎስ የሰንበት ት/ቤት በመሳተፍና ቤተክርስቲያኑን በማገልገል ነው። ከተራ የሰንበት ት/ቤት አባልነት ጀምሮ አሁን እስካለበት የምዕራብ ክፍለ ከተማ የወጣት አስተባባሪነት ደረጃ በተለያዩ ኃላፊነቶች ሠርቷል። ቀሪውን የወጣት አሐዱ ታሪክ በሚቀጥለው መልክ አዘጋጅተነዋል።

**ፈለገ ጥበብ** – የልጅነት (የሕፃንነት) ሕይወትህ ምን ይመስል እንደ ነበር ልታወጋን ትችላለህ?

**አሐዱ ዓለሙ** – ከቤተሰቤ እንዳ ገኘሁት ታሪክ የስለት ልጅና ለቤተሰቤ ብቸኛ ልጅ ነኝ። እናቴ እንደ ነገረችኝ ለቁልቢ ቅዱስ ገብርኤል ልጅ ስጠኝ ብላ ተስላ ነው የወለደችኝ። ክርስትና በምነሳበት ጊዜም ለቅዱስ ገብርኤል ነው የተሰጠሁት። በመሆኑም የክርስትና አባቴ ቅዱስ ገብርኤል ነው። በሕፃንነቴ ዘመናዊ ት/ቤት ከመግባቴ በፊት በአብነት (ቄስ) ትምህርት ቤት ፊደል ከመቍጠር ጀምሮ ዳዊት ድረስ ተምሬ አለሁ። ከዛ በኋላ አልገፋሁበትም። ወደ ሰንበት ት/ቤት ከገባሁ በኋላ ግን መንፈሳዊውን የወንጌል ትምህርት በመማር እውቀቴን አሻሽያለሁ። የልጅነት ሕይወቴ በአጭሩ ይህን ይመስላል።

**ፈለገ ጥበብ** – በዘመናዊ ትምህር ትስ እስከምን ደርሰሃል?

**አሐዱ ዓለሙ** – ፲፪ኛ ክፍልን ጨርሸ አሁን በሂሳብ አያያዝ (አካውን ቲንግ) የመጀመሪያ ዓመት ተማሪ ነኝ።

**ፈለገ ጥበብ** – ወደሰንበት ት/ቤት የገባኸው መቼና እንዴት ነበር?

**አሐዱ ዓለሙ** – ትክክለኛ ዓመተ ምህረቱን ባላውቀውም በ፲፱፻፸ዎቹ ድርቅ በነበረበት ወቅት ነው። ቤተሰቦቼ በጣም የቤተክርስቲያን ሰዎች ናቸው። እናቴ ዘወትር ወደ ቤተ ክርስቲያን ይዛኝ ትሄድ ስለ ነበር ከሕፃንነቴ ጀምሬ ወደቤተክርስቲያን አደላ ነበር። በተለይ የቤተክርስቲያን አልባሳትን ሳይ ይመስጠኛል። ካህናት ልብሰ ተክህኖ ለብሰው ሲቀድሱ፣ ታቦታቱን አጅበው ወደ ባሕረ ጥምቀት ሲሄዱና ሲመለሱ በጣም ይማርከኝ ነበር። በዚህ በዚህ እየተሳብኩ መጣሁና ሰንበት ት/ቤት ገባሁ፤ ከገባሁ በኋላም የበለጠ እየወደድኩት መጣሁ።

**ፈለገ ጥበብ** – በሰንበት ት/ቤት በቆየህባቸው ዓመታት በምን በምን የሥራ ኃላፊነት ሠርተሃል?

**አሐዱ ዓለሙ** – በተለያየ ኃላፊነት በተደጋጋሚ ሠርቻለሁ። በተለይ ከ፲፱፻፹፩ ዓ.ም እስከ ፲፱፻፺፪ ዓ.ም የሰንበት ት/ቤቱ ኃላፊ ሁኜ አገልግያለሁ። ከዚህ በተጨማሪ በተለያዩ የቤተክርስቲያኑ የልማት ኮሚቴዎች በኃላፊነት ሠርቻለሁ።

**ፈለገ ጥበብ** – ከአዲስ አበባ ውጭ ያየሃቸው ገዳማትና አድባራት ይኖራሉ?

**አሐዱ ዓለሙ** – ገዳማትንና አድባራትን ማየት በጣም እወዳለሁ። መውደድ ብቻ ሳይሆን መጐብኘትም አዘወትራለሁ። እንዲያውም በራሴ አነሳሽነት «ደብረ ሐይቅ እስጢፋኖስ መንፈሳዊ ጉዞ ማኅበር» የሚል አቋቁሚ የማኅበሩ አባላት በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች በሚገኙ አድባራትና ገዳማት ጉብኝት አድርገናል። በዚህ ማኅበር ውስጥ ፲፰ ቋሚ አባላት አለን። ሁላችንም ወጣቶች ነን። እስከ አሁን በማኅበራችን አማካኝነት አክሱም ጽዮንን፣ ቁልቢ ቅዱስ ገብርኤልን፣ ግሸን ማርያምን፣ ደብረ ሊባኖስን፣ አዳዲ ማርያምን፣ ዝቋላ አቦን፣ ሸንኮራ ዮሐንስን ጐብኝተናል። ይህ በአዲስ አበባና በዙሪያዋ የሚገኙትን ሳይጨምር ነው። ለወደፊቱም ያላየናቸውን ለማየት ዕቅድ አለን።

**ፈለገ ጥበብ** – እስከ አሁን ካየሃቸው ይበልጥ የማረከህ የትኛው ገዳም (ቤተክርስቲያን) ነው?

**አሐዱ ዓለሙ** – መንፈሴን በጣም የመሰጠኝ ግሸን ማርያም ነው። እዛ ከደረስኩ በኋላ ወደዚህ መመለስ ሁሉ የተቸገርኩበት ሁኔታ ነበር። ከጠበቅኩት በላይ ሆኖ ነበር ያገኘሁት።

**ፈለገ ጥበብ** – አሁን ደግሞ ወደ ወጣትነት ሕይወት ልመልስህ፤ ባንተ አመለካከት (አስተያየት) በአሁኑ ወቅት የወጣቱ መንፈሳዊ ተሳትፎ እየተጠናከረ ነው እየተዳከመ የሚገኘው?

**አሐዱ ዓለሙ** – በኔ ዕይታ ወጣቱ የበለጠ እየተጠናከረ ያለበት ሁኔታ ይመስለኛል። በተለይ ክርስትናው በክርስትናነቱ ከማንገብ ይልቅ ክርስትናውን እየኖረበት ያለበት ዘመን ቢኖር ይህ ዘመን ነው ባይ ነኝ። «ክርስቲያንና ምስማር ሲመቱት ይጠብቃል» እንደሚባለው የተለያዩ የሃይማኖት ተጽእኖዎች በተበራከቱበት በአሁኑ ሰዓት ወጣቱ ሃይማኖቱን የበለጠ እያጠበቀ፣ እያጠነከረ ያለበት ሁኔታ ይመስለኛል።

**ፈለገ ጥበብ** – በዚህ ዓይነት ወጣቱን የሚያጋጥሙት ችግሮች የሉም ወይም ሊሻሻሉለት የሚገቡ አሠራሮች የሉም ማለትህ ነው?

**አሐዱ ዓለሙ** – አሉ እንጂ፣ እንደዛም ሆኖ ከኔ ጀምሮ ሁላችንም የሚጠበቅብንን ሠርተናል ማለቴ አይደለም። በተለይ ከላይ እስከ ታች ሊኖሩ የሚገባቸው መዋቅራዊ አዘረጋጎች አልተስተካከሉም። በመሆኑም ሰፊ ጥናት ተደርጎ ወጣቱ ወጥ በሆነ አሠራር በጋራ የሚንቀሳቀስበት መድረክ መመቻቸት አለበት። ወጣቱ በራሱ አነሳሽነት ሩቅ መሄድ አይችልምና።

**ፈለገ ጥበብ** – እንዳንተ ላሉ ወጣቶች በተደጋጋሚ የማቀርበውን ጥያቄ ላንተም ልጠይቅህና በወጣቱ ዘንድ እየታዩ ያሉ የሥነ ምግባር ጉድለቶች መንስኤያቸው ምንድነው ትላለህ? ምንጫቸው ከራሱ ከወጣቱ፣ ከወላጆች፣ ወይስ ከሌላ?

**አሐዱ ዓለሙ** – በሀገራችን በተለይ ደግሞ በከተሞች በወጣቶች የሚታየው የጥፋተኝነት አዝማሚያና ጉድለት መንስኤ ከቤተሰብና ከወጣቱ ብቻ አይደለም፤ መንግሥት የሚያወጣቸው ፖሊሲዎችና ሕጎች በራሳቸው ችግር ያለባቸው ይመስለኛል። በዲሞክራሲና በነፃነት ስም በባሕላዊ እሴቶቻችን ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ እየደረሰ ነው። ወጣቱ በተፈጥሮው አዲስ ነገር የሚፈልግ ኃይል ነው፤ ያየውን ነገር ቶሎ መገልበጥ የሚፈልግ ክፍል ነው። በመሆኑም የሚያያቸውን የባሕር ማዶ ነገሮች (መጥፎና ጥሩ መሆናቸውን ሳያገናዝብ) በራሱ ለመተግበር ይሮጣል።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ መታየት ያለበት የትምህርት ቤቶች ሁኔታ ነው። በት/ቤቶች የግብረ ገብነት ትምህርት አለመኖር በራሱ አንዱና ዋነኛ ችግር ነው። ከሁሉ በላይ ግን መምህራኑ ራሳቸው የግብረ ገብ ሰዎች ሆነው አለመገኘታቸው ነው። እነርሱ ራሳቸው እያጨሱ፣ እየጠጡ ተማሪዎችን ማጨስና መጠጣት ያስተምሩአቸዋል። አንደበታቸው ክፉ እየተናገረ ክፉ መናገርን ያስተምሩአቸዋል። በአለባበሳቸው ዝርክርክነት በሕፃናቱ አእምሮ ላይ መጥፎ ተጽእኖ ያሳድሩባቸዋል። እነዚህ ሁሉ ለወጣቱ ባሕርይ መበላሸት የራሳቸው የሆነ ድርሻ አላቸው።

**ፈለገ ጥበብ** – አሁን ደግሞ ወደ ግልህ ሁኔታ እንመለስ፤ በዚህ ዓመት በሚደረገው ሀገር አቀፍ ምርጫ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በግልህ ተወዳዳሪ ሆነህ መቅረብህን ሰምቻለሁ። ይህንን ለማድረግ ያነሳሳህ ምክንያት ምንድነው?

**አሐዱ ዓለሙ** – ምክንያቱን በግልጽ አላውቀውም፣ ብቻ አንድ ነገር በውስጤ አለ፣ በመጽሐፈ ነገሥት ውስጥ የብሉይ ታሪክ ሳነብ የመሪዎችን ተግባርና የሥልጣን ኃላፊነት አይቼ በዘመናችን ካሉት መሪዎቻችንና ባለሥልጣናቶቻችን ጋር ሳገናዝበው የሚሰማኝ ነገር አለ። ስለዚህ የእግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ ብመረጥ የሚሰማኝን ስሜት በተግባር ልግለጠው ብየነው። እኔ ብቻዬ ሳልሆን ዛሬ እኔ ብሞክረው ነገ ሌሎች እኔን አይተው የሚከተሉኝ ይኖራሉ ከሚል ነው።

**ፈለገ ጥበብ** – አሁን እየገባህ ያለው ወደ ፖለቲካው ዓለም ይመስ ለኛል፤ ለመሆኑ በግልህ በፖለቲካ ያለህ ዕውቀት (ግንዛቤ) ምን ይመስላል?

**አሐዱ ዓለሙ** – ዕውቀቱ የሰፋ ባይሆንም፣ መገናኛ ብዙኃንን በሚገባ ስለምከታተልና ስለማነብ በመጠኑ ግንዛቤ አለኝ ብዬ አስባለሁ።

**ፈለገ ጥበብ** – ባንተ አስተሳሰብ በአንድ ጊዜ ፖለቲከኛም መንፈሳዊም ሰው መሆን ይቻላል?

**አሐዱ ዓለሙ** – አይቻልም፣ ግን ፖለቲካ የራሱ የሆነ ጉድለቶችና ችግሮች አሉበት፣ እነዚህን ሸሽተን በመንፈሳዊ ሕይወት ብቻ እንኑር ብንል ደግሞ መጀመሪያ ተጠቂ የሚሆነው መንፈሳዊ ሰው ነው፣ ስለዚህ ሁለቱንም በአንድነት አጣምሮና አገናዝቦ ለማስኬድ የሚያስችል አሠራር ማምጣት ያስፈልጋል፤ የኔ ዓላማ ርእዮተ ዓለም ልበለው ይህንን አዲስ ሥርዓት ለመመሥረት ነው።

**ፈለገ ጥበብ** – ለተወካዮች ምክር ቤት ተወዳዳሪ ሆነህ በመቅረብህ ከሰንበት ት/ቤቶች ወጣቶችም ሆነ ከምእመናን የሚሰጥህ አስተያየት ምን ይመስላል? አሸንፋለሁ ብለህስ ትተማመናለህ?

**አሐዱ ዓለሙ** – በአብዛኛው ጥሩ ነው፣ እኔ ከጠበቅኩት በላይ ነው፣ እንዲያውም እኔ በቅስቀሳው ብዙም የለሁበትም፤ ምናልባት የእግዚአብሔር ኃይል ስለተጨመረበት ይሆናል ሁኔታው በጥሩ ሁኔታ ነው ያለው። ታሸንፋለህ ወይ? ለተባለው አሸናፊው የሚያውቀው እግዚአብሔር ነው። ለመወዳደር ስገባ ግን ለማሸነፍም ለመሸነፍም ነው። ለሁሉም ጊዜው ሲደርስ ይታወቃል።

**ፈለገ ጥበብ** – በደብራችሁ በብርሃናተ ዓለም ጴጥሮስ ወጳውሎስ ቤተክርስቲያን በተገነባው ዘመናዊ የሰንበት ት/ቤቶች ሕንፃ ያንተ አስተዋጽኦ ከፍተኛ እንደ ነበር ይነገራል። ስለዚህ ጉዳይ ልታጫውተኝ ትችላለህ?

**አሐዱ ዓለሙ**፣ ሕንፃው ባለሦስት ፎቅ ዘመናዊ ሕንፃ ነው፣ ይህንን ሕንፃ ያሠሩት አቶ ወልድሄር ይዘንጋው የተባሉ የግዮን ኢንዱስትሪያል ኮሜርሻል አክስዮን ማኅበር ባለቤት ናቸው። ትክክለኛ የገንዘቡ መጠን ባላውቀውም በጎ አድራጊው እስከ አሁን መጋቢት አጋማሽ ከሰባት መቶ ሺህ በላይ ገንዘብ ለዚህ ሥራ ወጪ አድርገዋል። ሕንፃው በውስጡ የተለያዩ ቢሮዎች፣ መሰብሰቢያ አዳራሽና የመሳሰሉትን የያዘ ነው። ወደ ጥያቄው ልመለስ አዳራሹን ያሠሩትና ሊመሰገኑ የሚገባቸው አቶ ወልድሄር ናቸው። እኔ ያደረግኩት ቢኖር ሥራው ከመጀመሩ በፊት ላቀድነው ዓላማ እንዲያግዙን ለሳቸው ጥያቄ ማቅረቤ ብቻ ነው።

**ፈለገ ጥበብ** – በመጨረሻ ለወጣቱ የምታስተላልፈው መልእክት ይኖርሃል?

**አሐዱ ዓለሙ** – እኔም ወጣት እንደመሆኔ መጠን ለወጣቱ የማስተላልፈው መልእክት ወጣቱ ቤተክርስቲያን ያለችበትን ሁኔታ ከአባቶች ሕይወታቸውን፣ ታሪካቸውን፣ ምግባራቸውን፣ ፍሬአቸውን በወሬ ሳይሆን ጠጋ ብሎ፣ ቀርቦ፣ አይቶ፣ ተረድቶ ቀምሶም ማወቅ አለበት። ቤተክርስቲያንን ዝም ብሎ ሊመላለስባት ሳይሆን በውስጧ ሊኖርባት ከስዋም በረከት፣ ረድኤትና ጸጋ ሊያገኝባት የሚችልበትን ሁኔታ ሊያመቻች ይገባዋል። ሃይማኖቱን በምግባር አስደግፎ ከሁሉ የሚበልጠውና የማያልፈው ሰማያዊ ክብርን ለማግኘት ወደ ቤተክርስቲያን ቀርቦ የቤተክርስቲያን ልጅ ሆኖ እንዲያድግ ነው የምመኘውና የምመክረው። ✣



www.ethiopianorthodox.org

# መንፈሳዊ ጉዞ ወደ ምድረ ምሁር

(የብዕር ቅኝት) ካሕሳይ ገ/እግዚአብሔር

ምሁር በጉራጌ ዞን መስተዳድር ሥር የምትገኝ፣ በውስጧ ቆላ፣ ወይና ደጋና ደጋ የአየር ንብረት አጣምራ የያዘች ውብ አካባቢ ናት። ምሁር ከሌላው የጉራጌ አካባቢ የሚለያት አንዱና ዋናው ምክንያት ነዋሪዎቿ በሙሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አማኞች መሆናቸው ነው። ዛሬ ዛሬ ግን በንጹሑ የምሁር የስንዴ ማሣ ላይ እንክርዳድ መብቀል ጀምሯል።

የምሁር ተወላጆች እንክርዳዱ ተባዝቶ ንጹሑን የስንዴ ዘር ከማበላሸቱ በፊት በኅብረት ሆነው የአባቶቻቸው፣ የእናቶቻቸው፣ ከሁሉ በላይ ደግሞ የአቡነ ዜና ማርቆስን ፀረ እንክርዳድና ፀረ አረም የወንጌል መድኃኒት በሁሉም የጉራጌ ማኅበረሰብ ማሳ ላይ ለመርጨት የተቀናጀ መንፈሳዊ ዘመቻ በማካሄድ ላይ ናቸው፤

እኔም ምሁርን ለመጀመሪያ ጊዜ ያየሁዋት ባለፈው ጥር ወር በአካባቢው በተካሄደው አንድ መንፈሳዊ ዘመቻ ተካፋይ ሁኜ ለመሄድ በመቻሌ ነበር። በዚህ ዘመቻ በብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ የከምባታ ሐድያና ጉራጌ አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ መሪነት በአካባቢው ተወላጆች የተቋቋመው መንፈሳዊ ኮሚቴ አባላት፣ ከመንበረ ፓትርያርክና ከአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት የተመረጡ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ተካፋይ ሆነዋል።

ጥር ፳፪ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ.ም ከጠዋቱ ፫:፲፭ ላይ በሁለት መኪናዎች ተሳፍረን ከአዲስ አበባ ጉዞ ጀመርን። እንደ አጋጣሚ (እንደ ዕድልም ልበለው) እኔ የጉራጌ ማኅበረሰብ የሀገር ሽማግሌዎች (የመንፈሳዊው ኮሚቴ አባላት) በነበሩባት ሽንጠ ረዥም መኪና ላይ ነበር የተሳፈርኩት። ጉዞአችን ተራ ጉዞ አልነበረም፣ በኮሚቴው ሰብሳቢ በአቶ ግርማ አጌቦ የተመራው ጉዞ ከጅምሩ እስከ ፍጻሜው የተሳካ ነበር። አዛውንቶች በየተራ እየተነሱ ከጉዞአችን ጋር የተያያዘ መንፈሳዊ ትምህርት ያስተላልፋሉ፣ ሌሎች ደግሞ ከተሰጠው ትምህርት ተነስተው የራሳቸውን ያክላሉ። ጉራጌዎች የሥራ ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ ጠንካራ የእምነት ሕዝቦች መሆናቸውን ይበልጥ የተገነዘብኩበት አጋጣሚ ነበር።

በተለይ አንድ አዛውንት ከመኪናው መሃል ቆመው ሲያስተምሩ «አባቶች ወንድሞች፣ አሁን ወደዘመቻ እየሄድን ነው፤ ዘመቻችን የወንጌል ዘመቻ፣ የመስቀል ዘመቻ፣ የሰላም ዘመቻ ነው፤ ትጥቃችን የክርስቶስ መስቀል ነው፤ ዓላማችን የጠራው የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነታችንን፣ አኩሪ ባህላችንን፣ በማይበቅል የመከነ ስንዴና ሰልቫጅ ለመለወጥ የመጡብንን አረማሞዎችን በወንጌል ትምህርት ለመንቀል ነው፤ በዘመቻችን ብዙ ፈተናዎችን ሊገጥሙን ይችላሉ፣ ቢሆንም ከሐዋርያትና ከጻድቃን ሰማዕታት አባቶቻችንና እናቶቻችን እንደተማርነው ያለፈተና ክብር አይገኝምና ሁላችንም ለመስዋዕትነት እንዘጋጅ» ያሉትን ምን ጊዜም አልረሳውም።

ጉዞአችን ሞቅ ባለ መንፈሳዊ ውይይት የታጀበ ስለ ነበር የጉራጌ ዞን ርእሰ ከተማ ከሆነችው ወልቂጤ ከተማ የደረስነው ሳይታወቀን ነበር። እዛም የኛን መምጣት ይጠባበቁ ከነበሩት ብፁዓን አባቶችና የቤተ ክርስቲያን ልዑካን ጋር ተገናኝተን አጭር ዕረፍት ካደረግን በኋላ ወደ ምሁር አቀናን። ወደጅማ የሚወስደውን የአስፋልት መንገድ ወደ ቀኝ ትተን ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ ታጠፍን። ሦስት ኪ.ሜ ያህል እንደ ተጓዝን ዋቢ ወንዝ ተቀበለን።

ዋቢ በጥር ወርም ቢሆን ውሃ እንደ ጠገበ እንደ ቆላ ዘንዶ እየተጠማዘዘ ቁልቁል ይንዶለዶላል። ለምልክት የቀሩ የሚመስሉ የዋርካ፣ የሾላ፣ የዶቅማ ወዘተ የመሳሰሉ «ሀገር በቀል ዛፎች» ዋቢን ከሐይለኛው የበጋ ፀሐይ ለመከላከል የፈለጉ ይመስል በሰልፍ ከወንዙ ዳርና ዳር ቆመው፣ ቅርንጫፎቻቸውን ወደ ውሃው ዘንበል አድርገው ይወዛወዛሉ። የዋህዋ ወልቂጤ ከተማ ግን ዋቢን የመሰለ ወንዝ በትራስዋ አስተኝታ ለዘመናት በውሃ ጥም ስትቃጠል ኖራለች አሉ።

ዋቤን ለቀን ትንሽ እንደ ተጓዝን የወሉሳላይሽ ሜዳን ከመሰለ ለጥ ያለ ስፍራ ደረስን። አብረውኝ የነበሩ የሀገር ሽማግሌዎችን ጠይቄ እንደ ተረዳሁት አካባቢው «አሞራ ሜዳ» ይሉታል። አሞራ ሜዳ የተባለው ታዲያ አሞራ በብዛት ያለበት ሳይሆን ከስፋቱ የተነሳ አሞራ በሮ አይጨርሰውም ለማለት ነው። እኔም እዚህም እዛም ለገጠሽ ከተሰማሩ ከብቶችና አነስተኛ ወፎች በስተቀር አሞራ ሜዳ ላይ አሞራ አላጋጠመኝም። አሞራ ሜዳ ገላጣ ብቻ ሳይሆን ዛፍ አልባ መላጣም ነው። በዛ ዝርግና ሰፊ ሜዳ አልፎ አልፎ የሚታዩት የዘንባባ ተክሎች ብቻ ናቸው። ጊዜው እየከነፈ ስለነበረ አሞራ ሜዳንና የከሰዓት በኋላ ፀሐይን የኋሊት እየተውን ወደ ፊት እንደ አሞራ ከነፍን።

አሞራ ሜዳ ሲያበቃ የአፈሩ ቀለምም አብሮ ተለወጠ፤ እንግዲህ ምሁር እየገባን ነው፣ ከአሞራ ሜዳ ቀጥሎ ያለው አካባቢ አክሊል ይባላል፣ አሉኝ አጠገቤ ሆነው ሲያስረዱኝ የነበሩ አዛውንት። እኔ ግን የእንሰት፣ የቡና፣ የጫት፣ የሙዝና የጌሾ ተክል እዚህም እዚያም ማየት ስጀምር ጉራጌ መሬት እንደገባሁ ቀደም ሲልም ገብቶኝ ነበር። ወደ ምሁር ክልል ይበልጥ እየዘለቅን በሄድን ቁጥር አፈሩ ብቻ ሳይሆን አየሩም የመሬት አቀማመጡም እየተለወጠ መጣ። በተለይ የጥር ወንዝን ከተሻገርን በኋላ ሙሉ በሙሉ በተፈጥሮ ዕፀዋት የተሸፈነ አካባቢ ነበር ያጋጠመን። በአጋም፣ በክትክታ፣ በብሳና በግራር በተሸፈነው መሬት ለገዳጅ የተሠማራ ወታደር ይመስል ኸርገራዎች በየሜዳውና በየዛፎች ሥር ይርመሰመሳሉ፤ ከቅርብና ከርቀት የቆቆች «መዝሙር» ይሰማል፣ ለስላሳው የወይና ደጋ ነፋስ ከየዛፎች እየተሸከመ የሚነስንሰው አየር ኅሊናን እርከቶ የደከመ አካልን ያድሳል።

ብዙም አልቆየሁ ዓይኖቼን አሻግሬ ሳማትር እዚያም እዚህም ጥቅጥቅ ባለ የተፈጥሮ ደን የተከበቡ፣ በአጸድ የታጠሩ ሥፍራዎች በብዛት ማየት ጀመርኩኝ። በመጀመሪያ እነዛ አካባቢዎች አብያተ ክርስቲያናት ያሉባቸው ሳይሆኑ አይቀርም የሚል ሃሳብ ቢመጣብኝም ቁጥራቸው ሲበዛብኝ ጊዜ መልሼ ተጠራጠርኩኝ። በኋላ ግን እነዛ ሁሉ አብያተ ክርስቲያናት መሆናቸውን ሲነገረኝ ግርምቴ ወሰን አልነበረውም። ያለማጋነን በአራቱም ማዕዘን በየአንዳንዱ ኪ.ሜ ርቀት (በአዲስ አበባችን አለካክ በየፈርማታው) ቤተ ክርስቲያን አለ። ሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ጥቅጥቅ ባለ አጸድ የተከበቡ በመሆናቸው ከቅርብም ሆነ ከርቀት ሕንፃ ቤተ ክርስቲያኑን ማየት አይቻልም። በምሁር ብቻ ፵፩ መሰል ጥንታዊያን አብያተ ክርስቲያናት አሉ። የሚገርመው ሁሉም አብያተክርስቲያናት በቅርጻቸው፣ ተመሳሳይ ከመሆናቸው የተነሳ አንድ መሃንዲስ የሠራቸው ነው የሚመስሉት። በአሁኑ ወቅት በአካባቢው ካሉት ፵፮ አብያተ ክርስቲያናት መካከል በገዳምነት የሚታወቁት ጥቂቶች ቢሆኑም አብያተ ክርስቲያናቱ ቀርተው ራሷ የምሁር መሬት ገዳም ናት ማለት ይቻላል።

በመጀመሪያ ያየሁትን ቤተ ክርስቲያን ሁሉ ስም ለመጠየቅ ሞካክሬ ነበር፣ ይሁንና ከብዛታቸው የተነሳ በቃሌ ስማቸውን ማስታወስ የቻልኩት በጣት የሚቆጠሩትን ብቻ ነው። አንድ ያስተዋልኩት ነገር ቢኖር በምሁር ውስጥ በኢየሱስ፣ በቅዱስ ሚካኤል፣ በአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ስም የሚጠሩ አብያተ ክርስቲያናት ቁጥር በርከት ማለታቸው ነው። ከዚህ ውጭ በአብዛኛው የኢትዮጵያ ክፍል ብዙም የማይዘወተር የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን በምሁር አጋጥሞኛል።

ቀኑን ሙሉ በጉዞ ላይ ያሳለፍን ቢሆንም ያየሁትን ሁሉ ሳልጠግበው ነበር ከታላቁ ገዳመ ኢየሱስ መቃረባችንን ያወቅኩት። ገዳመ ኢየሱስ ገና ከሩቅ አሻግረው ሲያዩት «ወደኔ ኑ» እያለ የሚጣራ ይመስላል። ከገዳሙ ለመድረስ በገዝ ወንዝን መሻገር ነበረብን፤ በገዝ ወንዝ የሁለት ወንዞች ድምር ነው። ሁለቱም ገባሮች እንደ ኤፍራጢስና ጤግሮስ ወንዞች ከመካከላቸው ደሴት በመፍጠር ቁልቁል ሲሽቀዳደሙ ከቆዩ በኋላ በገዝ ወንዝ ድልድይ አካባቢ ሲገናኙ ለብዙ ጊዜ ተለያይተው እንደተገናኙ ወንድማማቾች ተቃቅፈው የሚሳሳሙ ይመስላሉ።

ጠባቡና አንዳንዴም የሚያስፈራውን ገደላ ገደል መንገድ አልፈን ገዳመ ኢየሱስ ስንደርስ ፀሐይዋ «ከማደርያ ቦታችሁ ካደረስኩዋችሁ ዘንድ እንግዲህ ይበቃኛል ደህና እደሩ» ለማለት የፈለገች ይመስል ድንገት ጥላን ከአድማስ ባሻገር ወዳለው ማኅደርዋ ገባች። ገዳሙን ከበው የቆሙ ግዙፍ የወይራ፣ የጥድና የዝግባ ዛፎች በቁመትም በውፍረትም የአማዞንን ጫካ ዛፎች የሚያስንቁ ናቸው። ከሥር ሆነው ሲያዩዋቸው አሐዱ አብ፣ አሐዱ ወልድ፣ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ እያለ እንደሚጸልይ ካህን ቅርንጫፎቻቸውን ሽቅብ ዘርግተው ለፈጣሪያቸው ጸሎት የሚያደርሱ ይመስላሉ።

የገዳሙን አፀድ እየቃኘን፣ እያደነቅን፣ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ግቢ ስንዘልቅ ከ፹ በላይ የሚሆኑ ሕፃናትና ወጣቶች በመዝሙር ተቀበሉን። የለበሱት ፀዓዳ ልብስ ድንግዝግዝ ካለው ምሽት ጋር ተዳምሮ በጠራ ሰማይ ላይ በከዋክብት ተከባ እንደምትታይ ጨረቃ ልዩ ውበት አጐናጽፎአቸዋል። በገዳመ ኢየሱስ ውስጥ በደቡብ ኢትዮጵያ በዓይነቱ ብቸኛ የሆነ የአብነት ት/ቤት ተቋቁሟል። በብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ ጥረት በተለይ ደግሞ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ልዩ እገዛና ድጋፍ እንደዚሁም በአካባቢው ተወላጆች ርዳታ የተቋቋመው ይህ ት/ቤት በአሁኑ ጊዜ ከተለያዩ የጉራጌ ዞን አካባቢዎችና ከደቡብ ኢትዮጵያ የመጡ ከ፹፩ በላይ ሕፃናትን በአዳሪነት ተቀብሎ በማስተማር ላይ ይገኛል። የአብዛኞዎች ሕፃናት ዕድሜ ከ፰ እስከ ፲፪ ዓመት መካከል ያለ ነው። ከሕፃናቱ ሌላ ፳፰ የሚደርሱ መናንያን ደናግልና በማገልገልና በመማር ላይ የሚገኙ መነኮሳት በአጠቃላይ ፻፵፫ ያህል የቤተሰብ አባላት በገዳሙ ውስጥ ይገኛሉ።

ት/ቤቱ እነዚህን ሕፃናት ተቀብሎ ይፋ የማስተማር ሥራውን ከጀመረ ገና ሁለት ዓመቱ ቢሆንም ሕፃናቱ በዚህ አጭር ጊዜ ያስመዘገቡት ውጤት በእጅጉ የሚያስደንቅ ነው። የስምንትና የዘጠኝ ዓመታት ሕፃናት ቃለ እግዚአብሔርን ከወንጌል እየጠቀሱ፣ እየተነተኑ፣ እየተረጐሙ ሲያስተምሩ፣ በዛ የሕፃንነት ድምፃቸው ዜማ ሲያንቆረቁሩ፣ ቅኔ ሲዘርፉ፣ ማየቱና መስማቱ መንፈሳዊ ኩራትን ያጐናጽፋል። ወጣት መናንያን መነኮሳይያትም በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ ታዳጊ ሕፃናትን በመንከባከብ ከሚያበረክቱት መንፈሳዊ አገልግሎት በተጨማሪ ባለቻቸው ትንሽ ትርፍ ጊዜ ተምረው የቅኔ ማዕበል ሲያዘንቡ መስማቱ ኅሊናን ያጠግባል።

በርካታ ሊቃውንት እጥላቸው ሥር አስቀምጠው ሲያስተምሩ፣ ጻድቃን ሰማዕታትን ሲያስተናግዱ፣ የእነ አቡነ ዜና ማርቆስን የወንጌል ትምህርት ሲሰሙ ያደጉ እነዛ የመናንያን አምባዎቹ የወይራና የጥድ ዛፎች እነዚህ ሕፃናት በጥላዎቻቸው ዙርያ ሲመላለሱ የአበውን በረከት ሳያስተላልፉላቸው ይቀራሉ? ወይም ደግሞ ከእነዚህ ሕፃናት መካከል አንዱ የሉቃስ ወንጌልን ጠቅሶ ሲያስተምር እንዳለው በእምላክ ጸጋ ተሞልተው እያደጉ ስለሚገኙም ይሆናል።

ጥር ፳፪ ቀንን በዚህ መልክ ከፈጸምን በኋላ ጥር ፳፫ ገዳመ ኢየሱስን በማለዳ ለቀን የመጀመሪያው መንፈሳዊ ጉባኤ ወደሚካሄድበት አበደማን ቅዱስ ጊዮርጊስ አቀናን። አበደማን ቅዱስ ጊዮርጊስ በወይና ደጋውና በደጋማው የምሁር ጠርዝ ላይ ነው የሚገኘው። እንደተቀሩት የምሁር አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ዙርያው ጥቅጥቅ ባለ አጸድ የተከበበ በመሆኑ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ መግባት የሚቻለው በምሥራቅ አቅጣጫ ባለው በር ብቻ ነው።

አበደማን ቅዱስ ጊዮርጊስ ስንደርስ ራቅ ካሉ አካባቢዎች ሳይቀር በእግርና በፈረስ የመጡ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ምእመናን በሆታና በእልልታ ተቀበሉን። «መንፈሳዊው ዘመቻ» ከአበደማን ቅዱስ ጊዮርጊስ የተጀመረበት የራሱ የሆነ ምክንያት ነበረው። በመጀመሪያ ቤተ ክርስቲያኑ በምሁር አካባቢ ካሉት አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ቀዳሚና ጥንታዊ ነው። መልእክ ብርሃን ወልደ ኢየሱስ ወልደ ጊዮርጊስ የተባሉ የደብሩ አባት አገልጋይና አቶ ዓለሙ ዝርጋ የደብሩ ሰበካ ጉባኤ ም/ሊቀ መንበር በጋራ እንደ ነገሩኝ ቤተ ክርስቲያኑ የተመሠረተው ዞዊሳና ዘሚካኤል በተባሉ ከትግራይ በመጡ ሁለት ወንድማማቾች ነው። ጊዜው በትክክል ባያውቁትም ቤተ ክርስቲያኑ የተመሠረተው በአፄ ሰብሐት ዘመን እንደነበር ነው ሁለቱ አባቶች ያጫወቱኝ። ምሁሮች ዝርያችን ከእነዚህ ከትግራይ ከመጡ ሁለት ወንድማማቾች ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ነው ባዮች ናቸው።

መንፈሳዊው ጉባኤ በዚሁ አበደማን ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን እንዲጀመር የተደረገበት ሌላም ምክንያት ነበረው። ጥንት ነው አሉ፣ ወዳጀ ከተማ የሚባል እስላም ባለባት የምሁርን ሕዝብ ካላሰለምኩ ብሎ ተነሳ። ቤተ ክርስቲያኑን ለማቃጠልም ተደጋጋሚ ሙከራ አደረገ፤ ያኔ ቅዱስ ጊዮርጊስ በአካባቢው ብቸኛ ቤተ ክርስቲያን ነበር። በዚህ ጊዜ ነበር አበጋዝ እንጆ የተባለ የምሁር ተወላጅ ሕዝቡን አስተባብሮ ወዳጀ ከተማን ለመግጠም ክተት ያወጀው። ወደ ዘመቻ ከመነሳቱ በፊትም በቅዱስ ጊዮርጊስ



www.ethiopianorthodox.org

ቤተ ክርስቲያን ተገኝቶ ጸሎት ካደረሰ በኋላ «ቅዱስ ጊዮርጊስ ተከተለኝ እርዳኝ» ብሎ ተስሎ ሄደ። ወድያውም በቅዱስ ጊዮርጊስ ተራዳኢነት ወዳጁ ከተማን ድል አደረገው። በወቅቱ የወዳጁ ከተማን ወራሪ ፈረሰኛ ጦር ለመከላከል ተብሎ የተሠራ ምሽግ ዛሬ ድረስ በቤተክርስቲያኑ አጠገብ አለ። ይሁንና ይህ ጥንታዊ ምሽግ ከጊዜ በኋላ ወደ ወንዝነት ተለውጧል።

የእስላሞች ወረራ በዚህ አላበቃም። በሌላ ጊዜ ሃሰን እንጀም የተባለ ሙስሊም የወዳጁ ከተማን ሽንፈት ለመበቀል መጣ። በምሁር አካባቢ (ዙርያ) የሚገኙ ስፍራዎችን በወረራ አስገድዶ አሰለመ። ያኔ በምሁር አካባቢ ፵፬ ታቦታት (አብያተ ክርስቲያናት) ተተክለው ነበር። ሐሰን እንጀሞ በትምክህት «አርባ አራቱን አብያተ ክርስቲያናት ወደ መስጊድነት እለውጣቸዋለሁ» ብሎ ጦርነት አወጀ።

ጉራጌዎችም ሀገራቸውን ብሎም አብያተ ክርስቲያናቻቸውን በደማቸው ለመታደግ በአንድነት ተነሱ። በአራት አበጋዞች ማለትም ፩. አበጋዝ ጃቤ ፪. አበጋዝ ኢሌ ፫. አበጋዝ ሸበታ ፬. አበጋዝ ከሬ በተባሉ የሃይማኖት አርበኞች አዝማችነት በቅዱስ ጊዮርጊስ ተራዳኢነት የመጣባቸውን ጠላት ገጥመው ድል ከማድረጋቸውም በላይ ሐሰን እንጀሞን ጅማ ድረስ አሳድደው ገደሉት።

በኢጣሊያ ወረራ ወቅትም የሐሰን እንጀሞ ወገኖች ምቹ ጊዜ አገኘን ብለው በሃይማኖቱ በሚኮራው የምሁር የኦርቶዶክስ እማኝ ላይ ለሦስተኛ ጊዜ የሃይማኖት ወረራ አካሂደው ነበር። ይሁንና ዘናበር ላይ በተካሄደው ከባድ ፍልሚያ ጠላቶች ሽንፈታቸውን ጨልጠው ዋቢ ማዶ በመሻገር እግሬ አውጭኝ ብለው ሸሹ። በዚህ ውጊያ የምሁር እናቶች ሳይቀሩ ገጀራቸውን ይዘው በመዝመት ታላቅ የሕይወት መስዋዕትነት እንደከፈሉ የእድሜ ባለጸጎች በኩራት ይናገራሉ። በእነዚህ ውጊያዎች ሁሉ ጉራጌዎች እንደ ዋና አዝማቻቸው አድርገው የሚወስዱት ቅዱስ ጊዮርጊስን ነበር። እንግዲህ ከጥር ፳፫ ቀን እስከ ፳፭ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ.ም በምሁር አካባቢ የተካሄደው አራተኛው ሰላማዊ መንፈሳዊ ዘመቻ ምሥጢር ያለው ከዚሁ ነው። ዛሬም እንደ ጥንቱ ዘመቻው የተጀመረው ከቅዱስ ጊዮርጊስ ብቻ ሳይሆን የተመራው የአካባቢው ተወላጅ በሆኑ «በአበጋዝ» በብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ መሆኑ በራሱ የሚያስገርም አጋጣሚ ነው።

የሰበካ ጉባኤው ም/ሊቀ መንበር አቶ ዓለሙ ጨምረው እንደ ነገሩን ታሪካዊው የአበደማን ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በግራኝ መሐመድ ወረራ ወቅትም አልተቃጠለም። በአሁኑ ወቅት በቅጽረ ቤተ ክርስቲያኑ ሁለት አብያተ ክርስቲያናት ነው ያሉት፤ አንደኛው ከኢጣልያ ወረራ በፊት ጥንታዊው ቤተ ክርስቲያን በድጋሚ ታድሶ የተሠራ ሲሆን ሁለተኛውና አሁን አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኘው በ፲፱፻፶፯ እና በ፶፰ ዓ.ም መካከል በነበሩት ዓመታት በዘመናዊ መልክ የተሠራ ነው። ሁለቱንም አብያተ ክርስቲያናት ያሠሩዋቸው አቶ ወልዴ ከሬ የተባሉ ግለሰብ ነበሩ። በተለይ የመጀመርያውን ቤተ ክርስቲያን ባሠሩበት ወቅት የመኪና መንገድ ስላልነበረ ከአዲስ አበባ ድረስ ቆርቆሮ በሰው ትከሻ በማስመጣትና ከነበራቸው ንብረት ሢሦውን ለዚህ ሥራ በማበርከት ነበር። አቶ ወልዴ በዚህ ብቻ የተወሰኑ አልነበሩም። በምሁር አካባቢ የሳቸው አስተዋጽኦ ያልታከለበት የቤተ ክርስቲያን ሥራ የለም ማለት ይቻላል። በነገራችን ላይ አቶ ወልዴ ከሬ የዝነኛው አበጋዝ ከሬ ልጅ ናቸው። አበደማን ቅዱስ ጊዮርጊስ በኢትዮጵያ ታሪክ «ከአዋሽ በታች» ለመጀመርያ ጊዜ ቆርቆሮ የለበሰ ቤተ ክርስቲያን መሆኑ ይነገርለታል።

ጥር ፳፬ ቀን ተራው የአበጀ ደብረ አሚን ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን ነበር። አበጀ ተክለ ሃይማኖት በደጋማው የምሁር አካባቢ የሚገኝ ነው። አካባቢውን የሚያውደው የጦስኝ መዓዛ የማለዳውን ቅዝቃዜ ያስረሳል። እንደ አበደማን ሁሉ በዚህ ቤተ ክርስቲያን የተካሄደው መንፈሳዊ ጉባኤ ከፍተኛ የሕዝብ ተሳትፎ የታከለበትና ውጤታማ ነበር። መናፍቃን ለመጀመሪያ ጊዜ ራሳችንን በቤተ ክርስቲያን ቅጽረ ግቢ ካልቀበርን በሚል ችግር የፈጠሩበትና በዚህ የተነሳ ካህናትና ምእመናን አለ አግባብ ለእሥርና ለእንግልት የተዳረጉበት በአጠቃላይ ጠንካራ የምሁር የኦርቶዶክስ ልጆች የአባቶቻቸውን እርግማ አንስተው የተፈተኑበት በዚህ የምሁር አካባቢ ነበር።

ጥር ፳፬ ቀን ከሰዓት በኋላ ጉዞ ወደ የናዳ ሆነ። የናዳ በጥንታዊው የቅዱስ ሚካኤልና በአቡነ ዜና ማርቆስ ገዳም መካከል ለጥ ባለ ደጋማ ሥፍራ የምትገኝ መንደር ናት። በአካባቢው የሚገኙ ምእመናን በቅርብ ቤተ ክርስቲያን ስላልነበራቸው አቀብቁልቁለትን አቋርጠው ገደሉን ቧጠው ከሰፈራቸው ርቆ ወደሚገኘው ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ድረስ መሄድ ነበረባቸው። ወደ ቤተ ክርስቲያኑ የሚወስደው መንገድ ገደላማና ድንጋያማ ሬሣ ተሸክሞ ለመሄድም ሆነ ለእድሜ ባለጸጎች የማያመች በመሆኑ በቅርብ የአካባቢው ተወላጆች ተመካክረው በየናዳ አካባቢ አዲስ የኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን አሠርተው ጥር ፳፭ ቀን በብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ ተባርኮ ቅዳሴ ቤቱ ተከብሯል።

ሦስተኛውና የመጨረሻው መንፈሳዊ ጉባኤ የተካሄደውም በዚሁ የናዳ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ነበር። አካባቢው በጳጳስ ሲባረክ ለመጀመሪያ ጊዜ ስለነበር ሕዝቡ የተሰማው ከፍተኛ የደስታ ስሜት በእልልታና በዘፈን ለመግለጽ ቀኑ ስላልበቃው ዘፈኑም ጭፈራው እስከ ምሽቱ ነበር የዘለቀው። እኛ እነዛ እንግዳ አክባሪዎችና ጠንካራ ሕዝቦችን ለመለየት ባንፈልግም የሥራ ነገር ሆነና የሦስት ቀን ቆይታችንን ፈጽመን ያላስተዋልነውን እየቃ ኘን የምሁርን ትዝታ በጎሊናችን ቋጥረን ወደ አዲስ አበባ የመልስ ጉዞ መጀመር ነበረብን።

ምሁር በቆየሁባቸው ቀናት ያስተዋ ልኩት አንድ ታላቅ ቁም ነገር ነበር። ጉባኤ በተካሄደባቸው አጥቢያ የሚገኙ ምእመናን ከየቤታቸው ጠላ፤ እንጀራ፤ ወጥ፤ ወተት፤ ቆሎ በማምጣት ራቅ ካሉ አካባቢዎች ትምህ ርቱን ለመከታተል ለመጡ ምእመናን ያስተና ግዳሉ። መስተንግዶውም የድግስ ያህል ነው። የሚገርመው ጋባዥቹም ተጋባዥቹም በአንድ ነት በዐፀደ ቤተ ክርስቲያን ተሰባስበው ነው የሚመገቡት፤ የሚያስቀና ክርስቲያናዊ ባህል።

«ምሁር» የሚለው ቃል በጉራግኛ ያለው ፍቺ ጠይቄ ባልረዳም (በስንፍናዩ) በራሴ ግን ፈትቸዋለሁ። እንደ ምሁሮች አባባል የዘራቸው ሥርወ ግንድ ትግራይ ነው። ስለዚህ ቃሉ ከትግርኛ የተወረሰ መሆን አለበት። ምሁር በትግርኛ ሁለት ትርጉሞችን የያዘ ነው። አንደኛው የተማረ፤ ያወቀ ማለት ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ከእግዚአብሔር ምህረት ያገኘ የተመረቀ የተባረከ ማለት ነው። ትክክለኛ ትርጉሙም ይህ መሆን አለበት፤ ምሁሮች ሁለቱን ያሟላሉና። ✣



# «እግዚአብሔር ለሕዝቡ በመጽሐፍ ይነግራቸዋል»

በመጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ



እግዚአብሔር ከሥነ–ጽሕፈት በፊት ለሕዝቡ በራእይ፤ በሕልምና በመልአክ በሌላም ልዩ መገለጥ ይናገር ነበር። በኋላ ግን በእነዚህ መንገዶች ተገልጦ ለሕዝቡ የነገ ራቸው ሁሉ ስለተጻፈ ሕዝቡ በመጽሐፉ እንዲጠቀሙ ሆነ።

በመጨረሻም ራሱ እግዚአብሔር ወልድ ሰው ሆኖ ፊት ለፊት ቃል በቃል ለሕዝቡ ነገራ ቸው። ይህም እንደገና መጽሐፍ ሆነ። እግዚ አብሔር ለሕዝቡ ሊናገረው፤ ሕዝቡም ከእግ ዚአብሔር ሊሰማው የሚያስፈልገው ሁሉ እነሆ በአንድ መጽሐፍ ተካትቶአል። ስለዚህ «ጌታ ሆይ ተናገር ባሪያህም ይሰማል» (፩ሳሙ.፫፥፲) በማለት ዛሬ የእግዚአብሔርን ድምፅ ለመስማት ራእይ ወይም ሕልም መጠ በቅ ሳይሆን እግዚአብሔር ለሕዝቡ ለመናገር ድምፁን የሚያሰማበትን መጽሐፍ መመርመር ነው የሚያስፈልገው «ኅሡ መጻሕፍተ ወትረ ከቡ:- መጻሕፍትን መርምሩ ታገኛላችሁም» (ዮሐ.፭፥፴፱) ተብሎአልና።

እግዚአብሔር ለመናገር ድምፁን የሚያ ሰማበት መጽሐፍ ምንድን ነው? ጥያቄው ቀላል ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ነው ብሎ መመለስ ግን ቀላል አይደለም። የእግዚ አብሔርና የሰዎች መነጋገሪያ መሣሪያ የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ መሆኑን ማወቅ ከዕውቀት ሁሉ በላይ ነውና።

ቅዱስ መጽሐፍ ለእግዚአብሔር መናገ ሪያ ለሆነው መጽሐፍ የተሰጠ ልዩ ስም ነው። እስካሁን ሌላ መጽሐፍ ያልተጠራበት ወደ ፊትም የማይጠራበት ቅዱስ ስም ነው። ከቅዱስ እግዚአብሔር ለቅዱስ ሕዝብ በቅዱስ መካን በመስጠቱ፤ በቅዱሳን ሰዎች በመጻፉ፤ በሃይማኖት (በእምነት) የሚያነቡትን ሁሉ በመቀደሱ ቅዱስ የሚለው ቅጽል ተሰጥቶ ታል። በቅድስት ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ለሚፈጸሙ ምሥጢራትና ሥርዓታት ሁሉ በዚሁ መጽሐፍ ውስጥ በተገመረው ቃለ እግዚአብሔር አመካኝነት ቅድስና መስጠቱ ቅዱስነቱን በተጨማሪ ያረጋግጠዋል። ቅዱስ የሚለውም ቃል ልዩ ማለትን ያመለክታል፤ በይዘቱ፤ በማያቋርጥ መልእክቱና በምሥጢር ጥልቀቱ እስካሁን ከተጻፉትና ወደፊትም ከሚጻፉት መጻሕፍት ሁሉ ልዩ ነውና። ለምሳሌ ሌሎች መጻሕፍት ወቅታውያን ናቸው። ቋንቋቸው መልእክታቸው ወቅቱን የሚመ ለከት ብቻ ነው፤ የመጽሐፍ ቅዱስ መልእክት ግን በዘመናት ሁሉ አይለወጥም። ሌሎች መጻሕፍት በቋንቋው ለተጻፉለት ለአንድ ሀገር ሕዝብ ብቻ ስሜት ይሰጣሉ፤ ቅዱስ መጽሐፍ ግን በተለያዩ ቋንቋዎች የሚናገር የዓለምን ሕዝብ ሁሉ ስሜት ይነካል፤ ይመክራል፤ ይገስጻል፤ ያስተምራልም።

ሌሎች መጻሕፍት ከተነበቡ በኋላ በመደ ርደሪያቸው የሚቀመጡ ከዚያም በኋላ ካስፈለጉ የሚታዩ ናቸው። ቅዱስ መጽሐፍ ግን ምን ጊዜም ከጠረጴዛ ሊለይ የማይገባው የዘወትር መጽሐፍ፤ የዕለት ሥነ–ዜና ነው።

ሌሎች መጻሕፍት በዕድሜ ይወሰናሉ፤ ቅዱስ መጽሐፍ ግን ወጣቶችም ሽማግሌ ዎችም የሚወዱት፤ ለሁሉም በየደረጃቸው መልእክትን የያዘ መጽሐፍ ነው። «...ሕፃ ንነትህን የሚንቃት አይኑር፤ በቃልህም፤ በሥራህም፤ በፍቅርና በሃይማኖት በንጽሕናም ለምእመናን አርአያና ምሳሌ ሁናቸው። እስከመጣም ድረስ በማንበብ፤ በመምከርና በማስተማር በመጸለይም ጸንተህ ኑር።» (፩ጢሞ.፲፪፥፲፫)

«ወጣቶች እጽፍላችኋለሁ፤ ክፉውን ድል ነሥታችሁታልና፤ አባቶች ጻፍሁላችሁ፤ ቀዳማዊ እርሱን ዐውቃችሁታልና። ወጣቶች ጻፍሁላችሁ፤ ብርቱዎች ናችሁና። የእግዚአብ ሔርም ቃል በእናንተ ዘንድ ጸንቶ ይኖ ራልና... (፩ዮሐ.፪፥፲፫–፲፬) በማለት በየዕድ ሚያቸው ደረጃ ይመክራልና፤ ያስተም ራልምና።

እያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊ በራሱ ቃላት፤ ቋንቋ፤ ሥነ–ጽሕፈትና ስልት ቢጠቀምም አሳቡም ቃሉም የእግዚአብሔር እንጂ የጸሐፊው አይደለም። እግዚአብሔር ሙሴን አለው «...ይህን ለመታሰቢያ በመጽ ሐፍ ጻፈው» (ዘጸአ.፲፯፥፲፬) «ታላቅ ሰሌዳ ወስደህ...በሰው ፊደል ጻፍ...» አለው ኢሳ ይያስን። ኤርምያስንም አለው «...ክርታስ ውሰድ፤ በእስራኤልና በይሁዳ ላይ፤ በአሕ ዛብም ሁሉ ላይ የተናገርሁህን ቃል ሁሉ ጻፍ» (ኢሳ.፰፥፩፤ ኤር.፴፮፥፪) ይህና የመሰለው ሁሉ የሚያስረዳን በሰብአዊ ጸሐፊ የተጻፈው የእግዚአብሔር ቃልና አሳብ መሆኑን ነው።

ዐምደ ሃይማኖት ቅዱስ ቁርሎስም «ቅዱሳት መጻሕፍት እስትንፋሰ እግዚአብ ሔር ናቸው።» (ቁርሎስ ሃይማኖተ አበው ፸፰:፳፯) በማለት እንዳስተማረው ቅዱስ መጽ ሐፍ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ መሪነት፤ አለባዊነትና አስተናባኢነት ተጽፏል።

ስለዚህም መጽሐፍ ቅዱስ ስሕተት የሌለበት መጽሐፍ እንደሆነ ይታመናል። በው ስጡ የሚገኙ ትንቢቶች ሁሉ በጊዜያቸው የተፈጸሙና የሚፈጸሙ ሲሆኑ ጥርጣሬ የሌለ ባቸው እውነቶች ናቸው፤ «ቃልህ እውነት ነው» (ዮሐ.፲፯፥፲፯) ስለሆነም ቅዱስ መጽ ሐፍ አይለወጥም፤ አይጨመርበትም፤ አይቀነ ስለትምም «የእግዚአብሔር ቃል ሁሉ የጠራ ነው፤ እርሱ ለሚታመኑት ጋሻ ነው፤ እንዳይ

www.ethiopianorthodox.org

ዘልፍህ፡ ሐሰተኛም እንዳትሆን በቃሉ አትጨምር» ተብሎአልና (ምሳሌ ፴፥፭–፮)

ቅዱስ መጽሐፍ የእግዚአብሔር የፈቃዱ ጽሑፋዊ መገለጫ ሲሆን ዋና የአላማው ማእከልም በፍቅሩ የተከናወነው ምሥጢረ አድኅኖ ነው።

እንደ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቀኖና ቅዱስ መጽሐፍ ሰማንያ አንድ መጻሕፍትን የያዘ ከ፵ በላይ የሆኑ ሰዎች የጻፉት ነው። የጽሕፈት ዘመኑም ፲፮ ሺህ ዓመታትን ወስዶአል። ይህም የአምስቱ ብሔረ ኦሪት ጸሐፊ ሙሴ የነበረው በ፩ ሺህ ፭፻ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ሲሆን የመጨረሻው የሐዲስ ኪዳን ጸሐፊ ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ በ፻ ዓ.ም ስለ ነበረ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ብሉይና ሐዲስ ኪዳን ተብሎ በሁለት ክፍል የተከፈለ ነው። ኪዳን ማለትም ስምምነት ወይም ውል ማለት ነው። እግዚአብሔር በፍቅሩ ከሰዎች ጋር የገባውን ቃለ–ኪዳን ያመለክታል።

ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት አብዛኛው በዕብራይስጥ ተጽፏል። በጣም ጥቂት ክፍሎች ግን በሱርስት (በሶርያ ቋንቋ) ተጽፈዋል። ከክርስትና በፊት ፪፻፹፭ ዓመት ገደማ መላው የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ወደ ፅርዕ (ግሪክ) ተተርጉመዋል። የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ግን በሙሉ ለመጀመሪያ ጊዜ በፅርዕ የተጻፉ ናቸው። ርግጥ የማቴዎስ ወንጌል በዕብራይስጥ፣ የማርቆስ ወንጌል ደግሞ በሮማይስጥ እንደ ተጻፉ ይተረካል። ይሁን እንጂ አንዳንዶች በኋለኛው አይስማሙም።

ቅዱስ መጽሐፍ ብሉይና ሐዲስ ኪዳን ተብሎ በሁለት ቢከፈልም አንድ መጽሐፍ ነው። የሁለቱን አንድነት በተመለከተ በመጽሐፈ ሃይማኖተ አበው የሚከተለው አገናዛቢ ማስረጃ ተሰጥቷል።

«ከመምህራን አንዱ ስለ መጽሐፈ ብሉይና ሐዲስ እንዲህ አለ፡-

መጀመሪያው ስለ ሁለተኛው ይናገራል፤

ሁለተኛውም መጀመሪያውን ይፈጽማል፤

መጀመሪያው የሕንፃ መሠረት ነው፤

ሁለተኛውም ፍጻሜና ማሕተም ነው፤

ብሉይ ለሐዲስ አርአያና አምሳል ነው፤

እኒህ ሁለቱ እርስ በርሳቸው የተሰናሰሉና የተስማሙ የተያያዙም ናቸው፤

ለተናጋሪያቸውም በቃል እውነቶች ናቸው፤ ቃላቸው አንድ ነው፤

ከአንድ ቃል የወጡ ናቸው፤ ከአንድ ተናጋሪም የተገኙ ናቸው፤ እርሱም ክብር ይግባውና በቃሉ ፍጡራንን ሁሉ የፈጠረ ሥራዎችንም የሠራ አምላክ ነው»

(ሱኑትዩ ሃይማኖት አበው ፺፲፥፲፰–፲፱፤ ዘሐዋ.፹)።

የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፍያን በሀገር፣ በሥራ፣ በዕውቀትና በዕድሜ በዘመንም የተለያዩ ናቸው። ይህም ማለት ጸሐፊዎቹ ነቢያት፣ ካህናት፣ ጠቢባን፣ ነገሥት፣ እረኞች፣ ዓሣ አጥማጆች፣ ቀራጮችና ባለመድኃኒቶች ነበሩ።

የመጽሐፎቻቸውም አይነት ሕግ፣ ታሪክ፣ ጥበብ፣ ትምህርት፣ ቅኔ፣ ትንቢትና ራዕይ፣ ብሥራትና መልእክት ነው። ቢሆንም የሁሉም ምሥጢራዊ አቅጣጫ አንድ ነው። ሁሉም እግዚአብሔር ስለሰዎች የገለጠውን ፈቃድ፣ ያስተላለፈውን መልእክት፣ ፍቅሩንና አድኅኖቱን ይገልጣሉ። ሰብአውያን ጸሐፍቱ ብዙዎች ቢሆኑ መለኮታዊ ደራሲያቸው አንድ ነውና። እርሱም እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ነው። ስለዚህም እንዲህ ተባለ፡- «…ትንቢት ከሰው ፈቃድ ከሰውም ፍላጎት አይሆንም፤ ቅዱሳን ሰዎች ከእግዚአብሔር ተልከው በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝተው ተናገሩ እንጂ» (፪ጴጥ.፩፥፳፩)

የቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን አርቶዶክሳውያን አበው፡- ቅዱስ መጽሐፍን እንብበው ተርጉመውና አመሥጥረው ከማስተማራቸው ሌላ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የተለያዩ ሰረዮችን ተናግረዋል።

«ቅዱስ መጽሐፍ ከመንፈስ ቅዱስ የሚፈልቅ የማይነጥፍ ምንጭ፤ የመንግሥተ እግዚአብሔር መስከ፤ የዘለዓለማዊነት ገነት ነው። ከአዳም ገነት እጅግ የበለጠ፤ ያማረና የተዋበ ገነት ፍሥሐ ነው። ከዚህ ቅዱስ ምንጭ ሁል ጊዜ የሚጠጣ ሰው የመንፈስ ቅዱስን ውሒዝ በነፍሱ ይቀዳልና ብፁዕ ነው። ቅዱስ መጽሐፍን በአክብሮት፤ በግልጥነትና በንስሐ ማንበብ እንደ ቅዱስ ጥምቀት መንጽሒ ነው።» (ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ)

እንደ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ትምህርትም «ቅዱስ መጽሐፍ የእግዚአብሔር መልእክትና የራሱ ክሥተት ነው። ቅዱስ መጽሐፍ የእግዚአብሔር አይቆን (ሥዕል) ነው…» ቅዱስ ጎርጎርዮስ!

ሌላውም መምህር «መጽሐፍ ቅዱስ መጣፍ ብቻ ሳይሆን ቤተ መጻሕፍት ነው። ብዙኃት መጻሕፍትን በውስጡ ይዞአልና፤ የዕውቀትና የጥበብ፣ የሕግና የታሪክም ምንጭ ነው» ካለ በኋላ «ይሁን እንጂ መጽሐፍ ቅዱስን የምናነበው ለታሪክ ወይም ለሕግ ብለን አይደለም። ለዘለዓለማዊ ድኅነት እናነበዋለን እንጂ» ብሎአል።

ስለ ቅዱስ መጽሐፍ፡- በቅዱሳን አበው ብዙ ተብሎአል፤ እንደ ተባለውም ነው። ከሁሉም በላይ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የሚናገርበት መሣሪያ በመሆኑ ሁል ጊዜ ቃሉን እንድናነበው፤ እንድንማረው፤ እንድናስተውለውና ተግባራዊ እንድናደርገው ያስፈልጋል። ቅዱስ መጽሐፍን በምናነብበት ጊዜ ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር እንነጋገራለንና በጥንቃቄ እናንብበው፤ ቅዱስ መጽሐፍን አለማንበብ ደግሞ እግዚአብሔር ሊመክረንና ሊገሥጸን፣ ሊፈትነንና ሊያስጠነቅቀን ፈልጎ እያነጋገረን ሳለ አንፈልግህምና አትናገረን እንደማለት ይሆናል። እንደ ተባለ «…አንተ ተናገረን እንጂ…እግዚአብሔር አይናገረን…» (ዘጸአ.፳፥፲፱)

ነገር ግን በዚህ ፈንታ ከቅዱሳን ነቢያት ዳዊትና ዕንባቆም ጋር አብረን፡- «እግዚአብሔር አምላኬ የሚናገረኝን እሰማለሁ» (መዝ.፹፬፥፰) «የሚናገረኝን አውቅ ዘንድ… አመለከታለሁ» (ዕንባቆም ፪፥፩) ማለቱ ይበጀናል። ✣

# እስትግቡእ

(እስትግቡእ - ጥርቅም፣ የተቀመመ፣ የተሰባሰበ ማለት ነው)

## ሐተራይቶች

(የሐዋርያት ቤተሰቦች) ተዛማጅ ትርጉም

ካሕሳይ ገ/እግዚአብሔር

ሐተራውያን በምዕራብ አሜሪካ በደቡብ ምሥራቅ ሞንታና ግዛት በቦግሆርን ወንዝ ዳርቻ የሚኖሩ ሕዝቦች ናቸው። አካባቢው ለእርሻም ሆነ ለከብት ርቢ የተመቸ ለምለም ቦታ ነው። ሐተራውያን በሰለጠነችው አሜሪካ ውስጥ ሆነው ሥልጣኔን ንቀውና ሸሽተው ራሳቸውን ከሌላው እግልለው የሚኖሩ የተለዩ ሕዝቦች ናቸው፤ በዜግነት አሜሪካውያን ቢሆኑም በተቀረው የዓለም ሕዝብ ቀርቶ በራሳቸው በአሜሪካውያን ዘንድም ብዙ አይታወቁም።

ሐተራውያን የግል ንብረት የሚባል ነገር የላቸውም። አኗኗራቸው የጥንቱ ክርስቲያኖች (የሐዋርያት ዘመን) ሥርዓትን የተከተለ የኅብረት (የቤተሰብ) ኑሮ ነው። እያንዳንዱ ቡድን (ቤተሰብ) በውስጡ ከ፳፰ እስከ ፻፳ ሰዎችን ይይዛል። በአብዛኛው የቤተሰቡ ቁጥር በ፻፳ የተወሰነው ነው። ይህም የጌታችን የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፻፳ ቤተሰቦችን ለማስታወስ (በአርአያነት ለመከተል) የሚጠቀሙበት ብልሃት ነው።

የአንድ ቤተሰብ ቁጥር ከ፻፳ ከበለጠ በቤተሰቡ አባላት አጠቃላይ ስብሰባና ውሳኔ ከመካከላቸው ፳፰ ሰዎች ተመርጠው የራሳቸው አዲስ ቤተሰብ እንዲመሠርቱ ይደረጋል። በነገራችን ላይ ሐተራውያን የግል ንብረት ባይኖራቸውም የጋራ (የቤተሰብ) የሆነ ሀብትና ንብረት አላቸው። በመሆኑም አንድ ቤተሰብ ከእናት ቤተሰቡ ተነጥሎ «ጉጅ» እንዲወጣ ሲደረግ ለጉጆ መውጫ የሚሆን በጥሬ ገንዘብ ከ፰ እስከ ፲፭ ሚሊዮን ዶላር፣ ለእርሻና ለከብት ርቢ የሚሆን ፹ ማይልስ ርዝማኔ ያለው መሬትና አንድ ሺህ ከብት ይሰጠዋል።

ሁሉም ቤተሰብ (ነባርም ሆነ አዲስ) የሚያገኘው የመሬት ስፋት እኩል ነው። እያንዳንዱ ቤተሰብ በአባላቱ ሙሉ ፈቃደኝነት የሚመረጥ አንድ መሪ (የቤተሰብ አባት) አለው። የከብት እረኛን ከመቅጠር ጀምሮ ሌሎች ጉዳዮችን በኃላፊነት የሚያስፈጽመው የቤተሰብ አባት ነው።

ሐተራውያን ቤቶቻቸውን የሚሠሩት በአካባቢያቸው በቀላሉ በሚያገኙዋቸው እንደ እንጨትና የወዳደቁ ብረታ ብረቶች አማካኝነት ነው። ሌላው ቀርቶ አብያተ ክርስቲያኖቻቸውንም ቢሆን የሚሠሩት ውድ ባልሆኑ የአካባቢያቸው ቁሳቁሶች ነው።

ከመግቢያው ለመግለጽ እንደ ተሞከረው ሐተራውያን ዘመናዊነትን (ሥልጣኔን) በጥርጣሬና በንቀት ዓይን ነው የሚመለከቱት። ይሁንና በዚህ በኩል ያላቸው አመለካከት የተወሳሰበ ነው ማለት ይቻላል። በአንድ በኩል ዘመናዊነትን ይቃወማሉ፤ የዘመኑ ሳይንስ በወለዳቸው መሣሪያዎች መገልገልን ይጠላሉ። በሌላ በኩል ደግሞ የጥንት ሥሪት የሆኑ እንደ ግልጽ ፒክአፕ ቶዮታዎች፣ ለእውድማ አጨዳና ለመውቅያ የሚያገለግሉ የእርሻ መኪናዎች፤ የጥንት መኪናዎችን ይጠቀማሉ። ሁሉም መኪናዎቻቸው እ.አ.አ.ከ፲፱፻፶ ዓ.ም በፊት የተሠሩ ናቸው።

እነዚህን መኪናዎች ሲበላሹ የሚሠሩዋቸው፣ ሲሰበሩ የሚጠግኑዋቸው፣ ባለሞያዎች (ቴክኒሻኖች) ዕውቀታቸውን ከቀደምት አባቶች በልምድ የወረሱት ችሎታ ነው። ሌላው አስገራሚ ነጥብ የሁሉም ሐተራውያን የትምህርት ደረጃ ተመሳሳይ መሆኑ ነው። በእነርሱ ዘንድ ከማንበብና መጻፍ በላይ የዘለለ ትምህርት አስፈላጊ አይደለም። ሐተራውያን ብዙ መማርና ማወቅ ውሸትን፣ ማታለልን፣ ራስ ወዳድነትን ያስከትላል፤ ሌላው ቀርቶ ቴሌቪዥን አይመለከቱም። አሁን አሁን ግን በድብቅ ቴሌቪዥን የሚያዩ አንዳንድ ሐተራውያን ወጣቶች መከሰት እንደ ጀመሩ ይሰማል።

ሬዲዮን ግን ይጠቀማሉ። ይሁንና ሬዲዮን የሚጠቀሙት የዕለት የአየር ትንበያዎችን ለመከታተል (ለማዳመጥ) ብቻ ነው። ከዛ ውጭ ዜናና ዘፈን የመሳሰሉት ፕሮግራሞችን ፈጽመው አያዳምጡም። የዘመኑን ኢንተርኔትንም በጥርጣሬ ነው የሚመለከቱት። ይሁንና በቅርቡ ከ፴፱ የሐተራውያን ቤተሰቦች መካከል አንዱ ብቻ የራሱ የሆነ ዌብሳይት እንዲኖረው አድርጓል። አልፎ አልፎም በፀሐይ ኃይል በሚሠራ ስልክ የሚጠቀሙ ሐተራውያን ቤተሰቦችም ብቅ ብቅ ማለት ጀምረዋል።

የሐተራውያን አንዱ አስገራሚ ባህል ሀብታም ለመሆን ያለመፈለጋቸው ጉዳይ ነው። ለሐተራውያን «የእለት እንጀራችንን ስጠን ዛሬ» የምትለዋን የአምላክ ቃል በቂ ናት። ታድያ ሀብታም መሆንን የሚጠሉትን ያህል ማጣትንም አይፈልጉም። እንደዛም ሆኖ በጋራ ከሚያመርቱዋቸው የተለያዩ ምርቶች የግዛቲቱን (ሞንታና (፰%) የዓሣማ ሥጋ ፶% የእንቁላል አቅርቦት ፲፯% የወተት ምርት ይሸፍናሉ። በሞንታና ግዛት ውስጥ ባሉት ፴፱ ቤተሰቦች ፬ ሺህ (አራት ሺህ) ያህል ሐተራውያን ይገኛሉ።

ሐተራውያን እንደተቀሩት አሜሪካውያን የሕክምናም ሆነ የሕይወት ዋስትና የላቸውም። በእነርሱ እምነት ሰው ሲታመም በእግዚአብሔር ኃይል ይድናል። ከሞተም የእግዚአብሔር ትእዛዝ ነውና ምንም አይደለም። ከዚህ ውጭ «ድሎትና ምቾት ሲበዛ የክርስትና እምነት ይደበዝዛል» ባዮች ናቸው። ይህ ስለተባለ ግን በምግብ ራሳቸውን ይጎዳሉ ማለት አይደለም። ቤታቸውን፣ ግቢያቸውን፣ የግል ንጽሕናቸውን በሚገባ ይጠብቃሉ። ምግባቸውን በሥርዓት አዘጋጅተው ይመገባሉ። ከሁሉም በላይ ቤተሰባዊ አንድነታቸው፣ የፍቅር ትስስራቸው የጠበቀ ነው፤ አንዱ ለአንዱ ተሰባስቦ፣ ተዛዝኖ፣ አንዱ ሌላውን ከራሱ አስበልጦ ይኖራል። ሐተራውያን ትርፍ ሃብታችን ፍቅር ነው ይላሉ። ለዚህም ይመስላል በሐተራውያን ዘንድ ስርቆት፣ ውሸት፣ ማታለል የመሳሰሉ ጉጂ ልማዶች ጨርሰው አይታወቁም። ሌብነት ስለማይታወቅም የሐተራውያን ቤቶች በር እንጂ ቁልፍ የላቸውም።

ሐተራውያን ለራሳቸው የሚበቃቸው ምግብ የሚያመርቱ ቢሆንም በአካባቢያቸው ለማይመረቱ አንዳንድ ቁሳቁሶች መግዣ የሚሆን ተጨማሪ ገንዘብ ሲያስፈልጋቸው ወጪአቸውን የሚሸፍኑት አደን አድነው በሚያገኙት ገቢ ነው። መኪና የሚያገኙት ግን በግዥ መልክ ሳይሆን በፈረስ በመለወጥ ነው። በነገራችን ላይ የሐተራውያን እረኛ ፒክ አፕ ቶዮታ መኪናና (መስተዋት የሌለው) ፈረስ ሊኖረው የግድ ነው። እረኛው ከሐተራውያን ቤተሰብ ውጭ ከሌላ ቦታ ተቀጥሮ የሚመጣ ሲሆን ለራሱ ለፈረሱና ለመኪናው የሚሆን ቤት፣ ለራሱና ለፈረሱ ከሚሆን ምግብ ሌላ በገንዘብ መልክ የሚሰጠው ክፍያ የለም።

ሐተራውያን ሥራቸውን ብቻ ሳይሆን ምግባቸውንም የሚመገቡት በአንድነት ሆነው ነው። በተለይ ዘወትር ከቀኑ ፲፩፡፴ ሲሆን ቤተ ሰብ በሙሉ በአንድነት ተሰባስቦ ማዕድ ይቀርባል። ብዙውን ጊዜ ወንዶችና ሴቶች በተለያየ ጠረጴዛ ይመገባሉ። ምን ጊዜም ቢሆን ሴቶች ረገርኝም ቀሚስ መልበስና ፀጉራቸውን በሻሽ መሸፈን፣ በሥራ ሰዓት ሽርጥ መደረብ (ማገልደም) አለባቸው።

ሐተራውያን በራሳቸው የፍቅርና የሰላም ሕዝቦች ቢሆኑም ጎረቤቶቻቸው ሕንዳውያን በሚፈጽሙባቸው ሕገ ወጥ ድርጊት የተነሳ መጠነኛ ቅራኔ መከሰቱ አልቀረም። ለዚህ መንስኤ የሆነው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ወጣት ክሮው ሕንዳውያን በቡድን በመደራጀት የሐተራውያንን ከብቶችና እህል መዝረፍ በመጀመራቸው ነው። ሐተራውያን ግን በዚህ ተነሳስተው የአጸፋ እርምጃ አልወሰዱም። እንዲያውም «ሕንዳውያን ከጥንት ጀምሮ ወዳጆቻችንና ጥሩ ጎረቤቶቻችን ናቸው ችግር የተከሰተው በአሁኖቹ ወጣት ሕንዳውያን አማካኝነት ነው፤ ለዚህ ደግሞ ተጠያቂዎቹ የሰለጠኑ (ነጮ) አሜሪካውያን ናቸው። ምክንያቱም ውሸት፣ ሌብነትና ማታለልን የመሳሰሉ እኩይ ተግባራትን ያስተማርዋቸው እነርሱ ናቸውና» ይላሉ።

ሐተራውያን ተግባራቸው፣ ባሕላቸው ከመጀመሪያዎች ክርስቲያኖች ጋር ይመሳሰላል ብለናል። ሌላው ቀርቶ በየአብያተ ክርስቲያኖቻቸው የሚጠቀሙባቸው የእምነት መጻሕፍት ሁሉ ከዛሬ ፬፻፶ እና ፫ መቶ ዓመታት በፊት የተጻፉ የብራና መጻሕፍት ናቸው። ሐተራውያን ሃይማኖታዊ ሥርዓታቸው ብቻ ሳይሆን ማኅበራዊ ሕግጋቶቻቸውም ሁሉ ከእነዚህ ጥንታውያን መጻሕፍት የተገኙ ናቸው። ሁሉም ሐተራውያን ቤተ ክርስቲያናቸው በምታወጣላቸው ፕሮግራም መሠረት በየዕለቱና በየሳምንቱ የጋራ ጸሎት ያከናውናሉ፤ ለኑሮአቸው የሚያስፈልግዋቸው የሕይወት መመሪያዎችና ደንቦችንም የሚያጠኑት በቤተ ክርስቲያን ነው። እያንዳንዱ ሐተራዊ ኢየሱስ ክርስቶስ ፈጣሪና የዓለም መድኅን መሆኑን አምኖ መቀበል ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር ሕግጋትን በተግባር የመፈጸም ግዴታ አለበት።

ሐተራውያን ሴቶች የራሳቸው የሆነ በሕግ የተደነገገ የአለባበስ ሥርዓት እንዳላቸው አይተናል። የአለባበሱ ሥርዓት ግን በሴቶች ብቻ የተወሰነ አይደለም። ወንዶቹም ቢሆኑ አለባበሳቸው አንድ ወጥ ነው። ሁሉም ወንዶች ባለማንገቻ ጥቁር ሱሪና (ቀበቶ አይፈቀድም) ኪስ የሌለው ሸሚዝ ነው የሚለብሱት። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ወጣት ሐተራውያን የቆየው የአለባበስ ሥርዓትን ላለመቀበል ማንገራገር ጀምረዋል። ለወጣቱ ትውልድ ይበልጥ አልዋጥ ያለው ጥቁር ሱሪ ያልለበሰ ወንድ ገነት አይገባም የሚለው የቆየ አባባል ነው።

አባውንቱ ሐተራውያን ግን የአዲሱን ትውልድ የለውጥ አመለካከት አልወደዱትም። የእድሜ ባለጸጎቹ «ጥቁር ሱሪ ለሐተራውያን እንደ አንድ መለያና የሕልውና ምልክታችን ነው፤ ይህ ከተቀረ ማንነታችንም አብሮ ይጠፋል» ባዮች ናቸው። የሆነስ ሆነና በ፳፩ኛው ክፍለ ዘመን የ፩ኛው ክፍለ ዘመን ሰዎች (ያውም በአሜሪካ) መኖራቸው አይገርምም?

ምንጭ ዘ.ኢኮኖሚስት እ.አ.አ.ጥር ፳/፲፬/፪ ሺህ ዓ.ም





www.ethiopianorthodox.org